# የኢትዮጵያ የ5 ሺ ዓመት ታሪክ

## ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ

## መጽሐፍ ፩

ፍስሐ ያዜ ካሣ

2003
አዲስ አበባ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ ሕትመት 2003 ዓ.ም.
ሁለተኛ ሕትመት 2004 ዓ.ም.
ሶስተኛ ሕትመት 2004 ዓ.ም.
አራተኛ ሕትመት 2005 ዓ.ም.

**መታሰቢያነቱ :-**

ለክቡር አቶ ተክለሃይማኖት መኩሪያ እና ለሌሎች ላለፉ ቀደምት ኢትዮጵያዊ የታሪክ ፀሐፍት።

**ማስወሻነቱ:-**

ለፍቅርተ ሁሴን አብዲ እና ለቤተሰቦቿ፤ እንዲሁም ለዳዊት እወቀ እና ለቤተሰቦቹ ይሁንልኝ።

**ምስጋና:-**

ለወ/ሮ እታፈራሁ አበበ
እና
ለወ/ት አሰምነሽ ታከለ
እንዲሁም አስቸጋሪውን የመተየብ ሥራ ያለመታከት ላከናወነችው ለወ/ት ትዝታ ላቀው
ምስጋናዬንም አክብሮቴንም ገለጽኩ።

ለአስተያየትዎ:- Fiseha Yaze@yahoo.com
Only text:- 0921797053

## ማውጫ

| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 8 |
| 2 | መግባቢያ | 11 |
| 3 | ምዕራፍ 1 ኖኅ እና ኢትዮጵያ | 21 |
| 4 | ምዕራፍ 2<br>የነገደ ካም ዘመነ መንግስት ከ3500 እስከ 1985 ቅ.ል.ክ | 30 |
| 5 | ምዕራፍ 3<br>ኢትዮጵያና ባቢሎን | 34 |
| 6 | ምዕራፍ 4<br>አርጌው ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ | 44 |
| 7 | ምዕራፍ 5<br>የአጋዝያን ዘመነ መንግስት | 55 |
| 8 | ምዕራፍ 6<br>የኢትዮጵያ ትክክለኛ መጠሪያ ስም | 70 |
| 9 | ምዕራፍ 7<br>የአክሱም ኢትዮጵያና የኑብያ ኢትዮጵያ ልዩነትና አንድነት | 79 |
| 10 | ምዕራፍ 8<br>ኢትዮጵያ በታላቁ መፅሃፍ | 82 |
| 11 | ምዕራፍ 9<br>የግብፅ ስልጣኔ | 85 |
| 12 | ምዕራፍ 10<br>የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ | 91 |
| 13 | ምዕራፍ 11<br>ከንግስተ ሣባ እስከ ንጉስ ባዚን የነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታት ዝርዝር | 95 |
| 14 | ምዕራፍ 12<br>የንግስተ ሣባ ታሪክ | 99 |
| 15 | ምዕራፍ 13<br>የቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግስት | 104 |
| 16 | ምዕራፍ 14<br>ከንጉስ ሐንድዮን እስከ ንጉስ ተዋስያ2ኛ | 108 |
| 17 | ምዕራፍ 15<br>የኢትዮጵያ ግዛት በግብፅ ላይ፤ በንጉስ ፒያንኪ 2ኛ ዘመነ መንግስት | 110 |
| 18 | ምዕራፍ 16<br>የአክሱማይ ወረደ ፀሐይአና የካስታህ ሐን ድዮን ዘመነ መንግስት | 118 |
| 19 | ምዕራፍ 17<br>የንጉስ ሻባካ ዘመነ መንግስት | 120 |
| 20 | ምዕራፍ 18 | 122 |

የንግስት ኒካንታ ህንዳኬ ዘመነ መንግስት

21 ምዕራፍ 19 — 123
የንጉስ ቲሃርቃ ዘመነ መንግስት

22 ምዕራፍ 20 — 128
የንጉስ ታንታሙን ዘመነ መንግስት

23 ምዕራፍ 21 — 132
የመናገሻ ከተማ ለውጥ ከናፓታ ወደ መርዌ

24 ምዕራፍ 22 — 134
የንጉስ ናስቶስኔን ዘመነ መንግስት

25 ምዕራፍ 23 — 136
የንጉስ ሐንዲው አብራ ዘመነ መንግስት

26 ምዕራፍ 24 — 140
የመርዌ መዳከም

27 ምዕራፍ 25 — 142
የአክሱም አነሳስና አመሠራረት

28 ምዕራፍ 26 — 151
የአክሱማውያን /የኢትዮጵያውያን/ የፊደል አመጣጥ

29 ምዕራፍ 27 — 155
የአክሱማውያን ቀደምት እምልኮና የክርስትና ወደ
ኢትዮጵያ መግባት

30 ምዕራፍ 28 — 159
የአክሱማውያን ገንዘቦችና በላያቸው ላይ የሰፈረው ጽሁፍ

31 ምዕራፍ 29 — 161
የንጉስ ዒዛና እና ሲዛና /የአብርሃ ወ አፅባሃ/ ዘመነ
መንግስት

32 ምዕራፍ 30 — 173
የንጉስ እለዓሜዳ ዘመነ መንግስት

33 ምዕራፍ 31 — 175
የአፄ ካሌብ ዘመነ መንግስት

34 ምዕራፍ 32 — 181
የአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስት

35 ምዕራፍ 34 — 187
የንጉስ አርማህ 2ኛ ዘመነ መንግስት

36 ምዕራፍ 33 — 189
የእስልምና መስፋፋት

37 ምዕራፍ 35 — 194
የዮዲት ጉዲት ዘመነ መንግስት

38 ምዕራፍ 36 — 198
አክሱምና በአካባቢዋ የሚገኙ ቅርሶች

39 ምዕራፍ 37 — 201
የዛግዌ ስርወ መንግስት አመሠራረትና የመስራቹ የንጉስ
መራ ተክለሐይማኖት ዘመነ መንግስት

40 ምዕራፍ 38 — 204
ከአፄ ጠጠውድም እስከ አፄ ይምርሐነ ክርስቶስ

41 ምዕራፍ 39 — 207
የቅዱስ ሐርቤ 2ኛ ዘመነ መንግስት

42 ምዕራፍ 40 — 210
የአፄ ላሊበላ ዘመነ መንግስት

43 ምዕራፍ 41 — 218
የስልጣን ሽግግር ከላስታ ወደ ሽዋ፣ በአፄ ነአኩቶለአብ
ዘመነ መንግስት

44 ምዕራፍ 42 — 222
የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ማኅበረሰቦች

45 ምዕራፍ 43 — 224
የሸዋ ነገስታት

46 ምዕራፍ 44 — 228
የአፄ አምደጽዮን ዘመነ መንግስት

47 ምዕራፍ 45 — 239
የአፄ ሠይፈ አርዕድ ዘመነ መንግስት

48 ምዕራፍ 46 — 241
የአፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት

49 ምዕራፍ 47 — 246
የአፄ ቴዎድሮስ 1ኛ ዘመነ መንግስት

50 ምዕራፍ 48 — 249
የአፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግስት

51 ምዕራፍ 49 — 252
የአፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግስት

52 ምዕራፍ 50 — 264
የአፄ በእደ ማርያም ዘመነ መንግስት

53 ምዕራፍ 51 — 268
የአፄ እስክንድር ዘመነ መንግስት

54 ምዕራፍ 52 — 271
ቱርክ፣ ፖርቹጋልና ኢትዮጵያ

55 ምዕራፍ 53 — 274
የአፄ ናኦድ ዘመነ መንግስት

56 ምዕራፍ 54 — 280
የአፄ ልብነድንግል ዘመነ መንግስት

57 ምዕራፍ 55 — 284
የግራኝ አህመድ የበላይነት

58 ምዕራፍ 56 — 291
የአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግስት

59 ምዕራፍ 57 — 299
የአፄ ሚናስ ዘመነ መንግስት

60 ***ምዕራፍ 58*** 302
የጎንደር ነገስታት ዘመን
61 ***ምዕራፍ 59*** 304
የአፄ ሠርፀድንግል ዘመነ መንግስት
62 ***ምዕራፍ 60*** 311
የአፄ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት
63 ***ምዕራፍ 61*** 313
የአፄ ዘድንግል ዘመነ መንግስት
64 ***ምዕራፍ 62*** 315
የአፄ ሱስኒዮስ ዘመነ መንግስት
65 ***ምዕራፍ 63*** 319
የአፄ ፋሲል ዘመነ መንግስት
66 ***ምዕራፍ 64*** 332
የአፄ ዮሐንስ 1ኛ ዘመነ መንግስት
67 ***ምዕራፍ 65*** 336
የአፄ እያሱ 1ኛ ዘመነ መንግስት
68 ***ምዕራፍ 66*** 344
የአፄ /ርጉም/ ተክለሐይማኖት ዘመነ መንግስት
69 ***ምዕራፍ 67*** 348
የአፄ ቴዎፍሎስ ዘመነ መንግስት
70 ***ምዕራፍ 68*** 350
የአፄ ዮስጦስ ዘመነ መንግስት
71 ***ምዕራፍ 69*** 351
የአፄ ዳዊት 3ኛ ዘመነ መንግስት
72 ***ምዕራፍ 70*** 355
የአፄ በካፋ ዘመነ መንግስት
73 ***ምዕራፍ 71*** 357
የአፄ እያሱ 2ኛ ዘመነ መንግስት
74 ***ምዕራፍ 72*** 364
የአፄ ኢዮአስ ዘመነ መንግስት
75 ***ምዕራፍ 73*** 366
የአፄ ዮሐንስ 2ኛ ዘመነ መንግስት
76 ***ምዕራፍ 74*** 369
የአፄ ተክለሐይማኖት 2ኛ ዘመነ መንግስት
77 ***ምዕራፍ 75*** 371
የአፄ ሰሎሞን ዘመነ መንግስት

78 ***ምዕራፍ 76*** 372
የአፄ ተክለጊዮርጊስ ዘመነ መንግስት
79 ***ምዕራፍ 77*** 374
ዘመነ መሳፍንት፤ ከትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ
80 ***ምዕራፍ 78*** 376
የአፄ ቴዎድሮስ 2ኛ ዘመነ መንግስት
81 ***ምዕራፍ 79*** 401
የአፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ ዘመነ መንግስት
82 ***ምዕራፍ 80*** 404
የአፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመነ መንግስት
83 ***ምዕራፍ 81*** 424
የአፄ ምኒልክ 2ኛ ዘመነ መንግስት
84 ዋቢ መጻሕፍት 454

## መግቢያ

ከሳይንሱ አንፃር የዓለምና የህዝቦቿ ታሪክ የሚጀምረው ከሚሊዮኖችና ከቢሊዮኖች አመታት በፊት ነው።

ከመንፈሣዊ ትንታኔ አንፃር ደግሞ የዓለምና የሠው ልጆች ታሪክ የሚጀምረው ከአዳም መፈጠር በኋላ ነው። ዘመኑም ከክርስቶስ ልደት በፊት 5500 ዓመት ተብሎ ይሰላል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ ከላይ ወደታች ወደ ኋላ እየተቆጠረ ኖሮ፤ ከክርስቶስ ውልደት በኋላ ደግሞ እንደ አዲስ "አንድ" ተብሎ ወደፊት መቆጠር ጀምሮዋል። ስለዚህም በዚህ መፅሃፍ የተካተቱት ታሪኮች የሚታወሱትም ሆነ የሚያጠነጥኑት "የሠው ልጆች የፍጥረት መጀመሪያ አዳም ነው" በሚለው መነሻ ይሆናል።

ሣይንስ መነሻችን ሲነግረን ቢዳዳም. መድረሻችን እስካላሳወቀን ድረስ ሁሉም ከጥያቄ አይድንም። ስለዚህ ሠው ከ"ዱዳሌብ አፈር፣ ከኮራብ እሣት፣ ከአዜብ ነፋስና ከናጌብ ውሐ ተውጣጥቶ ተፈጠረ፤ ከፈጣሪው ነባቢነትን፣ ልባዊነትን፣ ህያውነትን አገኘ፣ የፍጥረታት የበላይ እንዲሆንም ተደረገ። ህግ ተሠጠው፣ ያንን ህግ ተላለፈ፣ ቅጣቱ ሞት ሆነ። "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሣለህ ሞትንም ትሞታለህ.."ተባለ። ይሄው ዛሬ ድረስ እየሞትን ነው። ሳይንስ ሞትን እስኪያስቀር ድረስ የትኛውን መነሻ መምረጥ እንዳለብን መድረሻችን በራሡ ስለሚነግረን ብዙ ማለት አያስፈልገንም።

ምንም ቢሆን ግን የኢትዮጵያን ታሪክ በተመለከተ መፈናፈኛ የለም። በከርሠ ምድር ጥናት ቢባል በምን.. ያው የሠው ዘር መገኛነቷ የተረጋገጠ ነው።

ለማንኛውም ግን በዚህ መፅሃፍ የኢትዮጵያ ዘመን ሲቆጠር የ5844 አመታት እድሜ ያላት አገር ሆና ነው የምናገኘው። ይህም ሲባል የኢትዮጵያ ታሪክ ከ "ኖኅ" ስለሚጀምር ከክርስቶስ ልደት በፊት 3844፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ 2ሺ. አመት ስላለ በድምሩ 5844 ዓመታት ይሆናል።

የዘመን አቆጣጠርን በተመለከተ ከወዲሁ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ። "ዓመተ ዓለም" ሲባል ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላ እየተቆጠረ ሲመጣ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲባል ግን ከውልደቱ



ዋዜማ ተነስተን ወደ ላይ እየቆጠርን ስንሄድ የምንደርስበት ነው። ስለዚህ ዓ.ዓለምና ቅ.ል.ክ ሠፊ ልዩነት አላቸው። በጥንታዊ ታሪኮች ላይ በተደጋጋሚ በብዙዎች ዘንድ ውዝግብ ሲፈጥር እንደመኖሩ መጠን በአንድ ምሣሌ ገልፀነው እንለፍ።

ለምሳሌ በምድር ላይ የጥፋት ውሃ ሲደርስና ኖኅና ቤተሠቦቹ ብቻ የተረፉበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት 3844 ላይ ነበር። ይህ በዓመተ ዓለም ሲሠላ 1656 ዓ.ዓለም ተብሎ ይገለፃል። በድምሩ 5500 አመት ይሆናል። ዓለም በተፈጠረ በ1656 ዓ.ዓ ላይ የጥፋት ውሃ ተከሠተ እንደማለት። ከዚሁ ጋር በተያያዘም "አንድ አመት" የሚባለው በጨረቃ አቆጣጠር 254 ቀናትን ስለሚሸፍንና በፀሃይ አቆጣጠር "አንድ አመት" 365 ቀናትን ስለሚሸፍን በተለይ የፀሐይ አቆጣጠሩ ግኝት ከሠው ልጆች እስኪመነጭ ድረስ የነበረው ጊዜ በመጠኑ ሊያወዛግብ ቢችል ቅር ልንሰኝ አይገባም። ያም ቢሆን ከክ.ል በፊት 3ሺ. አመታት ቀደም በሚለው ታሪክ እንጂ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ አያጋጥምም። ይህንኑም ቢሆን ለማስተካከል ተሞክሯል። በታሪኩ ውስጥ ከክ.ል በፊት እየተባለ ስለተገለፀም ብዙ ችግር አይኖርም። በዋናነት ቀድሞ መግለፅ ያስፈለገበት ምክንያት የሌሎች ፀሃፍትን የዘመን አገላለፅ እንደወረደ በምናይበት ጊዜ ግር እንደይለን ነው። በተረፈ እንደተለመደው (እ. ኤ. አ) ከሚሉት በቀር ሌሎች ሁሉ በ፣ አቆጣጠር ናቸው።

የኢትዮጵያን የብዙ ዘመንና ተዘርዝሮ የማያልቀውን ታሪካ በአንድ መፅሃፍ ብቻ መፈፀሙ አስገራሚ ሊመስል ይችላል። ምክንያቱ. የአንድ ኢትዮጵያዊ ንጉሠ ነገስት ታሪክ እንኳን ብቻውን ከዚህ መፅሃፍ ገፆች በላይ እንደሚወስድ ይታወቃልና ነው። ቢሆንም የረዘመውን በማሣጠር፣ የተዘበራረቀውን በማደራጀት፣ የሚምታታውን አመሣክሮ በማስማማትና አሣማኝ ማስረጃ የተገኘለትን መርጦና አሣጥሮ ይዘቱን ሣይለቅ ለማቅረብ ተሞክሯል። ለነገሩ እንዲህ ለማለት የሚያስችል የመረጃ ክምር የለም። ቀደምት ፀሃፍትም ቢሆኑ የአንድ፣ የሁለት፣ የሦስት ሚሊኒየምን ታሪክ ሲፅፉ የነገስታቱን ስም ዝርዝርና የገዙበትን ዘመን አስፍሮ ከማለፍ ውጪ ዝርዝር ታሪኩን ለማተት የቻሉበት ሁኔታ በስፋት የለም። የመረጃ እጥረት ይገድባል። የዚህ መፅሐፍ ዓላማ ደግሞ በተቻለ መጠን ጎደለውን መሙላት፣ ሊፈርስ የተቃረበውን ከ3 ሺ አመት በፊት የነበረውን የኢትዮጵያን የታሪክ አጥር መጠጋገን ነው።

"የኢትዮጵያ የ5 ሽ. አመት ታሪክ - ከኖኅ እስከ ኢሕአዴግ" በሚል ርእስ የቀረበው ይህ መጽሐፍ በዚህ ጥራዙ እስከ አፄ ምኒልክ ድረስ

ያለውን ታሪክ ያካተተ ሲሆን፤ በቅርቡ የልጅ እያሱ፣ የንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ፣ የአፄ ሀይለስላሴ ፣ የደርግና የኢሕአዴግ ዘመን ታሪኮችን ያካተተው ተከታይ ክፍል ይከተለዋል። የ100 ዓመት ታሪክ አስተርፈናል ማለት ነው። በግልጽና በጠራ መንገድ መተንተንና ሰፋ ተደርጎ መዳሰስ ያለበትም ነው። ስለዚህ ካልተዘመረለት እያሱ እስከተዘመረለት ኢሕአዴግ ድረስ የነበረውን ታሪክ በሌላ ጥራዝ እናገኘዋለን።

በዚህ መፅሃፍ ውስጥ በአንድ ምዕራፍ ስር የምዕራፉ ባለቤት የሆኑ ነሲገስታት በዘመናቸው የፈፀሟቸውና በዘመናቸው የተፈፀሙ ታሪካዊ ክንውኖች ተጣምረው ስለሚገኙ "የንጉስ እገሌ ዘመነ መንግስት" እያልን ይሆናል የምንቀጥለው። ለምሳሌ "የአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስት" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ የቅዱስ ያሬድ ታሪክም አብሮ ተካቶ ይገኛል፣ የንጉስ ሐንዲው አብራ ዘመነ መንግስት በሚለው ምዕራፍ ውስጥ ኢትዮጵያ ፋርስን በጦርነት ድል ያደረገችበት ታሪክ ተካቶ ይገኛል ወዘተ…። ይህ ማለት ግን አንዳንድ ጉዳዮች ለብቻቸው ምዕራፍና ርዕስ ተሠጥቷቸው አይገኙም ማለት አይደለም።

የነገስታቱን ታሪክ በተመለከተ ሙሉ ታሪካቸው የተገኘውንና ሠፋ ያለ ታሪክ የተፃፈላቸውን ሠፋ ባለሁኔታ፣ መጠነኛ ታሪክ ያላቸውን ከነመጠነኛ ታሪካቸው የአጭር ታሪክ ባለቤቶችንም ከነአጭር ታሪካቸው፣ የ "በጣም አጭር" ታሪክ ባለቤቶችንም ከነ "በጣም አጭር" ታሪካቸው፣ ከስማቸው በቀር ታሪካቸው ያልተገኘውን ወይም የጠፋውን ደግሞ ዝርዝራቸውን ብቻ አስፍሮ ለማለፍ ግድ የሚልበት ሁኔታ ይኖራል። መጥፎ እድል ሆኖ በስም ተዘርዛሪዎች ይበዛሉ።

"ያለፈ ታሪክን አለማወቅ አሁን ያለበትን ሁኔታ ከማዘንጋት ባለፈ የወደፊቱን አቅጣጫና አካሄድም እንዳናውቅ ይከለክለናል" ይባላል። እውነት ነው። ስለዚህ የትናንቷን ኢትዮጵያ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን መረዳት የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ለማወቅ፣ የወደፊቷን ኢትዮጵያም ለማየት ያስችለናል።

የሠው ልጅ ባለፈ.ታሪኩ መማር እንጂ መማረር እንደማይገባው ይታወቃል። ከዚህ አንፃር ይህ መፅሃፍ ከታሪክ የሚገኘውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ለማስገኘት እንጂ ለሌላ ለምንም ሲፃፍ አይችልም። ከዚህ ክብ በወጣ አካሄድና አተረጓጎም እየተረጎመ የሚቆጭ አንባቢ ይኖራል ብዬም አላስብም።

በተረፈ የሚጠቀሁ የታሪክ ምንጮች በየዕሁፉ ጣልቃ የሚገኙ ሲሆን፣ በስተመጨረሻ በጥቅል ሠፍረው ይገኛሉ።



## መግባቢያ

የምንግባባው በብዙ ነገር ነው። በዋናነት ግን በአንድ፣ በሁለት፣ ወይም በሶስት ነጥቦች ላይ መግባባት ይኖርብናል። ስለኢትዮጵያ ታሪክ የሚያትቱ የተለያዩ ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ሰነዶች አሉ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያን ታሪክ በሚመለከት አንድአይነትና ወጥ የሆነ ድምዳሜ ላይ ሊያደርሱን ሳይችሉ ቀይተዋል፤ይህም ሲባል በተለያዩ ፀሀፍት እይታ የኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ ዘመን የተለያየ ሆኖ ተጽፎ ስለሚገኝ ነው። ከዚህ አንፃር አንዱን የታሪክ ሰነድ ከሌላው ጋር እያገጣጠምን መቀጠል የግድ ይሆናል። ለአብነት ያህል ይቺን ሀገር በሚመለከት ከሰፈሩ ፅሁፎች ከብዙ በጥቂቱ ስናይ በምን አይነት ሁኔታ ከወዲሁ መግባባት እንዳስፈገን እንረዳለን።

"….. እምላክም በምስራቅ በዔድን ገነትን ተከለ። የፈጠረውንም ሠው ከዚያው አኖረው… ለማየት ደስ የሚያሠኘውን፣ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ። ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔድን ይወጣ ነበር። ከዚያም ለአራት ክፍል ይከፈል ነበር። የአንደኛው ወንዝ ስም ፈሶን ነው። እርሡም ወርቅ የሚገኝበትን የኤውላጥ ምድርን ይከብባል። የዚያም ምድር ወርቅ ጥሩ ነው። ከዚያም ሉልና የከበረ ድንጋይ ይገኛል።

- የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው፡ እርሡም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል። የሶስተኛሡም ወንዝ ስም ጤግሮስ ነው። እርሡም በአሦር ምስራቅ የሚሄድ ነው። አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው። እምላክም ሠፁን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው…"/ መፅሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ከቁ 8-16/

ነገር ግን የሠው ልጅ ሣተ። ትዕዛዝ በመተላለፉም ከምቹ መኖሪያው ሊፈናቀል ግድ ሆነ። ፈጣሪውንም አሣዘነ ማለት ነው። ስለዚህ ፈጣሪ ለአዳም እንዲህ ይለዋል።

"… ምድር ካንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን። በህይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርሷ ትበላለህ።… የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደመጣህባት ምድር እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ። አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሣለህና…" /ምዕ. 3 ከቁ16-20/

"…የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ አዳምንም አስወጣው። ወደ ህይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና

የምትገለባበጥ የነበልባል ሠይፍን በዔድን ገነት ምስራቅ አስቀመጠ።"/ ምዕ 3 ከቁ 23-24/

ወደ ዓለማዊ የታሪክ መፃህፍት ስንመጣ፡-

"... ኦፊር የአፍሪካውያን አባት ለዛሬዎቹ አፋሮች አባት ነው። በኦፊር ስም በዛሬው አውሣ የሚገኘው ወርቅ ኦፊር ይባል ነበር። ዋና ከተማው ተርሴስ ነው። እርሡም በሠለሞን ዘመነ መንግስት የታወቀ ወርቅ ስለነበረ የኦፊር ወርቅ ክቡር ነበር። በኦፊር አገሩን/አህጉሩን/ አፍሪቃ፣ ሠዎችን አፍሪካዊ ይሉዋቸዋል።.."/ መፅሃፍ አብርሃት በመሪ ራስ አማን በላይ/

"... ኢት ስጦታ፣ ዮጵ ብጫ ወርቅ ወይም እንቁ፣ ግዮን ፈሣሽ ወንዝ፣ በጥቅል ኢትዮጵግዮን፤ የግዮን ወርቅ ስጦታ ተብሎ በሱባ ይተረጎማል.."/ "መፅሃፈ አብርሂት" በመሪ ራስ አማን በላይ/

"... ይች አገር በሠሜን ከግብፅ፣ በምዕራብ ከኒል አባይ፣ በምስራቅ ከዓረብ አገር፣ በደቡብ ከህንዳዊው ውቅያኖስ ትዋሠን ነበረች። ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ብዙ አመታት በፊት በዚች አገር የኩሽ ዘሮች የሚባሉ የካም ወገን የሆኑ ተወላጆች ይቀመጡባት ነበር። እነዚህ የኩሽ ዘሮች ባላገሮችና ዘላኖች ስለነበሩ የእነርሡ አኗኗርና ዋና ስራቸው ከብት ማርባት ብቻ ነበር።... የማዕድኖችን ስራ ገና አላወቁም ነበርና መሣሪያቸው ሁሉ ከድንጋይ አይነት የተሠራ ነበር። ቆይቶ ግን እየሠለጠኑ ከሄዱ በኋላ ይህንን ለመሣሪያቸው የሚሆነውን ድንጊያ መጥረብና ማለዘብ ጀመሩ።... እንዲህ ሆኖ ስራቸው እየተስፋፋ ከሄደ በኋላም የስልጣኔ ኑሯቸው ከፍ እያለና እየተራመደ ሄደ። ለኑሯቸው የሚጠቅሙ ማዕድኖችንም ማግኘት ጀመሩ። ለጊዜው ያገኟቸው ማዕድኖችም ነሃስና መዳብ፣ ብረት፣ ወርቅና ብር ይህን የመሣሰሉ ሌሎችም ማዕድኖች አግኝተው መስራት ጀምረዋል። እኒህ ማዕድኖች አልፎ አልፎ በሙሉ ኢትዮጵያ ይገኙ ነበር። በተለይ ግን በኦጋዴንና በሱማሌ አገር ይገኙ ነበር። እንዲሁም ማለት መጽሃፍ ቅዱስ /3 ዘነገስት ም 1 ቁ 11፣ 2ኛ ዜና መዋዕል ም9 ቁ 10/ በብዙ ስፍራ የኦፊር ወርቅ ብሎ በሚያነሣው በተለይ ይገኙ ነበር ማለት ነው።

ሠው በየጊዜውና በየዘመኑ እየተለዋወጠ መሄዱ የታወቀ ነው። እንኳን ሠው መሬት እንኳ በእሣተ ጎመራ ዋዕይ ምክንያት ተራራ የነበረው ሜዳ ፣ ሜዳ የነበረው ተራራ ሆኖ፤ ያ ሜዳ የነበረው ቦታ ገደልና ሸንተረር ስለተገኘበት የወርቅና የብር የነሃስና የመዳብ፣ የብረትም የሌላም ልዩ ልዩ ማዕድን መገኛ ሆኖ ይታያል......" / "የኢትዮጵያ ታሪክ" አባጋስፖሪኒ ገ/ም/

"..... ግብፃውያን ከ2500 አመት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረው ወርቅና ሌላ ክቡር እቃ ለመፈለግ በኒል አባይና



በአትባራ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ይገቡ ነበር ። እነሱ የመጡበት ዘመን ኦሪት ከመፃፉ በፊት ስለሆነ የአገሪቱን ስም ኩሽ ብለው ጠርተዋት ሄዱ። ኋላም ሙሴ በግብፅ በስደት አገሩ ያደገና የተማረ ስለሆነ ከግብፅ አገር ሊቃውንቶች የሠማውን የኩሽ አገር ብሎ ኢትዮጵያን በኦሪት መፅሃፍ ላይ ፃፉት።

ግብፃውያን ወርቁን እየቆፈሩ ወስደው እኩሌቶቹ በኒል አባይና በአትባራ፣ እኩሌቶች በቀይ ባህር አድርገው ወደ አገራቸው ተመልሠው ከኢትዮጵያ በወሠዱት ወርቅ የአምላኮቻቸውን የነገስታቶቻቸውን ምስሎች ይሠሩ ነበር። እስካሁን ድረስ በግብፅ የሚገኙት የቀድሞ ዘመን ምስሎች ብዙዎቹ ከኢትዮጵያ በወሠዱት ወርቅ የተሠሩ ምስሎች ናቸው። የቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያን (የኩሽ ዘሮች) ግብፃውያን ከአገራቸው እየተሠደዱ መጥተው በኢትዮጵያ ውስጥ ወርቅ የሚገኙባቸውን ቦታዎች እየፈለጉ በነቀምት፣በሌቃ፣በማጂ፣ በጉባ፣ በሸጎሌ እስከ ኦጋዴን ድረስ የሚገኘውን የወርቅ ማዕድን እየፈለጉ ቆፍረው መውሠዳቸውን ካዩ በኋላ የወርቅ ማዕድንን ጥቅም አወቁ። እንደዚሁም እየሠለጠኑ ከድንጋይ ዘመን ወደ ወርቅ ማዕድን ዘመን ደረሡ። ከዚህም በኋላ ጥቂት በጥቂት ወደ ነሃስና ወደ መዳብ ወደ ብረትም ዘመን ደረሡ። /"የኢትዮጵያ ታሪክ" አባ ጋስፖሪኒ ገ/ም/

"... አንዳንድ ታሪክ ፀሃፊዎች ኦሪ ወይም ኣራም የተባለው የአዳም ልጅ ዓለም በተፈጠረ በ970 ዓመት በኢትዮጵያ ነግሶ ነበርና የእርሡ ነገድ እስከ ጥፋት ውሃ (ማየ አይኅ) ድረስ 21 ነገስታት ነግሠው ኢትዮጵያን ገዝተዋል ብለው ፅፈዋል።"/"ዋዜማ" ብላቴንጌታ ህሩይ ወልደስላሴ/

"... የአዳም መኖሪያ የነበረችው ገነት በአርማንያ አገር አጠገብ ናት።.. የእነዚህም ያራቱ ወንዞች ምንጫቸው በአርማንያ አገር ካለው አራራት ከሚባለው ተራራ እንደሆነ በጂዎግራፊ መፅሃፍ የታወቀ ነውና ገነት በአርማንያ አገር አጠገብ መሆንዋን ያስረዳል።... ነገር ግን ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ከመርከብ ወጥቶ ምድርን ከሶስት ከፍሎ መካከሉን እስያን ለሴም፣ ግራውን አፍሪቃን ለካም፣ ቀኙን አውሮጳን ለያፌት አከፋፍሎ ሠጥቷቸው ነበርና በዚያ ዘመን ካም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ባይነግስና ባይገዛ እንኳ አፍሪካ የካም ክፍል ከሆነ ካም በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ቢባል ተቃዋሚ የለበትም።... ከጥፋት ውሃ አስቀድሞ የአዳም ልጅ ኦሪ፣ ከጥፋት ውሃም በኋላ የኖህ ልጅ ካም፣ በኢትዮጵያ ነግሠው ነበር ብለን ብንፅፍ አንባቢዎችና ታሪክ መርማሪዎች እውነት ብለው አይቀበሉንምና፤ የነገደ ኦሪንና የካምን መንግስት ታሪክ ትተን ከካም የልጅ

ልጅ ከሰብታህ ጀምረን በኢትዮጵያ የነገሡትን ነገስታት ስምና ቁጥር እንፅፋለን።"/ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ስላሴ "ዋዜማ"/

"... በመጀመሪያ ከዓለም ክፍል ሠው የነበረበት እስያ ነበር። ሁለተኛው አፍሪካ ነው፤ ከዚያ ቀጥሎ አውሮጳ፤ በመጨረሻ አሜሪካ ነው።... አዳምና ሄዋን በእስያ በዔድን (ገነት) ተክል መኻከል ተቀመጡ። ይህም ስፍራ በእስያ ምዕራብ ወገን ካለው ከኤፍራጠስ ወንዝ ሩቅ አልነበረም። ነገር ግን እግዚአብሔርን በድለው በሃጢያት ከወደቁ በኋላ ያንን ደስ የሚያሠኝ ስፍራ ለቀቁ። በዚች ሠፊ ዓለም ለጊዜው የነበሩባት ከሠው ወገን አዳምና ሄዋን ብቻ ነበሩ። ይህም ስለሆነ እግዚአብሔር አልተለያቸውም ነበርና ብቻኝነታቸው አይሠማቸውም ነበር። ወዲያው ልጆች እየተወለዱላቸው ዘራቸው እየተባዛ ሄደ። እነዚህም በኤፍራጠስ ዙሪያ ያለውን አገር ሁሉ መኖሪያቸው አደረጉት። በዚያም ከተሞችንና መንደሮችን ሠሩ። ነገር ግን ክፋታቸው እየበዛ ስለሄደ አምላካቸውን ማምለክ ረስተው ክፋትንና አውሬነትን ተከተሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ለማይታዘዙ እምቢተተኞች ቅጣት፤ ወደ ፊት ለሚመጡት ነገዶች ጥንቃቄ እንዲሆናቸው ብሎ ከኖኅና ከልጆቹ በቀር የሠውን ወገን ሁሉ ለማጥፋት ቁርጥ ሃሣብ አደረገ፡" ("የዓለም ታሪክ" አቶ ዮሃንስ ወልደማርያም")።

"... ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሩት ህዝብ አንቲዴሉቭያን ይባላሉ። ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሩ ማለት ነው። ስለእነርሡም በመፅሃፍ ቅዱስ ከተነገረው በቀር ሌላ አናውቅም። ምናልባት በእስያ ውስጥ በትንሽ ስፍራ ተበትነው ይሆናል እንጂ ከጥፋት ውሃ በፊት በአፍሪካ፤ በአውሮፓና በአሜሪካ ክፍ ምንም ሠው አልነበረበትም። የጥፋት ውሃ መዝነሙን በህዳር ጀምሮ በመጋቢት እንደቆመ ይታሠባል። ወዲያው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ውሃው እየጎደለ ሄደ። የኖኅም መርከብ በአርመን አገር በአንድ ረጅም ተራራ ጫፍ ላይ አረፈ። ይህም ተራራ አራራት ይባላል። እስከ ዛሬም ድረስ ይታያል።

... ምናልባት ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሩ ሠዎች (ሡበዓ ትካት) የሠፈሩት በዚህ በኤፍራጠስ ወንዝ ዳር ሣይሆን አይቀርም። የቀድሞ ወገኖች መጀመሪያ ነገድ የሆኑበት በዚህ ስፍራ ነው..." (አቶ ዮሃንስ ወ/ም "የዓለም ታሪክ")

"... ፈጣሪም በኖኅ መስዋዕት እጅግ ተደስቶ ለአዳምና ለሄዋን የነሣቸውን ምድር እንዲወርስ ስለወደደ "የሠው ልጆችን ከእንግዲህ አላጠፋም" ሲል ቃል ኪዳን ገብቶ ለቃሉ ማረጋገጫ በደመና ቀስቱን አኑሮ በማመልከት ወደ ግዮን ዘአበ ሜለክ መነሻ ባና ሃይቅ (አዳምና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት ተባረው ኢየሩሳሊም ከመኖራቸው ቀደም ብሎ ይኖሩበት



የነበረ ቦታ እንደሆነ ይታመናል።) እንዲሄድ አዘዘው። ኖኅም ሴምንና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ ወደ አፍሪካ ኢትዮጵያ ምድር መጣ።" ("የጎንደር ታሪክ" ያሬድ ግርማ ሃይሌ)

"... የካም ዘሮች ያልሠፈሩበት ቦታ አልነበረም። ሔሮዱተስ የግሪክ ቀደምት ነዋሪዎች የካም ዘሮች ነበሩ ብሏል። ("የኢትዮጵያ አንድነትና ኢጣሊያ" ዶ/ር ተወልደ ትኩእ)

"... አንዳንድ ስለሠ ው ዘር የሚያጠኑ ጠበብት የመጀመሪያው የሠው ዘር ብቅ ያለው በዓባይ፤ በኤፍራጠስና ጢግሮስ ወንዝ ሸለቆዎች ነው። ይላሉ። ሌሎች ደግሞ የሚያምኑት የመካከለኛው ምስራቅ የመጀመሪያዎቹ ሠፋሪዎች ከአባይ ሸለቆ በቀይ ባህር በኩል ወደ ሠሜን የፈለሡ ጥቁር ኑብያንስ ናቸው በማለ ነው። የሚመስለው ግን ህይወት በእነዚህ አካባቢዎች በተመሣሣይ ጊዜ ተከሠተና የመካከለኛው ምስራቅ የመሬት ሠላጤ የእነዚህ ሁሉ ህዝቦች መገናኛ ሆነች የሚለው ነው።... በዚህ በኤፍራጠስና ጢግሮስ ወንዝ ሸለቆዎች የመጀመሪያውን የሠው ልጅ ስልጣኔ ፈጠሩ..." (David Lamb "the Arbs" እ.ኤ.አ 1987)

"... ኢትዮጵያውያን ገነት የምትባለው የራሣቸው አገር የኒል ምንጭ መሆኗን አያምኑም። ይደነግጣሉና።... ደግሞም የሩቅ አገር ሠው ፅሁፍ ይጠብቃሉ። በዚያ ላይ ስለራሣቸው ማውራት አይወዱም። ሃጢያት ነው ይላሉ።... (Fredric T.Bolton "Plant and planiet" እ.ኤ.አ 1982)

"... በ9ነኛው መቶ ዓመት የነበረው ሆሜርና ይልቁንም በ6ኛው መቶ አመት የነበረው ሄሮዱት የፃፉት ነው። እነርሡም ከብዙዎቹ ውስጥ እንደዚህ ይላሉ። ኢትዮጵያውያን ታላላቆች መልካቸው ያማረ፤ የሠውነታቸው ቅርፅ ደንበኛ የሆነ ግድቆች፤ በጎ አድራጊዎች፤ ለስራ የማይደክሙ፤ ጥበበኞች፤ በሩቅ ስፍራ የሚኖሩ አማልክት የሚወዷቸው፤ ባንደበታቸው ሃሠት የማይገባ፤ በጦርነትና በእርጅና ካልሆነ በስተቀር በበሽታ የማይሞቱ ናቸው። ("የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ/ናፓታ መርዌ/ ተክለፃድቅ መኩሪያ)

ከላይ የተጠቃቀሡት ሐተታዎች ሁሉ ከተጠቀሡት መፃህፍት የወጡ ናቸው። በርካታ ፀሃፍት ስለዚች አገር ብዙ ብዙ ብለዋል። በመጨረሻ የሚደርሡበት ድምዳሜ ግን "ይች አገር ሚስጥር ናት" የሚል ነው።

ስለኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ ብዙዎች ብዙ ይበሉ እንጂ አንዱ ፅሁፍ ካንዱ ሲስማማ የምናየው በጣም በውስን ነጥቦች ብቻ ነው። በስም ቢስማሙ በዘመን ይጣረሣሉ። በነገድ ቢስማሙ በመቸት ይጣላሉ... ወዘተ።

ይህም ነው ትልቅ ችግር ፈጥሮ ሲያወዛግብ የኖረው። ስለኢትዮጵያ የተፃፉና በደንብ ተደራጅተው ያልተቀመጡ ሙሉዕነት ያላቸው መረጃዎች ካለመኖራቸው ጋር ተደማምሮ ሁኔታውን ከባድ አድርጎታል። ስለዚህ የጎደለውን ከመፅሃፍ ቅዱስ እየቆነጠርን ለመሙላት እንሞክራለን።

ምንም እንኳ ለታሪክ ዋቢነት ተብሎ ያልተፃፈ ቢሆንም በአግባቡና በጥቂቱ ብንጠቀምበት ተከፊ ወገን ሊኖር አይገባም። ይህም ሲባል በጥንቱ ታሪክ ላይ መሠረቱን እስክንይዝ ድረስ ባሉት ጥቂት ገፆች ላይ ነው። በተረፈ ከሌሎች አገራት ታሪክ ነገስት፣ ዜና መዋዕል፣ የሃውልት ላይ ፅሁፎች... ወዘተ.. ተነስተው የተፃፉትን እየመረጥን ትውፊታዊ መረጃዎችንም እያካተትን አንዱን ከአንዱ እያስማማን እንቀጥላለን። የአንዱን ዓረፍተነገር ከሌላው፤ የሌላውን ሐተታ ካንዱ አስማምተን እያዋሃድን፣ ያንዱን እያነሳን ያንዱን እየጣልን፣ መንፈሣዊውን ፅሁፍ ከአለማዊው እያጣመርን የሩቁን ዘመን ታሪክ እንረዳና ሁሉም የተስማሙበት ወጥ የሆነ ታሪክ የምናይበት ዘመን ላይ እንደርሣለን። ያን ካላደረግን ወደ እውነታው መድረስ ስለማንችል እንደማለት። ይህ በእንዲህ እንዳለም ከወዲሁ መነሳት ያለበት ጥያቄ አለ፤ ይኸውም ፦

1ኛው ገነት የት ነበረች? የሚለው ሲሆን፤ 2ኛው የኖኅ መርከብ የት አረፈች? የሚለው ነው። በተለይ በ2ኛው ጥያቄ ላይ ጥቂት ነጥቦችን ማንሳት የግድ ይሆናል።

ብዙዎች የውጭ አገር ጸሃፊዎች ገነትን አርማንያ ውስጥ ያደርጓታል። ሁሜ ያጡ የሚመስሉ ጥቂት የአገር ውስጥ ፀሃፍት ደግሞ ጣና ላይ ነው ይላሉ። እርግጥ ነው ከሁለቱ አገራት ውጪ እንዳልሆነች ግልጽ ነው።

ገሚሱ ዔድን ገነት ኢትዮጵያ መሆኗን እርግጠኛ ይሆንና፤ ነገሩ ሁሉ ምስቅልቅሉ በወጣ ጊዜ እነ ጢግሮስ ተቆርሠው ሽሹ ይላል። የቀረው በእሣተ ገሞራ ሣቢያ ነገሩ ሁሉ ተለዋወጠ እንጂ ገነትማ ኢትዮጵያ ለመሆኑ ምን ጥርጥር አለው? ይለናል። አንዳንዱ አዳም ገነትን ለቆ ተባሯል። ከተባረረ በኋላም ኢትዮጵያን ለቆ አምላክ ወዳዘጋጀለት ሌላ ስፍራ ተወስዷል። ስለዚህ በኋለኛው ዘመን የጥፋት ውሃ ሲከሠትና ኖኅ ዛድቅ ሆኖ ሲተርፍ ለአዳም የነሣውን ምድር ለኖኅ መልሶ አውርሶታል ይላል።

ትውፊቱማ ጉድ የሚያሠኝ ነው። "የምትገለባበጥ የነበልባል ሠይፍን በዔድን ገነት ምስራቅ አስቀመጠ.." የሚለውን ነገር በማመለከትማ አንዳንድ ትውፊታዊ መረጃዎች መነሻቸውን ጣና ያደርጉና "ምስራቅ" የሚለውን ወደ አፋር አካባቢ ያመላክቱና ኤርታሌን



ሲጠቁሙን የሚሞክሩ አሉ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የወርቁንና የማዕድኑን ጉዳይ እያመሣከሩ ይተነትኑልናል። ኤርታሌን ከጴደን ባህረ ሠላጤ ጋር እያስማሙ ሠይፉን ተክለው እያብለጨለጩ ያሣዩናል።

ምናልባት ከግማሽ በላይ የሆኑ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ሀሃፍት ገነት አርማንያ መሆኑን ይስማሙበታል። ከግማሽ በታች የሆኑት ደግሞ በኢትዮጵያ መሆኑን ያምናሉ። ዛሬ ድረስ በስፋት ተቀባይነት አግኝቶ ያለውም የአርማንያው ነው። ምክንያቱም ከኛ ቀድመው "ዘመናዊ" ትምህርት የተማሩት ነጮች ስለሆኑ በሚመቻቸው መንገድ ቀድመው ታሪኩን ሁሉ ወደራሣቸው ወስደው ስለጨረሡት ነው።

ከአገር ውስጡ የብራና ፅሁፍ ይልቅም የነጮችን መርጠው የሚቀበሉ ምሁራን ስለ ማበረከቱ ቀደምት አባቶች ቆዳ ፍቀው የፃፉት ተቀባይነት እያጣ ተረተረት እየተባለ እዚህ ተደርሷል።

ቀደም ሲል በብላቴን ጌታ ህሩይ ወ/ሴ "ዋዜማ" መፃህፍ ላይ አንድ አስገራሚ ሃተታ አይተናል። "... የአዳም ልጅ አሪ ከጥፋት ውሃ በፊት፣ የኖኅ ልጅ ካም ከጥፋት ውሃ በኋላ በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ብለን ብንፅፍ የሚያምነን አይኖርምና.." በሚል መነሻ "ትተነዋል" ብለውናል። እንጂ የተፃፈ ሠነድ አግኝተው ነበር። እንዲህ ነው እንግዲህ የኢትዮጵያ ታሪክ! እንደነግባለን፤ አይመስለንም፤ ሽምቅቅ እንላለን።

መረጃ፣ መረጃ፣ መረጃ ይባላል። መረጃውንማ ወስደውታል። ምንም የለንም'ኮ በዘረፋም፣ በጎብኝዎችም፣ በጦርነትም፣ በስጦታም አልቋል፡፡ እኛ ስለ ፅሁፍና ስለመፃህፍ ምንነት ከመረዳታችን በፊት ነው የወሠዱት። አሁንም ቢሆን እነሡ የፃፉትን ተቀብለው ከፃፉ የአገራችን ሊቃውንት እየቆረስን እንጂ ከየትም አናመጣም።

ጥንታዊውን የታሪክ ሠነድ ወሠዱትና አደራጅተው ፃፉት። አንዳንዱን መለሡት። የቀረውን አስቀሩት። እነ ተክለፃድቅ መኩሪያን የመሣሠሉ ሊቃውንት በዲፕሎማትነት ዘመናቸው በየአውሮፓ አገሩ ቤተመፃህፍት ተቀምጠው ያሉትን ከኢትዮጵያ የተወሠዱትን ፅሁፎች አስፈቅደው እየገቡ መርምረው ታሪክ ፃፉ። እነ አለቃ ታዬን የመሣሠሉ የቤተክህነት ቀደምት ሊቃውንት ደግሞ በምኒልክ ጊዜ ወደ ጀርመንና ወደ ሌሎች የአውሮፓ አገራት እየተጓዙ ግዕዝን አስተማሩ። እነሡ ያስተማሯቸው አውሮፓውያን ዛሬ ከፍተኛውን የግዕዝ ት/ት ለኢትዮጵያ ምሁራን... ያስተምራሉ። ከዚያም እነዚህኞቹ እነዚያኞቹ የፃፉትን ተረተረት ነው ይላሉ። እንዴት? ስንል "ዘመናዊ የአጠናን ዘዴን ያልተከተለ፣ እንዲሁ መረጃ አልባ የሆነ ፅሁፍ ነው" ይላሉ።... ታዲያ በዘመናዊው የአጠናን ዘዴ አጥኑና አስተምሩን እንጂ፤ አለበለዚያኮ በትውፊት ተታለን መቅረታችን ነው ከማለት ውጪ ምንም አይባልም።

ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ ብቻ ሳይሆን ወደ መላው ዓለም ሄደ። ሁሉንም አይነት ስልጣኔ ቀደምት ኢትዮጵያውያን አሳልፈው ሠጡ። ከዚያም ባዶአችውን ቀሩ። እንደገና ተመልሠው እስኪያሠለጥኗቸው መጠበቅ ግዴታ ነበር። መለማመጥንም ይጨምራል። የታሪክ ሠነድ ከኢትዮጵያ ተወስዶ በመላው ዓለም ተሠራጨ። ከዚያም ባዶዋችንን ቀረን። እንደገና መልሠው እስኪሠጡን መጠበቅ ግዴታችን ነበር። መለማመጥንም ይጨምራል።

"ቀደምት ነን" ስንል "ምን መረጃ አላችሁ"? ይሉናል። መረጃችን እንደወሠዱት ስለሚያውቁ አጠያየቃቸው ልበ ሙሉነት የሚንፀባረቅበት ነው። ጥቂት ነገር ቆንጥረው (እሡንም አዘባርቀው) ይሠጡንና ስንወዛገብ እንድንኖር ያደርጋሉ። እንዲህ ነው'ጂ መወዛገብ!

ወደ ዋናውና ወደ ሁለተኛው ነጥባችን እንለፍ፤ አንደኛው ጥያቄ ከሁለተኛው ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ስላለው አብረን ልናየው እንችላለን። ከጥፋት ውሃ በኋላ የኖኅ መርከብ የት አረፈች? ስንል፤ ታላቁ መፅሃፍ "በአራራት ተራሮች" ይለናል። ከዚህ ያለፈ ነገር አይነግረንም፤ መንገርም አይጠበቅበትም። ስለዚህ አራራት ተራራ የት ነው? ብለን ስንጠይቅ ነጮች "አርማንያ" ወይም ቱርክ ይላሉ። ከነጮች ተቀብለው የዓፉ ሀበሾችም አርማንያ ብለው መልሠው ይነግሩናል። የአገር ውስጥ ጥቂት ሊቃውንት ደግሞ "አራራት ተራራ ጣና ላይ ነው" ይሉናል። አሁንም በተመሣሣይ አራራት ተራራ የሚባሉ በሁለት የተለያዩ የዓለም አገሮች ይገኛል። በአርማንያ እና በኢትዮጵያ። አይገርምም?

"አራራት ተራራ በደቡባዊ ጣና ሃይቅ በዘጌ ባህረ ገብ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ከአንድ ሠዓት የእግር ጉዞ በኋላ የሚገኝ የአካባቢውን ዙሪያና የጣና ሃይቅን ለመመልከት የሚያስችል፤ ሲሆን በዙሪያው ላይ ይጋንዳ ተክለሃይማኖት በአድያም ሠገድ እያሡ የተተከለ፣ ቅድስት ስላሴና በተራራው ስር ኡራ ኪዳነምህረት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ" ይላል ያሬድ ግርማ ሃይሌ የተሻለ አማራጭ አቅርቦ ክፍት አድርጎት ሲያልፍ። በሌላ በኩል አራራት ተራራ በአርማንያ ውስጥ የሚገኝ የከፍታ መጠኑ 5165 ሜትር ሲሆን፤ በዓለም ካሉ ተራሮች 27ኛ ተራ ረድፍ ላይ ይገኛል። አርማንያ ቱርክ፣ ጆርጂያ፣ አዘርባጃንና፣ ኢራን የሚያዋስኗት እስያዊት አገር ናት።"

የኛው አራራት ተራራ አልተለካም። ያን ያህል ቁመትም የለውም። ከፍታ ደግሞ ምንን ይገልፃል? የኖኅ መርከብ ከሁለቱ አራራት ተራራዎች በአንደኛው አርፋለች። የብዙሃኑ ምልከታ በእስያው አራራት ተራራ አረፈች የሚል ነው። ይህም ሲሆን ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ሴምንና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጣ ልንል ነው።



መርከቧ ያረፈችው በዚህኛው አራራት ተራራ ከሆነ ደግሞ ሴምና ያፌት ከዚህ ተነስተው ሄደው በእስያና በአውሮፓ ሲስፋፉ፤ ካም እዚሁ ቀርቶ በአፍሪካ ተስፋፋ ልንል ነው። የዚህን ምርጫ ለአንባብያን ክፍት አድርጎ ማለፍ ይቻል ይሆናል። ምክንያቱም እርግጠኛ ሆኖ መናገር የማይቻለው የመርከቧን ማረፊያ ቦታ እንጂ ኖኅ ካምን ይዞ ለመምጣቱ ወይም በዚች ምድር ለመኖሩ በዋናው ታሪክ ውስጥ ስለምናገኘው በታሪካችን ላይ ተፅእኖ አይፈጥርም። የትኛው ተራራ ላይ አረፈች? እዚህ ወይስ እዚያ? የሚለውን "እዚህ ነው" ብዬ ድምዳሜ ከወዲሁ ደምድሙ ለማለት የሚያስችል ከትውፊት በስተቀር በቂ መረጃ ለጊዜው ስለሌለኝ ክፍት አድርጌው ልለፍ እንጂ ግላዊ እምነቴ አርማንያ አይደለም። ስለዚህ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል በሚለው ለጊዜው ተግባብተን እንቆይና የታሪኩ ሂደት በራሡ የበለጠ ወደ አንዱ ድምዳሜ ሊያደርሣችሁ ከቻለ አብረን እንይ። ካላደረሳችሁ ብቻዬን እደርሣለሁ ማለቴ ነው። ይህን ለማለት ያስፈለገው በአንዳንድ ፀሐፍትና አንባብያን ዘንድ ትውፊት ሲጣልና ሲናቅ ስለሚስተዋል ነው። ስለዚህ ትውፊትን በተመለከተ አንድ ነገር ላንሳ። ይህ መፅሃፍ ተፅፎ ከመጠናቀቁና ከመታተሙ በፊት "ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ዘመኖች ቆጠራ" በሚል ርዕስ ሠለሞን አበበ ቸኮል (ሰ.አ.ቸ) የዚህን መፅሃፍ አጠቃላይ ሁኔታ በሚመለከት መጠነኛ ዳሠሳ ቢጤ እያደረገ ለጥቂት ሣምንታት ከህዳር 19 2002 ዓ.ም ጀምሮ በጋዜጣ አስነብቦ ነበር። እናም ትውፊትን በተመለከተ ካሠፈረው ፅሁፍ ጥቂት ዓረፍተነገሮችን ቆንጥሬ ላስፍር። እርሡ እንዲህ አለ፦

"... ለብዙዎች ትውፊት ማለት እውነት ያልሆነ ነገር ይመስላቸዋል። ትውፊት ማለት በውርስ የተገኘ በቅብብሎሽ የመጣ፣ የወረደ ማለት እንጂ ውሸት ወይም ተረተረት አይነት ማለት አይደለም። በትውፊት የተገኘ ታሪክን ሣይንስ በገዛ ራሡ መንገድ ለመከተትና ለማውጣት እስካልቻለ ድረስ ለዘመናት የኖረ ማህበረሠቡና ሃገር የኖረበትን ማንነቱን መግለጫነታቸውን ማስተሃቀር ትልቅ ውድቀት እና ጥፋት መፈፀም እንደሚሆን ከኛው ወዲያ ጥሩ አስረጅ ማቅረብ አይቻልም። ይህም ቢሆን ሊታወቅ የሚቻለው ኖኅን ከመሠሉ የሥው ልጅ የጋራ ቤቶችና አባቶች ከነበሩበት ጀምሮ ታሪክን በዘመን መንገድ ላይ እያሽከረከሩ ያመጡት እንደሆነ ነው...።" ስለዚህ ትውፊት መጣል፣ መናቅ የለበትም። በዚህም ልንግባባ ይገባል።

ትውፊት ከተባለውም በላይ ነው። በትውፊት ያልታገዘ ጥንተ ታሪክ አለ ብሎ ለማለት አይቻልም። ታሪክን ጠብቆ የማቆያ አንድ መንገድ ነው። ስለ ትውፊት እንዲህ ሲባል መነሻና መድረሻችን ትውፊት

ነው ማለት አይደለም። ትውፊትን መጣል ተገቢ አለመሆኑን ለመግለፅ እንጂ።

እኔ እንዲህ እላለሁ፦ የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻ አጼ ቴዎድሮስ ቢሆን ኖሮ ከቴዎድሮስ እጀምር ነበር። ሌላ ንጉስም ቢሆን ከሌላ እነሣ ነበር። ያሉትን አነስተኛ የኢትዮጵያ የታሪክ ሠነዶች ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ታሪክ ከስር ጀምሮ ለመፃፍ የተነሣ ፀሃፊ የግድ መነሻውን ይመረምራል። ፍለጋውን ሲጨርስ መነሻ ብሎ ከወሠነው ቦታ ጊዜና ንጉስ ጀምሮ ይፅፋል። ከቴዎድሮስ ከሆነ ከቴዎድሮስ፣ ከኖኅ ከሆነ ከኖኅ ይጀምራል። ከመሃል እስካልጀመረ ድረስ። ባጠቃላይ ኖኅን መነሻ ያደረግሁት ታሪኩ አስገድዶኝ እንጂ፣ ኖኅ ከጥፋት ውሃ የተረፈ የመጀመሪያው ግንድ ስለሆነ አይደለም ወደ ኢትዮጵያ ያመጣሁት። መነሻ እንዳደርገው ያስገደደኝ ታሪክም እኔን ብቻ ሣይሆን ሌሎች ቀደምት ፀሃፍትንም ያስገደደ ነውና በምናየው መልኩ በመጠቃቀስ ኖኅን መነሻ አድርጌያለሁ።

በዚህ መሰረት ከአዳም ጀምሮ 10 ትውልድ ወይም የዘር ግንድ ይቆጠራል። አዳም፣ ሴት፣ ሄኖስ፣ ቃይናን፣ መላልኤል፣ ያሬድ፣ ሔኖክ፣ ማቱሳላ ላሜህ፣ ኖኅ ተብለው ይቆጠራሉ። በኖኅ ዘመን የጥፋት ውሃ ይሆንና ኖኅና ቤተሠቦች ብቻ ይተርፋሉ። ከዚያም ከጥፋት ውሃ ከተረፈው ከኖኅና ከቤተሠቦቹ ጀምሮ "አዲስ" የዓለምና የህዝቦቿ የታሪክ ምዕራፍ ይከፈታል። ወይም ሁሉም የሠው ልጆች በጥፋት ውሃ ጠፍተው ኖኅና ቤተሠቦቹ ከተረፉ በኋላ በእነርሡ አማካኝነት ዓለም በሠው ልጆች ተሞልታለች። በዚህ ብንግባባ ምርጫዬ ነው። በዚህ ካልተግባባን በሙሉው መፅሃፍም ስለማንግባባ፣ ከዚህ እምነት ውጪ የሆነ አንባቢ ካለ ከወዲ[illegible] [illegible]ን እንዲያቋርጥልኝ በትህትና "ዝቅ" ብዬ ሣይሆን "ቀና" ብዬ እ[illegible]

[illegible]



## ምዕራፍ ፩
## ኖኅ እና ኢትዮጵያ

ኖኅ የ500 አመት እድሜ ላይ እያለ ነበር ሴምን፣ ካምንና፣ ያፌትን የወለደው። በኖኅ የህይወት ዘመን የሠው ልጆች በክፋ ስራቸው አማካኝነት አምላካቸውን በእጅጉ ሲያስከፉት ከምድረ ገፅ ሊያጠፋቸው ተገደደ። ነገር ግን ኖኅ ፍፁም ጥሩ ሠው ሆኖ ተገኝቶ ነበርና ከጥፋት ውሃ ይድን ዘንድ የፈጣሪ መልካም ፈቃድ ሆኖ መርከብ እንዲሠራ ታዘዘ።

መርከቧም 300 ክንድ ርዝመት፣ 50 ክንድ ወርድና፣ 30 ክንድ ከፍታ ያላት ሆና፣ በሮች እና መስኮቶች ያሏት ባለ 3 ደርብ የነበረች ስትሆን፣ ኖኅ ሚስቱን፣ ልጆቹንና የልጆቹን ሚስቶች እንዲሁም ከሁሉም አይነት ጥንድ ጥንድ እንስሣትን ይዞ በመርከቧ ተጠለለ።

ከዚህ በኋላ የምድር ቀላያት ፈንድተው፣ የሠማይ መስኮቶች ተከፍተው ለ40 ቀንና ለ40 ሌሊት በወረደ ውሃ ምድር ስትጥለቀለቅና ፍጥረቶች ሁሉ ሲጠፉ፣ የኖኅ መርከብ ወዲያ ወዲህ እያለች ስትንሣፈፍ ቆይታ ውሐው ሁሉን አጥፍቶ ሲጨርስ ከምድር ላይ እየነጠፈ በመሔዱ መርከቧ "አራራት" በተባለ ተራራ ላይ አረፈች። ኖኅና ባለቤቱ እሜቴ አይከል፣ እንዲሁም ሦስቱ ልጆቹ ሴም፣ካም፣ ያፌት ከነሚስቶቻቸው እንስሶችን ጨምሮ ከመርከቧ ወጡ። ኖኅ ከነቤተሠቦቹ በመትረፉ እጅግ ተደስቶ ለአምላኩ ምስጋናና መስዋዕት አቀረበ። ፈጣሪም በኖኅ መስዋዕት ደስ ተሠኘ።

ከዚህ የጥፋት ውሃ በኋላም አምላክ በድጋሚ የጥፋት ውሃ የሠው ልጆችን ላለማጥፋት ወሠነ። ለዚህም ቃል ኪዳኑን በሠማይ ላይ የደመናውን ሁብረ ቀስት ዘረጋ። ማለትም በእርሡና በሠው ልጆች መካከል ስላደረገው የምህረት ቃል የቃል ኪዳን ምልክቱን በሠማይ ላይ አኖረ።

ከላይ የሠፈሩትን እውነታዎች ቅዱሣት መፃህፍት ሲያረጋግጧቸው የተለያዩ የአገራችን ፀሃፍት ደግሞ መፅሃፍ ቅዱሡንም፣ ትውፊቱንም፣ በተለያዩ ጊዜያቶች የተገኙ ታሪካዊ ሠነዶችንና በዙሪያችን ያሉትን ማህበረሠቦች፣ ቋንቋ፣ ባህል እምነት፣ እንዲሁም ዛሬ ድረስ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን መሠረት በማድረግ ሁሉም የየበኩላቸውን እያሉ በመቀጠል የኖኅን ጉዳይ ዳር ያደርሡታል።

እነዚህን ነጥቦች በውል እሠናስለን ስንቀጥልም ነው የታሪካችን መነሻ መንገድ ለይተን የምናውቀው። "የቃል ኪዳን ምልክቱን በሠማይ ላይ አኖረ" ይላል ቅዱስ መፅሃፉ። ያሬድ ግርማ ሃይሌ "የጎንደር ታሪክ" ብሎ በሠየመውና በ1999 ዓ.ም ባሣተመው መፅሀፉ ደግሞ ሌሎች ዋቢዎችን ጠቅሶ ይቀጥለዋል።

" ኖኅ ከነቤተሠቦቹ በመትረፉ ተደስቶ ለፈጣሪው መስዋዕት አቀረበ። ፈጣሪም በኖኅ መስዋዕት ተደስቶ ለአዳምና ለሔዋን የነሣቸውን ምድር

እንዲወርስ ወደደ። "የሀው ልጆችን ከእንግዲህ አላጠፋም" የሚል ቃል ኪዳኑን ገብቶ ለቃሉ ማረጋገጫ በደመና ቀስቱን አኑሮ በማመልከት ወደ ግዮን መንሻ " አበሜሌክ" ማለትም ጣና ሐይቅ አዳምና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት ተባርረው እየሩሣሌም ከመኖራቸው ቀደም ብሎ ይኖሩበት እንደነበር በሚታመነው ቦታ እንዲሔድ አዘዘው። ኖኅም ሴምንና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ /አፍሪካ/ መጣ።" ይላል።

ኖኅ በመፅሃፍ ቅዱሱ መረጃ መሠረት ሶስት ልጆቹን ሲወልድ እድሜው 500 ዓመት የነበረ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ ምድር በጥፋት ውሃ ስትጥለቀለቅ ደግሞ ኖኅ እድሜው 600 ሞልቶ ነበር። በዚህ መሠረት በ"መግቢያችን" ላይ እንዳየነው የሠው ልጅ ታሪክ 5500 ዓመት ተብሎ የተወሠነው ከአዳም ጀምሮ ነው። በ"መግባቢያችን" ላይ እንዳየነውም ከአዳም እስከ ኖኅ 10 ትውልድ ይቆጠራል ብለናል። 9ኛው ላሜህ ነው። ስለዚህ ከአዳም እስከ ላሜህ ድረስ 1656 አመታት አልፈዋል። ከዚህ ውስጥም ኖኅ ከጥፋት ውሃ ሲተርፍ 600 አመት ሞልቶታልና ህይወት እንደ አዲስ የቀጠለው ከ3844 ቅ.ል.ክ. ጀምሮ ነው።

ኖኅ የመርከብ ስራውን ለማጠናቀቅ 100 አመት ፈጅቶበታል። (120 አመት የሚያደርሡትም አሉ) ሶስቱ ልጆቹ የተወለዱት ከጥፋት ውሃ በፊት ኖኅ የ500 አመት ጎልማሣ በነበረበት ጊዜ ስለሆነና፤ "የልጆቹ ሚስቶችም አብረው ወደ መርከብ ገቡ" ስለተባለ ለአቅመ አዳም የደረሡ ልጆች እንደነበሩ እንረዳለን።

ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ባለቤቱ፤ እንዲሁም ሶስቱ ልጆቹ ከነሚስቶቻቸው ከመርከብ ሲወጡ ሴም የ130 አመት ጉብል ወጣት ነበር። ጠይም ልጁ ካም የ120 አመት ልጅ እግር ነበር። ትንሹ ልጁ ያፌት የ100 አመት እምቦቀቅላ እንደነበር ይታመናል። ኖኅ ከ3844 ቅ.ል.ክ እስከ 3500 ቅ.ል.ክ ድረስ ለ350 አመታት ያህል የቤተሠቡ አለቃ ሆኖ ኖረ። መተዳደሪያውም ግብርና ነበር።

ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ቤተሠቦቹ ምድርን ይሞሏት ዘንድ ፈጣሪ ሲፈቅድም ሴምና ያፌት ሁለት እህትሮችን ይዘው ሲባሉ፤ ኖኅ ባለቤቱንና አንድ ልጁን ካምን ይዞ እንደመጣ ነው የሚታመነው። ይህም ሲባል "መርከቧ እዚያኛው አራራት ተራራ አረፈች" ብለው በሚያምኑ ፀሃፍት ዘንድ ሲታሠብ ነው። ወደፊት ባሉ ተከታታይ ምዕራፎች አንድ ድምዳሜ ላይ እስክንደርስ ይህንኑ እምነት ይዘን እንቀጥላለን። ምክንያቱም ኖኅ ካምን ይዞ ወደዚህ ሊመጣ የሚችለው መርከቧ በእስያው አራራት ተራራ ካረፈች ነው። በኢትዮጵያው አራራት ተራራ ካረፈች ግን ሴምና ያፌት ከዚህ ተመርቀው ተሸኝተው ካምና ኖኅ እዚህ ሲቀሩ ልናይ በለምንችል ነው። ለማንኛውም ግን ለጊዜው ሴምና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ መጣ የሚለውን ይዘን እንንጓዝ።



ኖኅ በዚች አገር እየኖረ ሣለ ባለቤቱ እሜቴ አይክል ሞቱበት። የሞቱትም ከጎንደር በስተምዕራብ በኩል በምትገኘውና ከከተማው 37 ኪ..ሜ ርቀት ላይ ባለችው "ጭልጋ" ተብላ በምትጠራው ምድር ነበር።

ጭልጋ ውስጥ እሜቴ አይክል የተቀበሩበት መቃብር እንደሆነ በሚታወቀው ቦታ ላይም ትልቅ ዛፍ በቅሎበት እስከ ዛሬ ድረስ የ"ቅማንት" ብሔረሠቦች ፀሎታቸውን ያደርሡበታል። የመቃብራቸው ሃውልትም ዛሬ ድረስ ጭልጋ/አይክል/ ውስጥ ይገኛል።

በዚህ ታሪክ መነሻነትም የጭልጋ ዋና ከተማ በስማቸው "አይክል" ተብሎ እንደተሠየመ ዛሬ ድረስ ይጠራል። አቶ ዮሃንስ ወልደማርያም "የዓለም ታሪክ" በተሠኘውና በ1936 ዓ.ም በታተመው መፃህፋቸው " በኢትዮጵያ 25 የካም ልጆች (ነገዶች) ተከታትለው መንገሣቸውን ይገልፁና "የቅማንት ብሔረሠብ ምንጭም ከካም መውረዱንና ተወራርሶ መቆየቱን፤ ቅማንት የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ "ክም" "ሸንት" ማለትም "አንተ ካም" ከሚለው የመጣ እንደሆነ" ይገልፃሉ።

በመሆኑም እነዚህ በጭልጋ /በአይክል/ እና በዙሪያው የሚኖሩ ህዝቦች የካምን ባህል፣ እምነት፣ ቋንቋ... ወዘተ.. ሳይበርዙና ሣይከልሡ ይዘው ይገኛሉ። የሠነበት ቀናቸውም ቅዳሜ ነው።

ወደ ኖኅ ታሪክ ስንመለስና ቀደም ሲል የጠቀስው "የጎንደር ታሪክ" የሚለው መፅሃፍ ደግሞ እንዲህ ይለናል "ኖኅ ባለቤቱ ከሞተችና ከቀበራት በኋላ የቀረችውን ጥቂት ዘመን ኖሮ (እንደሡ አገላለፅ በ850 አመቱ፣ እንደዚህ መፅሃፍ በ950 አመቱ) በአሁኗ የጎንደር ከተማ ሲሞት በመቃብሩ ላይ ምንጭ ፈልቆ በርካታ ሠዎችን ይፈውስ ነበር። ከዚያም ለኖኅ መታሠቢያ ይሆን ዘንድ አምላክ በቤተመንግስት አካባ የኖኅ የመቃብር ሃውልት እንዲታነፅ ፈቀደ። ይህም በኋለኛው ዘመን በንጉሥ ፋሲለደስ የታነፀው የፋሲል ግንብ ነው።" (የፋሲል ግንብን ታዓምራዊ አሠራር ዘመኑ ላይ ስንደርስ እናየዋለን)

ኖኅ ከ3844-3500 ቅ.ል.ክ ለ350 አመታታ ቤተሠቡን ሲመራ፤ በተመሣሣይ አገላለፅ ኢትዮጵያን ሲያስተዳድር ኖሮ ሲሞትም ልጁ ካም ተተክቶ ቤተሠቡንና አገሩን መምራት፣ መግዛት ቀጠለ።

የኖኅ ልጅ ካም ከ3500 ቅ.ል.ክ ጀምሮ ሲያስተዳድር ቆይቶ ሲሞት ልጁ ኩሽ ተተክቶ ከ2787-2545 ቅ.ል.ክ ድረስ የማስተዳደር ተግባሩን ተወጥቷል። ከኖኅ ሶስት ልጆች አንዱ የሆነው የካም ነገድ በአፍሪካ ምድር እየተባዛና እየተስፋፋ ሄዷል።

"ኖኅ"ሲባል የቃል ኪዳኑ ምልክት አብሮ ይነሣል። "የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ" የሚል ርዕስ ያለውና በመሪ ራስ ኤ.ኤም በላይ በ1986 ዓ.ም የተፃፈው መፅሃፍ ውስጥ እንዲህ የሚል ነገር የተካተተ ሲሆን፤ የቃል ኪዳኑንና የቀስተደመናውን ሁኔታ ከሠንደቅ ዓላማችን ጋር አመሣክሮ ከማስረዳት ጎን ለጎን እነ ኖኅ ስለ ፈገጡት ምድርና ስለጠጡት

ውሃ… ወዘተ የማስረዳት ብቃት ስላለው እንጠቀምበታለን፡፡ ሀሳፊው በደርግ ዘመን በጥንቷ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በ"ደንጎላ" በድንጋይ ሣጥን ውስጥ የተቀመጠና በኋለኛው ዘመን በ"ሱባ" ቋንቋ የተፃፈ ሰነድ አግኝተው ወደ አሜሪካ ወስደው እየዘገኑ በመተርጎም ከ6 በላይ ትልልቅ መፃህፍት ሊፅፉ የቻሉ ናቸው፡፡ እናም ከጉዳያችን ጋር የሚሄደውን መርጠን ስናይ፡-

"በ4000 ዓ.ዓ የኢትዮጵያን ግዛቶችና አፍሪካን በሙሉ እስያን ጨምሮ ይገዛ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ይገዛቸው ለነበሩ ህዝቦችና አገሮች ሁሉ መተዳደሪያ የሚሆናቸው ህግ ደንግጎ በሶስት ክፍል የተከፈሉና ሃያ ስምንት አንቀፆች ያሉት አዋጅ አውጥቶ በብራና ላይ በ"ሱባ" ቋንቋ ፊደል አፅፎ ለሁሉም እንዲታደል አድርጓል፡፡

በዚህ አዋጅ በአዋጁ ሶስተኛ ክፍል ስለሠንደቅ ዓላማ የተደነገገው እንዲህ ይላል፡፡

አንቀፅ 22 "ህያው አምላካችን ለአባታችን ለኖኅና ለልጆቹ፣ለኛ፣ እንዲሁም ለፍጥረቶች ሁሉ እንዲህ አለ፡፡ "በእኔና በእናንተ መካከል ለዘላለም የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው፡፡ ቀስቴን በደመና አድርጌያለሁ፡፡ የቃል ኪዳኑም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል፡፡ ከምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ በደመና ትታያለች" እኔም ዛሬ በህያው አምላኬ ፈቃድ፣ በአባቶቼ ዙፋን፣ በረገጡዋት ምድር፣ ባረፉባት መሬት፣ በቀመሁትና በተጠቀሙበት ውሐ ድንበር ሆኘ ይህን ለዘላለም የሚሆን በህዝብና በመንግስት መካከል ያለውን የፍቅር ምልክት ዓላማ በከፍታ ቦታ ላይ ሠቅዬ አውለበልብላችኋለሁ፡፡ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ሠማያዊ ቀለም መሆኑ፤ አረንጓዴው ምድራዊ፣ ቢጫው የፍቅር አበባ፣ ሠማያዊው ደግሞ የሠማያውያን መንፈሣዊ አካል እንዳለን የመግለፅ ምልክት ነው፡፡ ይህን ዓላማ አይቶም ሆነ ሠምቶ ያላከበረና ያላመነን ባሪያ ሆኖ እንዲኖር በህግ ተደንግጓል፡፡

አንቀፅ 23 "ማንኛውም ንጉሠነገስቱን የሚገልፅ ሠንደቅ ዓላማ በፊቱም ሆነ በኋላው ሊሠቅል ይችላል፡፡ ነገር ግን ከማድረጉ በፊት ለንጉሠ ነገስቱ ቀለሙን ማሳየትና ማስመረጥ አለበት፡፡ ይህን ሣያሣውቅ ቢሠቅል ከመንግስቱ እንዲወርድ ማድረግ፤ ባይወርድ እንዲገደል በህጋችሁ ተደንግጓል፡፡

አንቀፅ 24 "የአጼው/የንጉሡ/ የሠላም ሠራዊትና የጦር ሠራዊት ዓላማ ከንጉሠ ነገስቱ በታች ስንት ንጉሶች እንዳሉት የሚገልፅ የተሸነሸነ ዓላማ በፊትና በኋላቸው አስይዘው እንዲሄዱ በህጋችሁ ተደንግጓል፡፡

አንቀፅ 25 "በሠንደቅ ዓላማው አምድ ላይ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሃስም የተሠራ የኮከብ ቅርፅ ማስቀመጥ አለበት፡፡ ይህንን ሳያደርግ ሠንደቅ ዓላማ የሠቀለ በአደባባይ እንዲሠቀል በህግ ተደንግጓል፡፡"የሚሉት ይገኛሉ፡፡

ኖኅን በሚመለከት ቋንቋን፣ ባህልን፣ ብሔረሠብን፣ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ በፅሁፍ የተገኙ ሠነዶችን፣ ትውፊታዊ መረጃዎችን… መሠረት



ባደረገ መነሻ ይሄን ያህል ተንደርድረናል፡፡ "አይበቃም" ካልን ወደ ራሣችን ተጨማሪ ጥረት እንሄድና የማይገናኙ የማይተዋወቁ የሚመስሉ፤ ነገር ግን ተስማሚ የሆኑ ዓለማዊና መንፈሣዊ ፅሁፎችን አገጣጥመን አጠንክረነው እናልፋለን፡፡

ኖኅ የመርከብ ስራውን ካጠናቀቀ በኋላ ከፈጣሪው ዝርዝርና ሠፋ ያሉ ትዕዛዞች ደርሠውታል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም "… ከንፁህ እንስሳት ሠባት ሠባት ተባትና እንስት፣ ንፁህ ካልሆን እንስሳም ሁለት ሁለት ተባትና እንስት፣ ከሠማይ ወፍ ደግሞ ሠባት ሠባት ተባትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ ለዘር ይቀር ዘንድ ለአንተ ትወስዳለህ.." (ዘፍጥረት ምዕ. 7 ከቁ 1-4) ይህ ሃተታ ሠፍሮ ሲገኝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ብሔረሠቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት ዋና የታሪክ ኤክስፐርት የሆኑት/የነበሩት/ የያኔው ዶ/ር የአሁኑ ፕ/ር ላጲሶ ጌድሌቦ "Ethiopia a credil of History" ብለው በሠየሙት ጥናታዊ መፃህፋቸው እንዳሠፈሩት… "በሌላው ዓለም" በየትኛውም ስፍራ ወይም "ምድር" በተባለችው ኘላኔት ላይ በየትኛውም ገርና አህጉር የማይገኙ ሠባት አጥቢ እንስሣት በኢትዮጵያ ምድር ይገኛሉ" ፡፡ በትክክል እንደዚያ ነው፡፡ አነዋሊያ፣ እነ ቀይ ቀበሮ፣ እነ ቆርኪ፤ እ ጭላዳ ዝንጀሮ.. እዚህ ናቸው፡፡ (… መቸም ዋሊያ ያንን የሚያክል ቀንድ ይዞ.. ቀይ ባህርን ዋኝቶ መሄድም፣ መምጣትም የሚከብደው ይመስላል፡፡ ሠው ይዟቸው መጣ እንዳይባል ጭላዳ ዝንጀሮ እየነዳ የሚመጣ ነገድ አይኖርም…) ሌሎች ከሀገር መውጣት የማይችሉ እንስሶችም የሚገኙት በዚች ምድር ነው፡፡ ይሄው የኘ/ር ላጲሶ የ1983 ዓ.ም ጥናት "ኢትዮጵያ 239 አይነት አጥቢ እንስሣትና 832 የወፍ ዝርያዎች ሲኖሯት፤ ከእነዚህ መካከል ሠባት አጥቢ እንስሣትና 24 ወፎች በኢትዮጵያ ምድር ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡" ይበል እንጂ ከዚያ ጊዜ በኋላ ደግሞ አዳዲስ እንስሶች፣ አእዋፋትና እፅዋት እየተገኙ ባሁኑ ሠዓት በአገር አቀፍ ስታትስቲክስ መረጃዎች መሠረት 31 ጡት አጥቢ የዱር እንስሣት በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ከእነዚህ ውስጥ 7ቱ በሠሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ከ24ቱ 13ቱ አእዋፍትም በዚያው የነዋሊያ መኖሪያ በሆነውና ከኢትዮጵያ 1ኛ ከአፍሪካ 4ተኛ ደረጃ ላይ በተቀመጠው የከፍታ መጠኑ 4620 ሜትር በሆነው በራስ ደጀን ተራራ ሠፍረው ይገኛሉ፡፡

ከሠሜን ተራሮች ውስጥ ከፍተኛው ተራራ የሆነውን ራስ ደጀንን ፀሃፍት ሲገልፁት "የተራሮች ራስ፣ ቁንጮ፣ የራሶች ደጀን፣ ጋሻ፣ በተፈጥሮ የታነፀ፣ ያለ፣ የነበረ፣ የሚኖር፣ ማንም የማይገስሠው የማይከልሠው፣ ህያው ሆኖ ፀንቶ የሚኖር" በማለት ነው፡፡

ምናለ የተራራው ስም አራራት ቢሆን ልንል አይገባም፡፡ የጣናው አራራት ተራራ በቂ ነው፡፡ ታላቁ መፅሃፍም ቢሆንኮ ውሃው ወደ ላይ 15 ክንድ ከፍ ከፍ አለ ተራሮችም ተሸፈኑ አለ እንጂ ሌላ አልወጣውም፡፡

ለማንኛውም ግን ሁኔታዎቹ ባየነው መልኩ በደንብ የሚገናኙ እንጂ እንዲሁ የሚታለፉ አይደሉም። እነዚህን የመሣሠሉ ነባራዊ ሁኔታዎችም ናቸው ይችን አገር "ሚስጥር" እያሠኟት ያሉት። ኖኅን የሙጥኝ ብለው የቀሩ እንስሶች ናቸው ከማለት ውጪ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

እኔና እናንተ ችግር የለብንም። ለየብቻቸው ምዕራፍ ተሠጥቷቸው ባጭር ባጭሩ የሠፈሩ ታሪኮች ከጥቂት ገፆች በኋላ ተለቃልቀው ወደ አንድ እቃ ሲገለበጡ የኖኅ መርከብ በየትኛው አራራት ተራራ እንዳረፈች ስለምንረዳ ግድ የለም። አሁንም ገና አልወሠንንም። ታሪኩ እስኪያስወስነን እንጠብቃለን። ነገር ግን የታሪክ ሽሚያ በባዕዳኑ ዘንድ (ሁሉንም አንልም በብዙዎች ዘንድ) በእጅጉ ይንሀባረቃል። የኖኅ መርከብ በእስያው አራራት ተራራ እንዳረፈች ለማሣመን ብዙ ተጥሯል። ዛሬ ድረስ "የመርከቧን ስብርባሪ አገኘን" የሚል ዜና ይደመጣል። ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ሲባል የኖረ ነው። ሁለተኛው ማስረጃቸው የተራራው ስም እና ከፍተኛነቱ ብቻ ነው። ሌላ ነገር ቆጥረው ሊያሣምኑን አይችሉም። እኛ ግን እየቆጠርን ያለነው የጣውላ እድሜ አይደለም። የእንጨት እድሜ አይደለም። የነበረን፣ ያለን፣ የሚኖርን ነገር ነው። ከኖኅ ታሪክ ጋር የሚገናኝ ሆኖ እነሡ ጋ ኖሮ እኛ ጋ የሌለ አንድም ነገር የለም። እኛ ጋ ያለ እነሡ ጋ የሌለ ካልሆነ በቀር። ዓለማችን ካየቻቸው ግዙፍ የታሪክ ሽሚያዎች ቁጥር አንዱም ይሄ ነው።

ከኖኅ ታሪክ ጋር በተያያዘ መንደርደሪያችን እንደቀጠለ ነው። በተንደረደርን ቁጥር እየገፈተርናቸው ብንቀጥል በጥላቻ ሊተረጎም አይገባም። መንገዳችንን እያስለቀቅን ነው። በእነርሡ ዘንድ የኖኅ መርከብ በጥቁሮች አገር አታርፍም፤ ልታርፍም አትችልም ተብሎ ይታሠባል። በእነሡ ዘንድ ጥቁር ምንጊዜም ጥቁር ነው። ጨለማ። የችግርና የሠቆቃ ምንጭ ብቻ ነው። የመልካም ታሪክ ባለቤት ሆኖ ሲያዩ አይናቸው ደም ይለብሣል። ከኖኅ ልጆች አንዱ የሆነው ካም ጠይም የቆዳ ቀለም እንደነበረው ግን ያምናሉ። ያም ቢሆን ጥቁር ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የምንም አይነት ነገር ባለቤት ቢሆን ምንም ሆኖ እንዲቀር ይፈልጋሉ። ነገሩን ሁሉ ከቀለም ጋር ያያይዙታል። ስለቀለም ካነሣን አይቀር እንዴት እንዳቀለሙን አይተን እንለፍ።

ስለ ኖኅ ታሪክ በሚተረክበት በቅዱስ መፅሃፉ በዘፍጥረት ምዕ5 ከቁ 8 ጀምሮ እስከ 11 "... ርግብንም ውሃው ከምድር ፊት ቀልሎ እንደ ሆነ እንድታይ ከእርሡ ዘንድ ሠደዳት። ነገር ግን ርግብ እግሯን የምታሣርፍበት ስፍራ አላገኘችም። ወደ እርሡም ወደ መርከብ ተመለሠች፤ ውሃ በምድር ላይ ሁሉ ስለነበር እጁን ዘረጋና ተቀበላት፤ ወደ እርሡም ወደ መርከብ ውስጥ አስገባት። ከዚያም በኋላ ደግሞ እስከ 7 ቀን ቆዬ፤ እርግብንም እንደገና ከመርከብ ሠደደ። እርግብም በማታ ጊዜ ወደ እርሡ ተመለሠች፤ በአፍዋም እነሆ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ ነበር"። ይላል።

ከዚህ ታሪክ ጋር በተያየዘ ነው እርግብ የሠላም ተምሣሌት የሆነችው፤ ይህንንም ይዘው እነ ፖብሎ ፒካሶ እርግብን አሣምረውና



የለመለመ የወይራ ቅጠል አስነክሰው በሙሣል የሠላም አርማነቷን አፀደቁ። ስለዚህ ቀደምት ሠዓሊያን በዚህ ታሪክ ያምናሉ ማለት ነው። ነገር ግን መሠሎቻቸው ቀደምት ሠዓሊያን እነ ሚካኤል አንጀሎን የመሣሠሉ ካለፉ ጥቂት ምዕተ አመታት ያለፏቸው እንጋፋ የቀለም ሠዎች የታላላቅ ነገስታትን ቤተ መንግስትና የየአገሩን ቤተመቅደስ በመንፈሣዊ ስዕሎች ሲያሽበርቁ የሌለን ነገር ፈጥረው ነጭን የፈጣሪና የመላዕክት አምሣያ ጥቁርን የሠይጣን አምሣያ፤ አድርገው ስለው አፀደቁ። "ሠይጣን በጨለማ ስለሚመላለስ፣ ፈጣሪ በብርሃን ስለሚመሠል ነው" ብለው ሊከራከሩ ሞከሩ። "ጨለማም ብርሃንም "ይሁን" ተብሎ የሆነ ነው። ሠይጣን በጭለማ ብቻ ሣይሆን በቀንም ይመላለሣል። አስተሣሠቡ ነው ጭለማ፣ ብለው ሞገቷቸው። "የተገፈፈው ክብሩ እንጂ መልኩ አይደለም፤ መልኩና ቀለሙ የያኔው ሣጥናኤል ይባል በነበረበት ዘመን የነበረው አይነት ነው" አሏቸው። "ስለዚህ የግድ ፊቱን በጥቁር ከመመሠል ለምን እንደማንኛውም አይነት መልክ ያለው አድርጋችሁ ስላችሁ ስታበቁ ያንኑ መልክ እንደያዘ በጭለማ ሲመላለስ አትስሉትም?" ተባሉ፤ በጥቂት ጥቁር ተሟጋቾች። አልቻሉም ወይም አልፈቀዱም። ስለዚህ ነጮች በምንም መልኩ ቢሆን ጥቁር የበላይ እንዲሆን አይፈልጉም። በስዕልም ቢሆን! ከጥንት ጀምሮ የነበረ ታሪክ ቢሆንም፤ በተለይ በመካከለኛው ዘመን ተባብሶ ቀጠለና ጥቁር ላይ በህብረት ተዘመተ። የምንም ነገር ምንጭም፣ ፍንጭም ሆኖ እንዳይታይና እንዳይገኝ በጣም ይጠነቀቃሉ። ከግራ ከቀኝ ታሪካችን ሲዘርፉ ኖረዋል። ከዚህ አንፃር የታሪክ ሽሚያው መሟሟቱና የኖኅን የመርከብ እንጨት መለቃቀማቸው ሊገርመን አይገባም ነው ጉዳዩ። እንጂ... ከሆነ ጁይውሠዱት።

"... በኖኅ እድሜ በስድስት መቶ አንድ አመት፣ በመጀመሪያው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ውሃው ከምድር ላይ ደረቀ። ኖኅም የመርከቢቱን ክዳን አነሣ። እነሆም ውሃው ከምድር ፊት እንደደረቀ አዬ።" ቁ 13

የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ወይም አዲስ አመት መነሻው ይሄ ነው። መድረሻውም ጭምር። "መድረሻው" ሲባል ቋሚነቱን ለማመልከት ነው። በሌሎች ጃንዋሪ 1 በኛ መስከረም አንድ መባሉና ይሄ የኋለኛው ዘመን የ7/8 አመት እንቅደም ግኝትን መሠረት አድርገን አይደለም ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር አላት የምንለው። ነገር ግን ዋናው ምንጩ ቅ.ል.ክ ከ3 ሺ. አመት በፊት በነበረው ጊዜ ዓለም ገና ከጨረቃ አቆጣጠር ሣይወጣ፣ ግብፃውያን የፀሃዩን አቆጣጠር ግኝት (365 ቱን) አገኙ ከመባሉ በፊት ኢትዮጵያውያኑ ይጠቀሙበት የነበረ ነው። ይህ አቆጣጠር ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ የሄደ መሆኑን ወደፊት እናያለን።

በእርግጥ የፀሃይ አቆጣጠር በዘመናዊ መንገድ ተሠልቶና ተከትቦ ለዓለም ይፋ የሆነው በግብፅ አማካይነት ነው። ኢትዮጵያውያኑ ግን በባህላዊ መንገድ ይጠቀሙበት ነበር። የተለየ ነገር የለውም፤ የፀሃይ አቆጣጠር ሲባል አመቱን በ4 በመክፈል ክረምት፣ በጋ፣ በልግ፣ ፀደይ ማለት ነው። እነ ኖኅ

ለግብርና ብቻ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ "… በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም፡፡" ይላል ዘፍ 8 ቁ 22፡፡ ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅ ለፈጣሪው መስዋት ሲያቀርብ ፈጣሪ ያለው ነው፡፡ ከዚህ ቃል በኋላ ነው ህይወት እንደ አዲስ የሚጀምረው፡፡ "በእጃችሁ ተሠጥተዋል.." ይባላሉ ኖኅና ልጆቹ" ሁሉንም ነገር፡፡ ከዚህ ቃል በኋላ ነው ኖኅ ገበሬ መሆን የጀመረው፡፡ ይህ ክፍልፋይ ነው ወደ ቁጥር ተለውጦ የምናየው፡፡ እናም የነ ኖኅ ማሪፊያ በነበረችው ቦታ የዘመን መቁጠሪያ ቢኖር ባይኖር ለውጥ አልነበረውም፡፡ የዓመት መቁጠሪያ ጫፉ የመጀመሪያው ዓመት፣ የመጀመሪያው ወር፣ የመጀመሪያው ቀን መስከረም አንድ ተጨብጧል፡፡ እሡ (ብራው) ከታወቀ ሁሉም ቀላል ነው፡፡ እሁኑን ጊዜ መሠረት ባደረገ መልኩ መቁጠር ነው፡፡ ማረስ፣ መዝራት፣ማጨድ፣ መከመር መውቃት ነው፡፡ መስከረም መግባቱን ለማወቅ ከዚህም በላይ ጥርት ያለ የማወቂያ መንገድ ነበራቸው፡፡ አሁንም አለ፡፡ መነሻውም መድረሻውም ለማለት የተደፈረው ከዚህ በመነሣት ሲሆን፤ እሡም አደይ አበባ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ የስነእፅዋት ተመራማሪዎች ሁሉ ያመኑበት እውነት፣ ግራ የተጋቡበት፣ ሊደብቁት የማይችሉት የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሚበቅለው የአደይ አበባ ዝርያ በየትኛውም የዓለም ክፍል አይበቅልም፡፡ በአየር ብክለት የተፈጥሮ ሚዛን እስካልተዛባ ድረስ አደይ አበባ ኢትዮጵያን ቀጥሯት አይጠፋም፡፡ ሠዓቱንም አያዛንፍም፡፡ እርግጥ ቀጠሮ ነው ያላቸው፡፡ የኢትዮጵያ ቀደምት ካላንደር ይሄ ነው፡፡ የራሷ የዘመን አቆጣጠር ይሄ ነው፡፡ ስሙም መስከረም ነው፡፡ መጀመሪያ ማለት ነው፡፡ መደቡ ነጭ በሆነ ወረቀት የተፃፈ የዘመን መቁጠሪያ አይደለም፡፡ መደቡ ቢጫ ነው፤ "የፍቅር አበባ" ይሏል ይሄ ነው፡፡

ይችን ሀገር በሚመለከት ከዚህም ያለፈ ብዙ ብዙ የሚባል ነገር አለ፡፡ እንደተባለውም ይሄን የመሣሠለው እውነታ ነው ኢትዮጵያን "ሚስጥር፣ እንቆቅልሽ፣ እረቂቂ አገር እያሰኛት ያለው፡፡ በርግጥም ያስብላል፡፡ ቢሆንም በየገጹ "ሚስጥር ናት" እያልን መቀጠል ይከብዳል፡፡ ጊዜውም ቦታውም አይኖረንም፡፡ ብዙ ሚስጥር ነዋ ያለው፡፡ ስለዚህ ልዩ አገር በመሆኗ ለመስማማት ያህል ከኖኅ ታሪክ ወጣ እንበልና ጥቂት ነገሮችን በዚህ ምዕራፍ ጠቀስ ጠቀስ አድርገን ወደነ ካም ኩሽ ዘመን እንሄዳለን፡፡

በፈጣሪ እጅ ተፅፎበት ለሙሴ የተሠጠው ፅላት እዚህ ነው፡፡ የኢየሱስ ግማደ መስቀል አንድ አካል እዚህ ነው፡፡ በአፍሪካ የመጀመሪያው መስጊድ እዚህ ነው፣ የመጀመሪያው መንፈሣዊ ዜማና ሽብሸባ የሄደው ከዚህ ነው፣ ነብዩ መሐመድ ወገኖቻቸውን የላኩባት አገር ናት፣ የራሷ ብቻ የሆነ ጤፍ የተባለ ምግብ የሚሆን ሠብል የሚበቅልባት፣ እንጀራ በወጥ የሚበላባት ልበል ይሆን?

እንደ ፕ/ር ላጺሶ ጥናት ኢትዮጵያ የግሏ ከሆኑ የተፈጥሮ ቅርሶቿ ውስጥ አፅም የማያበሠብሡ የአፈር አይነቶች፣ የተፈጥሮ ድልድዮች፣ 13ቱ



ፀሃያማ ወራት፣ ካመት አመት አረንጓዴ ለብሶ የሚታየው ልምላሜ፣ ጤናማ የአየር ጠባይና ፍቱን የተፈጥሮ ፍል ውሃዎች፣ ነፋሻማ ኮረብታዎቿ፣ አይን የሚማርኩና መንፈስን የሚመስጡ ሸለቆዎቿ ኢትዮጵያን የመልክዓ ምድር እንቆቅልሽ አድርገዋታል፡፡ ከራስ ደጀን ከፍተኛ ተራራ ጫፍ ጀምሮ ከባህር በታች እስከ ዳሎል የእሣተ ገሞራ አዘቅት መካከል የሚገኘው የመልክዓ ምድር ገፅታዎቿ "የአፍሪካ ቷቤት "(እኛ የዓለም እንላለን) ወይም የአፍሪካ ሲዊትዘርላንድ" አሠኝተዋታል፡፡ የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ሐይቆች የልዩ ልዩ አእዋፍና የዱር እንስሳት መናህሪያዎች ናቸው፡፡ የአፍሪካ ጣራ /roof of Africa/ በሚል ስም ያስጠራትና እንደሠንሠለት የተቆላለፉ የሠሜንና ባሌ ተራራዎች "የአፍሪካ የውሃ ምንጭ" ወይም "የምስራቅ አፍሪካ የገናም መጋቢ" እየተባለች በልምላሜ እንድትደነቅ አድርገዋታል፡፡

"የኢትዮጵያ ህዝብ አብይ መተዳደሪያ እርሻ ሲሆን በአፍሪካ አህጉር በቀንድ ከብት ብዛት ተወዳዳሪ የማይገኝለት ምናልባትም በሬ ጠምዶ የማረስን ስልት ለሌሎች ያስተዋዋቀ ቀዳሚ ህዝብ እንደሆነ ይታመናል፡፡… ለእርሻ ተስማሚ የሆነ ለም አፈር፣ ልዩ ልዩ አዝርዕትን ለማብቀል ምቹ የሆነ የአየር ፀባይ፡ የተለያዩ የከበሩ ማዕድናት የሚገኙባት ምድር ናት" ( ፕ/ር ላጵሶ 1983 ዓ.ም) ፡፡

ለማንኛውም የእሜቴ አይከል የመቃብር ሃውልት፣ በሰባ ቋንቋ ተፅፎ የተገኘው ዓዋጅና የአዋጁ ቃላቶች፣ የኖኅን ልጅ የካምን ባህል ይዘው በጭልጋ የሚኖሩ ብሔረሠቦች መኖር፣ በየታሪክ ነገስቱ የነገደ ካም ነገስታት ተዘርዝረው መገኘታቸው፣ በአፍሪካ ምድር ተስፋፍተው ዛሬ ድረስ እየኖሩ ያሉት ህዝቦች የካም ልጅ በሆነው በኩሽ መጠሪታቸው ወዘተ.. ግንቡ፣ እንስሶቹ አእዋፍቱ፣ እፅዋቱ፣ ሁሉም "ኖኅና ኢትዮጵያ" ያላቸውን ቁርኝት ከመግለፅ ባለፈ፤ ወደዚች ምድር ለመምጣቱ ጠቋሚ ወይም አረጋጋጭ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ፪

# የነገደ ካም ዘመነ መንግስት

# ከ3500-1985 ቅ.ል.ክ

ቀጥሎ የተዘረዘሩት ከኖህ በኋላ "የነገደ ካም ነገስታት" ተብለው የሚታወቁት ናቸው። በጣም ጥቂት ቀደምት ፀሃፍት ከኖህ ጀምረው ይዘረዝራሉ። ጥቂቶች ከካም ጀምረው ይዘረዝራሉ። ብዙዎች ከኩሽ ጀምረው ይዘረዝሯቸዋል። በጣም ብዙዎች ከሰብታህ ጀምረው ይዘረዝራሉ። ከዚያ ዝቅ የሚል የለም።

| ተ.ቁ | የንጉስታቱ ስም | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የነገሱበት ዘመን ከክ.ል.በፊት |
|---|---|---|---|
| 1 | ኖህ | 344 | 3844 - 3500 |
| 2 | ካም | - | 3500 - 2787 |
| 3 | ኩሽ | 242 | 2787 - 2545 |
| 4 | ሰብታ | 30 | 2545 - 2515 |
| 5 | ኤሌክትሮን | 30 | 2515 - 2485 |
| 6 | ነቢር | 30 | 2485 - 2455 |
| 7 | አሜን 1ኛ | 21 | 2455 - 2434 |
| 8 | ነህሴ (አቢስ) | 30 | 2434 - 2404 |
| 9 | ታርኬም | 29 | 2404 - 2375 |
| 10 | ሳባ 1ኛ(ሳባኖባ) | 30 | 2375 - 2345 |
| 11 | ሳፎሪድ | 30 | 2345 - 2315 |
| 12 | እስክንዲ | 25 | 2315 - 2290 |
| 13 | ሆህይ ሰጥአ | 35 | 2290 - 2255 |
| 14 | አህያጥ | 20 | 2255 - 2235 |
| 15 | አድጋስ | 30 | 2235 - 2205 |
| 16 | ባኬንደን መሊስ | 25 | 2205 - 2180 |
| 17 | ማንቱራይ ሐቃቤ | 35 | 2180 - 2145 |
| 18 | ራክሁ ድድሜ | 30 | 2145 - 2115 |
| 19 | ሶቢ | 30 | 2115 - 2085 |
| 20 | አዜጋን ፈርኦን | 30 | 2085 - 2055 |
| 21 | ሱስሐል አቶሳኔዝ | 20 | 2055 - 2035 |
| 22 | አሚን ዳዊዛ 2ኛ | 15 | 2035 - 2020 |
| 23 | ራሚን ፀሃቲ መስልኔ | 20 | 2020 - 2000 |
| 24 | ዋኔና | 3 ቀን | 2000 - 2000 |
| 25 | ጲኦሬ 1ኛ | 15 | 2000 - 1985 |

*ያሬድ ግርማ 1999 ዓ.ም*
*መኩሪያ 1965 ዓ.ም*
*ጌታ ህሩይ ወልደ ስላሴ*

ከኖህ በኋላ ያሉት ተከታታይ ነገስታት የነገደ ካም ነገስታት በሚል ስያሜያቸው እየተፈራረቁ እስከ ጲኦሬ 1ኛ ድረስ ቆይተዋል። ከነዚህ 25 ነገስታቶች የግዛት ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስም በርከት ያሉ አ[illegible] የነገስታቱ መቀመጫ ሆነው አገልግለዋል። ረጅም ዘመን ባስቆ[illegible] የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነገስታቱ መቀመጫ ወይም ዋና ከተማ የነበሩ ተብለው በውል የሚታወቁና ተደጋግመው የሚጠሩት ቦታዎች ጥቂት ይምሁሉ እንጂ በርከት አድርገን ስንዘረዝራቸው የሚከተሉትን ይመስላሉ።

ጎንደር/ጣና/ ማንኩሽ /ቤንሻንጉል ውስጥ/ ቱብ (ሳእላይ ግብፅ) ናፓታ፣ ደንጎላ (በናፓታና በመርዌ መካከል) የሳባ ከተማ፣ መርዌ፣ አትባራ (አልፋ ገዳማ) አፈረዋ ናት (ወንድ በሽር ጣና) ኤለፋንተን (ደቡባዊ ግብፅ) መረብ (ከሰንዓ በስተምዕራብ) ዛፋር (ደቡባዊ ኢራቅ) መቋድሾ፣ ዳጋ እስጢፋኖስ (ጣና) የሃ፣ ሃውዜን፣ መጠራ፣ ከስከስ፣ አዶሊስ፣ ግሎማክዳ (ተሆንዶ ዛልአንበሳ) አክሱም፣ አክሱምና ጎሃፅዮን በጥምረት፣ አክሱም፣ ስቅንቅን፣ አክሱም፣ ሮሐ (ላስታ) ተጉለት፣ ደብረ ብርሃን፣ ሐረር፣ የረር፣ እንፍራዝ፣ ጎርጎራ፣ ጎመንጌ አዘዞ፣ ጎንደር፣ ደብረታቦር፣ መቅደላ፣ ላስታ፣ መቀሌ፣ እንጦጦ፣ (አዲስ አበባ) ተብለው ሲዘረዘሩ፣ እነዚህ ሁሉ ቦታዎች በተለያየ ዘመን የነገስታት መቀመጫ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፣ በዚህም የጥንቱን የኢትዮጵያ ግዛት ስፋት መረዳት እንችላለን።

ሁሉም ነገስታት በመረጡትና አመች በመሰለው ቦታ መቀመጫውን ሲያደርጉም የየራሱ መነሻ ምክንያት ይኖረዋል።

ለምሳሌ ኖኅ በኢትዮጵያ ምድር ቆይቶ ሲሞትና ልጁ ካም ተተክቶ ሲመራ ኖሮ ከሞተ በኋላ ልጁ ኩሽ ተተክቷል። የኩሽ ልጅ ሠብታህ ደግሞ በአባቶቹ ምድር በኢትዮጵያ ንጉስ ሆኖ ከ 2545-2515 ቅ.ል.ክ. ኢትዮጵያን አስተዳድሯል።

"ንጉስ ሰብታህ አጠቃላይ የሚገዛውን ምድር እየተዟዟረ እየጎበኘ በነበረበት ጊዜ የዓባይን ወንዝ ሲቃኝ ጉዞውን ወደ ወንዙ መነሻ ያደርጋል። ከምንጩ እንደደረሠም በአንድ ኮረብታ ላይ ድንኳን አስተክሎ አካባቢውን ሲቃኝ የአካባቢው የተፈጥሮ ውበት እጅግ አስደነቀው። ይህም 32 የተለያዩ ወንዞች የሚገብሩለት የጣና ሃይቅ ለንሮው ተስማሚ እንደሚሆን በመገንዘብ በጉብታው ላይ ካለው አፈረዋናት ከተባለው ቦታ ላይ ሐይቁንና ወንዙን ሲመለከት እጅግ በመማረኩ በዚያው ቦታ 9 በሮች የነበሩት ታላቅ ግንብ አስገንብቶ "ወንድ በሽር" ብሎ ሠየመው" ( ያሬድ ግርማ 1999 ዓ.ም)

ሌሎች የተዘረዘሩት ነገስታትም በየአውራጃው ተበታትኖ /ተሰራጭቶ/ ይኖር የነበረውን ህዝብ ጠቅልለው ያስተዳድሩ የነበሩት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩና በየጊዜው መቀመጫቸውን እየለዋወጡ ነበር። ነገር ግን በዋናነትና በሰፊው የሚታወቁት መናገሻዎች ናፓታ፣ የሳባ ከተማ፣ መርዌ፣ አክሱም፣ ላስታ፣ ሸዋና ጎንደር ናቸው።

ይህም ሲሆን በጥንቱ ዘመን የቀድሞዋ ሠፊዋ ኢትዮጵያ አንድ ራሱን የቻለ አሐዳዊ መንግስት ነበራት ማለት ነው። የተጠቀሱት ቦታዎችም የ"ንጉሰ ነገስት" መቀመጫ ሆነው ያገለገሉ እንጂ የ"ንጉሶች" አይደሉም። በየቦታው ከንጉሠ ነገስቱ በታች የሆኑ የየግዛቱ ንጉሶች ይሾማሉ።

የዘመናዊት ኢትዮጵያ የታሪክ አባት የሚባሉት ኘ/ር ባህሩ ዘውዴ "እውነተኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ አጀማመር ለማወቅ የፅሁፍ መረጃዎች ብቻቸውን ብዙም አያራምዱንም ..." ይላሉ።

በእርግጥም እንደዚያ ነው። ምክንያቱም በአገራችን ተጠብቆ ለትውልድ የተላለፈው ታሪክ የነገስታቱ ስም ዝርዝርና የገዙበት ዘመን ብቻ እንጂ ዝርዝር ስራቸው በተለይ የጥንቶቹ ተፅፎ ስላልተገኘ ነው። ይህም ብቻ ሣይሆን መነሻቸውን ታሪክነገስት ያደረጉ ቀደምት ፀሃፍት "መነሻ" ብለው በጋራ የወሠኑትና የተስማሙበት መዳረሻ የለም። እንደተባለው አንዳንዱ ከኖኅ፣ ሌላው ከካም፣ የቀረው ከኩሽ፣ ሲጀምር፤ በርከት ያሉት ከሰብታ ይነሣሉ።

በተጨማሪም የአንዱ መነሻ ንግስተ ሣባ ትሆንና 3 ሺ አመት ተብሎ ሲወሠን፤ ሌሎቹ የባቢሎኑ ግንብ ግንባታና የቋንቋ ድብልቁን እንዲሁም የህዝቦች ብተና በተከሠተ ጊዜ ከመካከለኛው ምስራቅ ፈልሠው የመጡ የኩሽ ዘሮች ኢትዮጵያን ቆረቆሯት ብለው ታሪኩን ወደ 4ሺ ዓመት አስጠግተው ይነሣሉ። ይህን አቋም የያዙት ቀላል ቁጥር የላቸውም።



ሌሎቹ ደግሞ ከግብፅና ከሌሎች ቀደምት ታሪክ ካላቸው አገሮች በየጊዜው የነገደ ኩሽ ዘሮች ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ለመገመት ይዳዳሉ፤ ሌላውም ሌላ።

ጥቂቶቹ እንዳየነው ከኖኅ ጀምረዋል። የሚያሳምነውም፣ የሚያስኬደውም፣ እውነታውም ያለው ከኖኅ ጀምረው በጻፉ ፀሃፍት ዘንድ ነው። ይህንኑ እውነታ እያጠነከሩና እያፀኑ ለመቀጠል ያመች ዘንድም ስለባቢሎንና ስለግብፅ የሚመለከቱ ታሪኮችን ራሣቸውን የቻሉ አንድ አንድ ምዕራፍ በመሥጠት ለማየት እንሞክራለን።

ያን ስናደርግም ሌላ ምዕራፍ ስለተሠጣቸው ብቻ ከነገደ ካም ዘመነ መንግስት ታሪክ ወጥተን ሌላ ታሪክ ጀመርን ማለት አይደለም። ለየብቻ መስፈር ስላለባቸው ነው።

# ምዕራፍ ፫

## ኢትዮጵያና ባቢሎን

በርካታ ቀደምት የታሪክ ፀሃፍት ኢትዮጵያ በካም ኩሽ ነገድ መመስረቷን ያምናሉ። ከአዳም ጀምሮ በሚቆጠረው የሠው ዘር አመጣጥ የሚያምኑ ፀሃፍት በዚህ መነሻ ይስማማሉ። "የነገደ ካም ነገስታ " ብለውም ይዘረዝራሉ። ነገር ግን የኢትዮጵያ መስራቾች የሆኑ የካም ኩሽ ነገዶች ወደዚች አገር የመጡት ከባቢሎን ግንብ ጋር በተያያዘ በተከሠተው የቋንቋ መደባለቅና የህዝቦች ብተና አማካኝነት የመጡ ህዝቦች ያደርጓቸዋል። እንደገና ደግሞ መልሠው የነገደ ካም ነገስታት ብለው ከዚያ ዘመን በፊት እዚህ እንደነገሡ ይነግሩናል። ሁሉም ነገድ ቋንቋው ተደባልቆበት ሲበተን የኩሽ ዘሮች ወደ ኢትዮጵያ መጡና ይችን አገር ቆረቆሯት ይሉናል። ምናልባት ይህ ስህተት ለኛ የጠራ እውነትን ማያስጨብጠን አይቀርም። መቅደም ያለበትን እናስቀድምና እሡኑ እንቀጥላለን።

ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ከነቤተሠቦቹ ፈጣሪው ቃል ይገባለታል። "እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ…" በሚል ለኖኅና ለቤተሠቦቹ ይነገራቸዋል። አዲስ ኑሮ መጀመሩን ያሣየንና ኖኅ ልጆቹን ሲባርክ ሲመርቅ ያስነብበናል። ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ ወይንም ተከለ.. በማለት 350 አመት እንደኖረና እንደሞተ፣ ምድርም በልጆቹ እንተሞላች ገልፆልን ምዕራፍ 9ን ይደመድማል።

የብላቴን ጌታ ህሩይ "ዋዜማ" እስያን ለሴም፣ አውሮፓጳን ለያፌት፣ አፍሪካን ለካም እንዳካፈለ ይነግረናል። በርካታ ፀሃፍት የሚስማሙት በዚህ ነው። "የዓለም ታሪክ" ተብሎ የተተረጎመው መፅሃፍ ደግሞ በምዕራፍ 7 ቁ 7 "… እንዲህ ሆኖ የሠው ወገን ሁሉ ጠፋና እንደገና በምድር ላይ የአንድ ሠው ቤተሠብ ብቻ ቀረ። ይህም የሆነው 1656 ዓመት ከዓለም ፍጥረት በኋላ ነው።" ይላል። ማለትም ከክ.ል.በፊት 3844 ላይ ማለቱ ነው። ይሄው የዓለም ታሪክ በምዕራፍ 8 ከቁ 3 -4 ባለው "ኖኅ ከቤተሠቦቹና ከእንስሶቹ ጋር ከመርከብ ወጣ። በነዚህም እንደገና ዓለም በህዝብ ተሞላች። እንስሶችም በገዛ ራሣቸው ወደ ሩቅ እየሄዱ ተናኙ። ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ በየአገሩ ገቡበት። ለኖኅ ሶስት ልጆች ነበሩት። እነርሡም ሴም፣ ካም፣ የፌት ናቸው። እነዚህ ከቤተሠቦቻቸው ጋር ሰናኦር ወደተባለው አገር ገቡ።" ይልና ከቁ 6-10 ድረስ "… ህዝቡ በፍጥነት እየበዙ ይሄዱ ጀመር። ከጥፋት ውሃ ጀምሮ መቶው አመት እስኪፈፀም ድረስ ያለ ልክ ቁጥራቸው በዛ። ትውልዳቸውንም ለልጆቻቸው ይነግሯቸው ነበር። ወደ መርከብ ከገቡት



በቀር የጥፋት ውሃ መጥቶ ሠውንና እንስሣን ሁሉ እንዳጠፋ ይተርኩላቸው ነበር። በጥፋት ውሃ የሆነውን ሁሉ የሚያስታውሡ ወይም ወሬውን የሠሙ ሁሉ የሠው ክፋት ያንኑ የመሠለ ቅጣት እንደገና መልሶ ያመጣብናል እያሉ ይሠጉ ነበር። ስለዚህ ታላቅ ግንብ ለመስራት ተማከሩ። በዚያም ውስጥ ገብተው ሊሠወሩ ነበር። ይህም ግንብ ባብል ይባላል። በኤፍራጠስ ወንዝ ዳር በስተምዕራብ ወገን የህንፃውን መሠረት ቆረቆሩ። ወደ ሠማይ ለመድረስ እንዲመቻቸው ግንቡን ከፍ አድርገው ለመስራት አስበው ነበር። ግንቡን የሚሠሩት ፀሃይ ባደረቀው ጡብ ነበር። ጡቡንም ሲገነቡ ኖራና አሸዋ በመሠለ ነገር እያያያዙ ነው። ሠራተኞቹ በትጋት ይሠሩ ነበርና ጡቡን አንዱን በአንዱ ላይ እያደራረቡ ሲገነቡ ከላይ ሆነው ምድርን ቁልቁል ሲመለከቱት እጅግ ሩቅ ሆኖ እስኪታይ ድረስ ያጣድፉት ነበር። ነገር ግን ሠማዩና ፀሃዩ ከዋክብቱም ርቀታቸው ግንቡ ሲጀመር እንደነበሩ ናቸው እንጂ ያራራቃቸው ሁኔታ አልተለወጠም።" በማለት አሠራሩን ይተርካል። ይህ መፅሃፍ (የአለም ታሪክ) መፅሃፍ ቅዱሡ ዘርዝሮ የማይነግረንን የባቢሎንን ታሪክ ዘርዝሮ ስለሚነግረን ወሣኝ መንደርደሪያችን እናድርገውና ወደ መፅሃፍ ቅዱሡ እናልፋለን።

ስለዚህ በዚሁ በዓለም ታሪክ መፅሃፍ በምዕራፍ 9 ከቁ 1-7 ድረስ ያለውን ሃተታ እንደወረደ እንየው። "አንድቀን እነዚሁ እብዶች የሆኑ ህዝብ በስራቸው ላይ ሣሉ ታላቅ የሚያስገርም ነገር ሆነ። እንዲሁ እንደልማዳቸው ሲነጋገሩ ሣሉ በድንገት ቋንቋቸው ተለዋወጠና አንዱ ሲናገር ሌላው የሚለውን አላስተውል አለው። ማንኛውም ሠራተኛ ከላይ ሆኖ የታችኛውን ጡብ አቀብለኝ እያለ በጣቱ ሲያመለክተው የታችኛው ሠራተኛ የማያውቀው ቋንቋ ስለሆነ ሌላ ነገር አንስቶ ይሠጠው ጀመር። እንዲሁም ሠራተኞች አንድ ነገር ሲጠይቁ ሌሎች ደግሞ ሌላ ያልተባለውን ይሠጧቸዋል። ድምፅ ብቻ ይሠማቸዋል እንጂ አንዱ የተናገረውን ሌላው አይሠማውም ነበር። የሚለው እንደማይታወቅ ለመናገር እንደሚንተባተብ እንደ ትንሽ ህፃን ሆኑ። እንደዚህ ያለ የቋንቋ መለያየት ሲሆንባቸው ጊዜ የግንቡን ስራ ወደፊት ለመግፋት የማይሆንላቸው ስለሆነ ወደ ሠማይ እንደርሣለን የማለታቸው ተስፋ ተቆረጠና በዓለም ላይ ወደ ልዩ ልዩ ስፍራ ለመንከራተት ግድ ሆነባቸው። ከዚህ በኋላ በብዙ ክፍል ሆነው በብልሃት ለመነጋገር እየፈተኑ ወደ ልዩ ልዩ ስፍራ ለመሄድ ወጥተው የተበታተኑ ይመስላል። በእያንዳንዱ ክፍል ሲሄዱ ከኋላቸው ገልመጥ እያሉ ወደ ባብል ግንብ እያዩ ምናልባት ሣያዝኑ አይቀርም…..።

የሴም ልጆች በኤፍራጠስ አውራጃ ያለውን አገር እንደተካፈሉ ይመስላል:: የካም ልጆች በምዕራብ አውራጃ ያለውን አገር ይዘው ወደ አፍሪካ ፈቀቅ አሉ:: ከዚያ ምስርን/ግብፅን/ ያዙና ታላቅ ነገድ ለመሆን በቁ:: የያፌት ልጆች ወደ ግሪክ አገር ፈቀቅ አሉና ከዚያ አያሎችን የአውሮጳን አገር መሠረቱ:: በዛሬው ዘመን አያሌ መንገደኞች (በርካታ ጎብኝዎች አጥኝዎች) በኤፍራጠስ ወንዝ ዳር ሠፋፊ ኮረፍቶች አግኝተዋል:: የተሠሩበት በዝፍትና በሚያጣብቅ ነገር ባንድነት ተቦክቶ በፀሃይ በተተከሠ ጡብ ነው:: እነዚህም ኮረፍቶች ከ 4ሺ. ዓመት በፊት ተሠርቶ የነበረ የባብል ግንብ ፍራሽ እንደሆኑ ተረዱት::" ይላል:: ከ4ሺ. አመት በፊት የሚለው ከዚህ ዘመን ተነስቶ ወደ ላይ ተቆጥሮ ነው:: ማለትም ከክ.ል.በፊት 2ሺ. ዓመት ላይ መሆኑ ነው::

የጥፋት ውሃ ከደረሠ ከብዙ ዘመን በኋላ ነው የባቢሎን ግንብ የተጀመረው:: እናም እንደዚህ ሐተታና እንደ ሌሎች በርካታ ፀሃፍት እይታ ከሆነ ከ2ሺ. ቅ.ል.ክ በፊት የካም ልጆች ወደ አፍሪካ ጠጋ እያሉ ከመጡ ከዚህ ጊዜ በፊት በአፍሪካ ምድር ሠው አልነበረም ማለት ነው:: በአፍሪካ ምድር ሠው ከነበረ ደግሞ በባቢሎኑ ግንብ የተሣተፉ የካም፣ ኩሽ ነገዶች አይኖሩም ማለት ይሆናል:: መሪ ራስ ኤም.ኤ በላይ ቀደም ሲል እንዳየነው በጥንቷ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በነበረችው በናፓታና በመርዌ መካከል በምትገኝ "ደንጎላ" በተባለች ከተማ በአንድ ዋሻ የድንጋይ ሣጥን ውስጥ በርከት ያሉ ሠነዶች አገኙ ብለናል:: የተፃፈው በኋላኛው ዘመን በመጡ የሴም ዘሮች ነበር:: እናም የደንጎላው ሠነድ የሚያስረዳው በባቢሎኑ ግንብ የተሣተፉት 72 የቤተ ሤም፣ የቤተ ካምና የቤተ ያፌት ነገዶች መሆናቸውን ነው:: የተደባለቀውን የቋንቋ ዝርዝርም የተጠቀሠው መፅሃፍ ይዘረዝራል::

እነዚህን ነገሮች ይዘን ወደ መፅሃፍ ቅዱሡ እንምጣ:: በመፅሃፍ ቅዱስ በዘፍጥረት በምዕራፍ 10 ቁ 1 ጀምሮ "የኖኅ ልጆች የሴም የካም የያፌት ትውልድ ይህ ነው:: ከጥፋት ውሃም በኋላ ልጆች ተወለዱላቸው::" ብሎ ይጀምርና የያፌትን ነገድ በስም ዘርዝሮ ከቁጥር 6 ጀምሮ እስከ 20 ድረስ ባለው ደግሞ ስለ ካም ይዘረዝራል::

"የካምም ልጆች ኩሽ፣ ምጽራይም፣ ፋጥ፣ ከነዓን ናቸው:: የኩሽም ልጆች ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታህ፣ ራዕማ፣ ሰበቃታ ናቸው:: የራዕማ ልጆችም ሳባ ድዳን ናቸው::" ይልና መልሶ "ኩሽም" ብሎ ይቀጥለዋል::

"ኩሽም ናምሩድን ወለደ:: እርሡም በእግዚአብሄር ፊት ሃያል አዳኝ ነበር፣ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት ሃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ:: የግዛቱም መጀመሪያ በሰናኦር አገር ባቢሎን፣ ኦሬክ፣ አርካድ፣ ካልኔ ናቸው:: አሶርም ከዚያች አገር ወጣ:: ነነዌን፣ የረሆቦትን ከተማ፤



ካለህን፣ በነነዌና በካለህ መካከልም ሬሲንን፤ ሠራ:: እርሷም ታላቂቱ ከተማ ናት::

ምጽራይምም ሉዲምን ዐናሚምን፣ ላህቢምን፣ ነፍታሌምን፣ ፈትሩሲንም ከእርሡ የፍልስጤም ሠዎች የወጡባቸውን ከሱሊህምን፣ ቀፍቶሪምንም ወለደ:: ከነዓንም የበኩር ልጁን ሲዶንን (ሜዶን፣ መቄዶንያ ይሠኛል ወደ በኋላ) ኬጤያውያንንም፣ ኢያቡሳውያንንም፣ አሞራውያንንም፣ ጌርጌሣውያንንም አማቲንም ወለደ:: ከዚህም በኋላ የከነዓናውያን ነገድ ተበተኑ::" ይለናል:: ወደ የት ተበተኑ? ብለን ስንጠይቅ እዚያው በሚቀጥል ዓረፍተነገር አማካይነት እንዲህ የሚል ምላሽ ይሠጠናል "የከነዓናውያንም ወሠን ከሲዶን አንስቶ ወደ ጌራራ በኩል ሲል እስከ ጋዛ ድረስ ነው:: ወደ ሰዶምና ወደ ገሞራ ወደ አዳማና ወደ ሰቦይም በኩል ሲል እስከ ላሣ ድረስ ነው:: የካም ልጆች በየነገዳቸውና በየቋንቋቸው በየምድራቸውና በየህዝባቸው እነዚህ ናቸው::" ብሎ በቁ 20 ይዘጋውና በቁጥር 21 የሴምን ትውልድ ይዘረዝራል:: የያፌቱን መዘርዘር አይጠበቅብንም:: የሴሙን በስፋት እናገኘዋለን:: አሁን ማተኮር ያለብን በካም ላይ ነው::

ከላይኛው ታሪክ ስንነሣ የካም ልጆች ኩሽ፣ ሚጽራይ፣ ፋጥ፣ ከነዓን ሲሆኑ፤ የካም የመጀመሪያው ልጅ ኩሽ ደግሞ ሳባ፣ ኤውላጥ "ሠብታ"፣ ራዕማንና ሰበቃታን፣ እንዲሁም ናምሩድን ወልዷል:: የአገራችን ታሪክነገስትም ሆነ ክብረነገስት የአገር ውስጥ ፀሃፍትም ሆኑ የውጭ፣ የብራናው ወዘተ... ባጠቃላይ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ንጉስ ብለው የሚጀምሩበት ዝርዝር "ሠብታ"ህን ነው:: በዚህ መፅሃፍና በሌሎች ጥቂት መፅሃፎችም ቢሆን ኖህ፣ ካም፣ ኩሽ፣ ተብሎ ሠብታ ብሎ ነው የቀጠለው:: ባጭር አገላለፅ ከፍ ሲል "ኖኅ" ዝቅ ሲል "ሠብታ" አራት ነጥብ::

ይህ ከኩሽ ልጆች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ንጉስ የናምሩድ ወንድም ነው:: ናምሩድም የኩሽ ልጅ ነውና:: ነገር ግን ከሠብታህ ቀጥሎ በነገደ ካም ነገስታት ዝርዝር ውስጥ እንዳየነው ተከታዩ ንጉስ ኤሌክትሮን ነው:: ይህም የሠብታ ልጅ ነው:: ከዚያ ነቢር፣ አሜን 1ኛ... እያለ ይቀጥላል፤ እንጂ ናምሩድ በኢትዮጵያ የነገድ ካም ነገስታት ዝርዝር ውስጥ የለም ሊኖርም አይችልም:: እንግዲህ ናምሩድ የኩሽ ልጅ ሆኖ ሣለ ነገር ግን ከወንድሞቹ ተለይቶ ምናልባትም የዓባይን ወንዝ እያደነ ተከታትሎ በዚያው ወደ ባቢሎን ሄዶ ግዛት መስርቷል፣ ሃያል ተብሏል ከማለት ውጪ ሌላ እድል የለም!

የጎንደር ታሪክ የሚለው መፅሃፍ ቀደም ሲል እንዳየነው "... ካም በኢትዮጵያ ምድር ቆይቶ ሲሞት ልጁ ኩሽ የቤተሠቡ መሪ ሆነ::

እርሡም እንደ አባቱ ብዙ ዘመን ኑሮ ሲሞት ልጁ ሰብታህ/የናምሩድ ተከታይ/ በአባቶቹ ምድር በኢትዮጵያ ንጉስ ሆኖ ከክ.ል.በፊት ከ 2545-2515 ነገሠ" ይላል።

"የናምሩድ ተከታይ" ሲልም ሆነ፣ በመፅሃፍ ቅዱሡ የኩሽ ልጆች ተብለው ከተዘረዘሩ በኋላ እንደገና "ኩሽም" ብሎ በመጀመር "ናምሩድን ወለደ" ብሎ ስለሚቀጥለው ምናልባት የሚነሣ ጥያቄ ካለ አንድ ጥያቄ ብቻ ነው። እሡም ማነው ታናሽ ማነው ታላቅ? በተረፈ ወንድማማች መሆናቸው ከግልፅም በላይ ግልፅ ነው። ስለዚህ ማነው ታላቅ ማነው፣ ታናሽ የሚል ጥያቄ ሣይነሣ የሡብታህ ወንድም መሆኑን በመረዳትና ናምሩድ በኢትዮጵያ አለመንገሡን በመገንዘብ ብቻ ሁለት የኩሽ ዘሮች ተነጣጥለው መቀመጣቸውን እንወስዳለን። በአንድ አይነት ዘመን። ማን ወደዚህ መጣ? ማን ወደ ዚያ ሄደ? ናምሩድ ሃያል አዳኝ ሲባል (የአውሬ አደን አይደለም፣ የአገር አደን ነው፣ ምክንያቱም ".. ሃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ፣ የግዛቱም መጀመሪያ በሰናኦር አገር..." እያለ ስለሚቀጥል ግልፅ ነው።) ልክ በዚያው ዘመን ከወዲህ በኩል ከክ.ል.በፊት ከ2545-2515 ሡብታ በኢትዮጵያ ለመንገሡ ጥርጥር የለውም። ዘመኑ ከፍም ዝቅም ቢል አንድ ቡድን እዚያ አንድ ቡድን እዚህ ነበር የሚለውን እውነታ ሊያፋልስብን የሚችል ምንም ሃይል የለም። ነገሩን በደንብ ለማስረገጥ ያህል አንድ የኩሽ ሃያል ልጅ (ናምሩድ) ከኢትዮጵያ ወደ ባቢሎን ሔዶ ሌላ የኩሽ ልጅ (ሡብታህ) በኢትዮጵያ ነገሠ። ልጅ ሲባልም ነገድ መሆኑ ነው። ናምሩድ ብቻውን አልሄደም። ለዘመናት የተባዛ ህዝብ አለ። በተናጠል የምንጠቅሠው መሪ ነገስታቶችን ነው። ልክ በዚሁ መጠንም ወንድም የሚለው በታላቅና በታናሽ የሚገለፀው እንኳን መሆን ቢያቅተው ሁለቱም ከኩሽ እስከ ተገኙ ድረስ ለጊዜው (ለዚህ ሃተታ) በቂያችን ነው።

ስንቀጥል የካም ልጆች ኩሽ ሚጽራይ ፋጥ ከነዓን ናቸው ተብሏል። በዚህ መሠረት ከነዓን የኩሽ ወንድም ነው። የእርሡም ነገድ ቀደም ሲል እንዳየነው.. ሲዶንን፣ ኬጤያዊያንን ወዘተ ወለደ። የከነዓናውያንም ነገድ ተበተኑ የሚል ነገር አይተናል። ወዴት? ብለንም ጠይቀን ቦታዎቹ ተዘርዝረውልናል። የተጠቃቀሡት ቦታዎች (በነገድ ስም የተሠየሙትን ጨምሮ) በየጊዜው ስማቸው ሊለዋወጥ ይቻል እንጂ ወደ ጥንቷ ኑብያ ኢትዮጵያም ሆነ ወደ አሁኗ ኢትዮጵያ እልፍ አላላም።

ኢትዮጵያ ከቋንቋ መደባለቅ በኋላ የፈለሡ የኩሽ ዘሮች የመሠረቷት አገር አለመሆኗን በዚህ እንረዳለን።

የካም ኩሽ ነገድ የአፍሪካውያን መሠረቶች መሆናቸው ይታወቃል። እስካሁን ድረስ ባለው ጊዜ ማለትም ቋንቋ ከመደባለቁና



የባቢሎኑ ግንብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት፣ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የሡዎች ፍልሠት ከመከሠቱ በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ሠው ሳይኖር መሆኑ ነው። ስለዚህ በእነዚያ ዘመናት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ የኩሽ ዘር ከሌለ ለዘመናት ታምኖበት የመጣው የነገደ ካም የነገስታት ዝርዝር ስምና ገዙበት የተባለው ዘመንም ውድቅ ይሆናል ማለት ነው። ይሄ ደግሞ ሙሉውን የኢትዮጵያን ታሪክ መናድ ይባላል።

ሰብታ ከክ.ል. በፊት ከ2545-2515 በኢትዮጵያ መንገሡ እየታወቀ፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ መስራች የሆኑት ነገደ ካም ኩሽ ከባቢሎኑ ግንብ መፍረስ ጋር ተያይዞ ቋንቋ ሲደባለቅና የሡው ልጆች ሲበተኑ ከመጡና ከሡፈሩ የባቢሎን ሙከራና ክሽፈት እንዲሁም የቋንቋ መደባለቅና የነገዶች ፍልሠት ከክ.ል.በፊት በ2300 እና በ 2200 መካከል ነው። ይህም ሲሆን አይደለም ከሰብታ ከ "ባኬንደን መሊስ" እንኳ ብንነሣ ልክ አይመጣም። ስለዚህ ያለጥርጥር በኢትዮጵያ ያንኑ አንድ ቋንቋ ይዞ የነበረ የነገደ ካም ኩሽ ህዝብ ነበረ። ናምሩድ ከዚህ ገስግሶ ሄዶ እዚያው ሃያል ተብሎ እዚያው ተስፋፍቶ፣ እዚያው ቀርቷል። በትክክለኛው የመፅሃፍ ቅዱስ ያዘመን አቆጣጠር መሠረት የባቢሎን ግንብ ታሪክ 2247 ቅ.ል.ክ. መሆኑ ታውቋል። ነገር ግን መፅሃፍ ቅዱስ ዝርዝር ነገሮችን መተንተን ስለማይጠበቅበት ዘመኑ አልሠፈረም። ይሁን እንጂ በምዕራፍ 10 ከላይ ያየናቸውን የነገድ ተዋረዶች እንደየወገኑ ከዘረዘረልን በኋላ ነው ዝቅ ብሎ በምዕራፍ 11 ስለባቢሎን የሚተርክልን። የባቢሎኑ ስራ ወይም ሴራ በምዕራፍ 11 ከሠፈረ ደግሞ የዘመን ተዋረዱን እንደጠበቀ በቀላሉ እንረዳለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በፍልሠት መጡ ልንል ብንችል እንኳን ከወዲያኛው አገር ወደዚህኛው አገራችን ፈልሶ የመጣ የነገደ ካም ኩሽ ዘር የለም፣ ግብፅን ያለፈ የለም። ፈልሶ የመጣው ወደፊት እንደምናገኘው የሴም ዘር እንጂ የኩሽ ዘር የሚል በየትኛውም የታሪክ ሠነድ ተፈልጎ አይገኝም። ነገር ግን ተስፋፍቷል፣ ከሌላው ጋር ተዋልዷል፣ ተዳቅሏል፣ ተቀላቅሏል። ይሄ አንዱ ነው። ሌላው ቀሪ አማራጫችን ነገደ ካም ኩሽ በዚሁ በአፍሪካ ምድር ቀረ እንጂ ወደየትም አልተንቀሳቀም የሚል ነው። ይሄ የማይሆን ብቻ ሣይሆን አስቂኝ ቀልድ ይሆናል። በባቢሎኑ ግንብ የተሣተፈ ነገደ ካም ኩሽ ነበረ፣ ግንቡ በተገነባበትም ወቅት እዚህም ንጉስ ነበር። በጥቅሉ 1ኛ የኩሽ ልጅ የሆነው ናምሩድ የትም አልሄደም ብሎ መካድ፣ 2ኛ በአሁኑ ሠዓት የኩሽ ነገድ በአሁኗ ኢትዮጵያና በቀደሞዋ ኢትዮጵያ/ኑብያ/ እንዲሁም በመላው አፍሪካ ፈፅሞ የለም ብሎ መካድ። እነዚህ ናቸው አማራጮቻችን፡- ይህን ሁለቱንም ምርጫ ማንም ስለማይቀበለው 3ኛውን ምርጫ እንይዛለን። "ግማሹ ነገደ ካም እዚያ፣ ግማሹ እዚህ።"

ነገድን በሚመለከት በኖህ ሶስት ልጆች መነሻነት ሴም፣ ካም ያፌት ተብለው ተገልፀዋል፡፡ በመፅሃፍ ቅዱስ እንዲህ ሲረጋገጥ፣ ሣይንስ በገዛ ራሡ መንገድ ደግሞ በተመሣሣይ በሶስት ክፍሎ 1ኛ የኒግሮይድ ሠው ዘር፡- ጥቁር የቆዳ ቀለም ያለው ሲሆን የአፍሪካ ጥቁሮች፣ ቡሽሜን፣ ሆቴንቶ፣ ማሌዥያ… ወዘተ ወዘተ… 2ኛ የሞንጎሎይድ ሰው ዘር፡- ቢጫ የቆዳ ቀለም ያለው ሲሆን ቻይናውያን፣ ጃፓናውያን ሞንጎሊያ.. ወዘተ… ወዘተ… 3ኛ የካውካስያን ሠው ዘር፡- ነጭ የቆዳ ቀለም ያለው ሲሆን የኖርዲክ ቅርንጫፍ፣ የአልፓንያን ቅርንጫፍ ወዘተ… ወዘተ… እያለ ይተነትነዋል፡፡ ይህ አይነቱን ትንታኔ ከዚህ በላይ መዘርዘር ስለማያስፈልገን ወደ ጉዳያችን እንመለስ፡፡

በምዕራፍ 10 ትንታኔ መሠረት ከላይ እንዳየነው የያፌትንና የካምን የዘር ሃረግ እንደሚተነትነው፤ ከዚያው ምዕራፍ ሣይወጣ "ለሴምም ደግሞ ልጆች ተወለዱለት…" ብሎ ይጀምርና የነገድን ተዋረድ በስም እየዘረዘረ ቀጥሎ… "ስፍራቸውም ከማሴ አንስቶ ወደ ስፋር፤ ሲል እስከ ምስራቅ ተራራ ድረስ ነው፡፡…" የሚል ገለፃ ያስከትልና በመጨረሻው ዓረፍተ ነገር "የኖኅ የልጆቹ ነገዶች እንደ ትውልዳቸው በየህዝባቸው እነዚህ ናቸው፡፡ ህዝቡም ከጥፋት ውሃ በኋላ በምድር ላይ ከእነዚህ ተከፋፈሉ፡፡" ብሎ ምዕራፍ 10ን ይዘጋና ምዕራፍ 11 ከቁ.1 ጀምሮ "ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች፡፡ ከምስራቅም ተነስተው በሄዱ ጊዜ በሰናኦር ምድር አንድ ሜዳ አገኙ፡፡ በዚያም ተቀምጠው…" ያው… ዶሉቱ ማለት ነው፡፡ ወደ ሠማይ ግንብ ሊገነቡ ስራውን ጀመሩት፡፡

እነማን ናቸው? ብለን መጠየቅ ካለብን ምናልባት "ከምስራቅ ተነስተው.." ስለሚል የሴም ወገን "ሊበረክቱ" እንደሚችሉ እያሠብን መቀጠል እንችላለን፤ የካም ወገኖችም እንደነበሩበት አይተናል፡፡ ዞሮ ዞሮ የደረሡበት ቦታ "በሠናኦር ምድር አንድ ሜዳ አግኝተው.." ስለሚልና ሠናኦር ማለት ደግሞ ቀደም ሲል ከናምሩድ ታሪክ ጋር በተያያዘ "ሃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ፣ የግዛቱም መጀመሪያ በሰናኦር አገር ባቢሎን አሬክ አርካድ ካልኔ [illegible]ው፡፡" ስለተባለ እዚያ ሆነው እንደዶለቱ ግልፅ ነው፡፡ ሠናኦር ማለት [illegible]ን ነው፡፡ በኋላ ላይ የአሶር መንግስት ተመስርቶበታል፡፡ መፅሃፍ ቅ[illegible]ስ "አሶርም ከዚያች አገር ወጣ" የሚለን በኋላ ላይ የአሶር ገናና መንግስት ስለተመ[illegible] ነው፡፡ ከናምሩድ በኋላ፡፡ በዚህ ጊዜ ፈጣሪያቸው ተቆጣ ማለ[illegible] ቋንቋቸውን ደባለቀው፡፡ " እግዚአብሔር በዚያ የም[illegible]ቋልና ከዚያም እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ [illegible]ላል ዘፍጥረት 11 ከ ቁ 9-10 ያለው ዓረፍተ ነገር፡፡

የዓለም ቀደምት ታሪክ ውስጥ በግልፅ የሚታወቁ ሶስት አይነት [illegible]ሉ፡፡ 1ኛ ከኖህ ሞት በፊትና በኋላ ሠዎች ተበትነዋል፡፡ 2ኛ ከባቢሎኑ ግንብ መፍረስ በኋላ ሠዎች ተበትነዋል፡፡ 3ኛ ክርስት እጣ መውጣት በሚባለው ሠዎች ተበትነዋል፡፡ ያም ሆኖ ብተና ሲባል ሌሎች ንዑስ ብተናዎች ይኖራሉ፡፡ ይህም ሲባል ፍልሠት፣ ስደት፣ የጦርነት ሽሽት… ወዘተ ለማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ውጭ የሆኑ ብተናዎችም አሉ፡፡ ለምሣሌ "የከነዓናውያንም ነገድ ተበተኑ፡፡" የሚል ነገር አይተናል፡፡ ወደየት? ብለን ስንጠይቅ ግን በቀደመው ዘመን የቦታ እንጂ የአህጉር (ወይም የአገር ርቀቱ እጅግ ሣይሠፋ ወደተቀራራቢ አዋሣኝ ግዛቶች) ሲበተኑ ነው የምናየው፡፡ ይህም ከንዑስ ብተናዎች የሚካተት አይነት ነው፡፡
የባቢሎኑ ብተና ግን ዋና ከሚባሉት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም የኛ ዋነኛው ነጥባችንም ከዚሁ ጉዳይ ጋር የተያየዘ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለፀው የኢትዮጵያ እንደ አገር የመቆርቆር ታሪክ የሚጀምር ተብሎ (በስፋት) የተወሠነው ከባቢሎኑ ብተና በኋላ መሆኑ ነው፡፡ በጣም በሚገርም ሁኔታ ደግሞ የሠው ልጆች ሁሉ እስከ ባቢሎኑ ግንብ ድረስ በአንድ ላይ በአንድ ቦታ ነበሩ ማለት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ቋንቋቸው ተደባልቆ እነሡም ተበትነው የየራሣቸውን አገር መሠረቱ መሆኑ ነው፡፡

የግብፅ OLD KINGDOM ግን ወደፊት እንደምናየው ከክ.ል.በፊት ከ3200 ዓመት ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ በኢትዮጵያውያኑ ተመስርቶ ነበር፡፡ በኢትዮጵያውያኑ ሲባልም ከዚህ ተነስተው በሄዱ በጥቁር ኑብያንስ ለማለት ነው፡፡ የቋንቋ ድብልቁ ግን 2247 ቅ.ል.ክ ነበር፡፡

በባቢሎን ታሪክ ውስጥ ከወደ ግብፅ የወረዱና በባቢሎን የሠፈሩ ነገዶች እንደነበሩ ተፅፏል፡፡ ሌሎች ደግሞ አካድያን የሚባሉ ዘራቸው ሴማዊ የሆኑ በአካባቢው ይኖሩ ነበር፡፡ እነዚህ ህዝቦች ከዋነኛው ንጉስ ከሐሙራቢ በፊት የየራሣቸውን ትንንሽ መንግስት አቁመው በነገስታት መመራት ጀምረው ነበር፡፡

ናምሩድ ባቢሎንን እና አሶርን፣ ኑኒስ የነነዌን ከተማ፣ ሴሚራሚስ የተባለችው የባቢሎንን ከተማ ያስጌጠች ንግስት፣ ሠርዳናፓል የነነዌ ከተማ በጠላት ሲከበብበት ሃብት ንብረት ቤተሠቡን ሠብስቦ በፈቃዱ እሣተ ውስጥ ገብቶ የሞተ ንጉስ… እንደተከታተሉ ተፅፏል፡፡

ሱሜርና አካድ በተባሉት ነገዶች ላይ ሌሎች የሴም ዘሮች በየጊዜው እየተደባለቁ የከለዳውያንንና የባቢሎንን የመጀመሪያውን መንግስት ከቀድሞው የበለጠ አድርገው አቋቋሙ፡፡ በመፅሃፍ ቅዱስ ተደጋግማ የተነሣችው የባቢሎን ከተማ በ2500 እና በ2000 ቅ.ል.ክ መካከል ተመስርታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደመቀች ሔዳለች፡፡ ከአሶር፤ ከሜዶን፣ ከህንድ፣ ከፋርስ፣ ከአርመን፤ ከግብፅ ለሚመጡ ነጋዴዎች ዋና መገናኛና የሸቀጥ መገበያ መደብር ሆነች፡፡ እንዲህ ሆኖ በደመቀችበት ጊዜ ሐሙራቢ የሚባል

ሃይለኛ አዋቂና ህግ አጋጊነትን አጣምሮ የያዘ ንጉስ ተነሣላቸው። እርሡም ለባቢሎን መንግስት ለመጀመሪያው ዳይናስቲ /ስርወመንግስት/ 6ኛ ንጉስ ነው። ይህ ንጉስ የነበረበት ዘመን ከ1792-1750 ቅ.ል.ክ እንደሆነም ታውቋል።

ሐሙራቢ በነገሠ ጊዜ እንደ ሁለት የተለያዩ ነገድ የሚቆጠሩትን አካድንና ሱሜርን በአንድነት አዋህዶ የአሶርን፣ የኤላምን አገሮች ሁሉ እየወጋ የባቢሎን ወይም የከለዳውያን መንግስት የሚባለውን አገነነው።

ከእርሡ መነሣት በፊት ግን ናምሩድ በአካባቢው ታላቅ ሆኖ ቤተጣኦትም ገንብቶ ነበር። "ቤሉስ" የሚባለውን የወርቅ ምስል አሠርቶ አስገብቶበታል። ይህም የሆነው ከቋንቋ ድብልቅ በፊት ነው። ከድብልቁ በኂላ ሁሉም በየነገዱ ተከፍሎ የየራሡን ቋንቋ እየፈጠረ፣ እያዳበረ፣ በየአገሩ ግዛት እየመሠረተ የኖረው በርካታ ነበር። ስለዚህ ከቋንቋ ድብልቅ በፊት ያንኑ አንድ ቋንቋ የያዘ ህዝብ በኢትዮጵያ ብቻ ሣይሆን በግብፅም ይኖር ነበር። በባቢሎንና በዙሪያውም እንዲሁ። እነዚህን አገሮች ቀድመው ያስለጠኑት ከወደ ግብፅ ወረዱ የተባሉት ናቸው። በኑብያ፣ በግብፅ አድርገው የሄዱት እነናምሩድ!

ከኖኅ ሞት በኂላና በፊት በነበሩት ብዙ መቶ አመታት የሠው ልጆች እጅግ በርክተው በዓለም ላይ ተሠራጭተዋል።

ምንም እንኳ የካምን ትክክለኛ እድሜ ለማወቅ ባይቻልም መፅሃፍ ቅዱስ ሴም 600 ዓመት ሲኖር ያሳየናል። ስለዚህም በዚያ ዘመን አንድ ሠው አንድ ሙሉ ወይም ግማሽ ሚሊኒየም ይኖር ስለነበር የህዝቡ ብዛትም በዚያው መጠን ሲሠላ መበርከቱ አይገርምም።

የኖኅ የልጅ ልጆችና ተከታይ ትውልዶች ልባቸው የፈቀደውን አምልኮ ማምለክ ጀመሩ እንጂ ያባታቸውን የኖኅን አምላክ በማምለክ አልቀጠሉም።

ከባቢሎን ግንብ በፊት በነበረው ታሪክ በመፅሃፍ ቅዱስ ስለነገዶች፣ ስለትውልዱ አወራረድ ተዘርዝሮ ተጠናቆ ነበር። ነገር ግን በምዕራፍ 11 ቁ 9 የባቢሎኑን ታሪክ ከደመደመ በኂላ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኂላ ተመልሶ የሴምን ሁኔታ ያነሣና በቁ 10 "የሴም ትውልድ ይህ ነው።" እያለ በመቀጠል ብዙ የሴም ተዋረዶችን ይዘረዝርና አብርሃም ሲወለድ ያሳየናል።

የሴምን ተዋረድ መልሶ ያነሣበት ምክንያት አብራም/በኂላ አብርሃም/ የተባለው ፃድቅ ሠው ተወራርሶ መምጣቱን ሊገልፅን ነው። አገሩ ሁሉ ጣኦት ሲያመልክ አብራም እውነተኛውን አምላክ ይዞ የሚቀጥል የእብራውያን ነገድ መስራች ሲሆን እናያለን። ከአሶራውያን መንግስት በስተደቡብ በኩል ካለው ከላውዲዎን (ካልዲያ) (ከለዳውያን) በተባለው አገር ከታራ ሲወለድ ነው የምናየው። የተወለደበትን አገር ለቆ በምዕራብ በኩል



ከነዓን ወደ ተባለው አገር ፈጣሪው እንዲሄድ ያዘዋል። ይህም ሲሆን አምላክ ለኖኅ የገባውን ቃል ኪዳን ሲተገብረው እንመለከታለን። በም. 12 ከቁ 1 ጀምሮ "…. ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሣይ ምድር ውጣ። ታላቅ ህዝብም አደርጋሃለሁ፤ እባርክሃለሁ።… የምድር ነገዶች ሁሉ ባንተ ይባረካሉ።" ይለዋል። አብራሃም ከዑር ከለዳውያን ወጥቶ ወደ ተባለው ምድር ወደ ከነዓን ሚስቱን /ሦራን/ ሣራን ይዞ ይሄዳል። እዚያም ሲደርስ "ይችን ምድር ለዘርህ እሠጣለሁ" ተብሎ ይነገረዋል። የሄደባት አገር ከነዓን በኂላ ላይ ፓለስታይን የተባለቸው ናት።

አብራም በዚያው ሆኖ በአምላኩ ትዕዛዝ ወዲያ ወዲህ እያለ ጥቂት ዘመን ይኖርና በምድሩ ረሃብ ተከስቶ ወደ ግብፅ በእንግድነት የሚሄደውና ከፈርኦኑም የሚገናኘው፣ ከዚያም ወጥቶ ወደ ከነዓን የሚመለሠው.. ወዘተ በዘፍጥረት ም. 12 ላይ ይተረካል። በምዕ 14 ቁ 14 ጀምሮ ደግሞ " አይንህን አንሣና አንተ ካለህበት ስፍራ ወደ ሠሜን እና ወደ ደቡብ፤ ወደ ምስራቅና ወደ ምዕራብ፤ እይ፤ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሠጣለሁና…" ይባላል (ደቡብ ወደ ቀይ ባህር አቅጣጫ ነው) በምዕ 15 ቁ 13 ላይም አምላኩ አብራምን ሲያነጋግረው "ዘርህ ለእርሡ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፤ ባሪያዎች አድርገው አራት መቶ አመት ያስጨንቋቸዋል።…" ይለዋል።

በዚሁ ምዕራፍ ሌላ ቃል ኪዳን ይገባለታል። "… ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ጥልቁ እስከ ኤፍራጠስ ወንዝ ድረስ ይችን ምድር ለዘርህ ሠጥቻለሁ።" ብሎ ምዕ 15ን ይዘጋል። በምዕ 17 አብራም "አብርሐም" ይባላል። "…. ቃል ኪዳኔ ካንተ ጋር ነው። ለብዙ አህዛብም አባት ትሆናለህ። እጅግም አበዛሃለሁ። ህዝብ አደርጋሃለሁ። ነገስታትም ካንተ ይወጣሉ። ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል፤ ከአንተም በኂላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ። ለአንተና ካንተ በኂላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር የከነዓንን ምድር ሁሉ ለዘላላም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኂላ ለዘርህ እሠጣለሁ። አምላክም እሆናቸዋለሁ።" (ምዕ 17 ከቁ 1-8)

አብርሃም ለዓረቦችም ለአይሁዶችም አባት መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ በኂላ ነው አብርሃም፣ ይስሃቅ፣ ያዕቆብ…. እየተባለ ዳዊት የሚነሣው። ዳዊት ሠለሞንን ይወልድና አዜብ (ደቡብ ማለት ነው በግዕዝ) ንግስተ አዜብ፣ ወይም የሣባ ንግስት /ንግስተ ሣባ/ ማክዳ ከምትባለዋ ንግስት ጋር አቆራኝቶ ምኒልክን ሲወልድ የምናየውና ኢትዮጵያ የ3 ሺ. አመት ታሪክ ያላት የምንባለው። ነገር ግን ከአብርሃም ዘመን በፊትም ሆነ ከባቢሎኑ የቋንቋ ድብልቅ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ ህዝቦች ይኖሩ የነበረ መሆኑን ከላይ ካየነው ሀተታ በቀላሉ እንረዳለን።

## ምዕራፍ ፬
# አሮጌው ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ

በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠንከር ያለ እውቅና የተሠጠው ታሪክ ፀሃፊ ግሪካዊው ሄሮዱተስ ነው፡፡ ዓባይን "የግብፅ ህይወት ነው" እያለ ደጋግሞ የሚያነሣውም እሡ ነበር፡፡፡ "የግብፃውያንን የቀደመ ታሪክ ለመፃፍ መነሻዬ የናይል ዴልታ (ድፍድፍ) ነው" ይላል ሄሮዱተስ፡፡ (ሄሮዱተስ የተወለደበተ ዘመን ቅ.ል.ክ 490 ላይ ነው)

እርሡን ጠቅሠው የኢትዮጵያን ታሪክ የፃፉትም በእውነታው ያምናሉ፡፡ የ1985ቱ የነጋ ወልደ ስላሴ "ባለታሪክ ኢትዮጵያ" የተሠኘው መፃህፍ አንዱ ነው፡፡ በዚህ መፃሃፍ በምዕራፍ ሶስት "ቀደምቶቹ ግብፃውያን ይህን የናይል ወንዝ ዴልታ የሚል ስም ሠጥተውት ነበር፡፡" ይለናል፡፡ ዓረቦቹ ደግሞ የጥንቱን የናይል ስም ይዘው ናይል ወይም ናይል ምስር ብለው ይጠሩታል፡፡ ከ 6ሺ. ዓመታት በፊት ታላቁ የናይል ወንዝ ለግብፆች ህይወት እንደበረ ሁሉ አሁንም ህይወት እንደሠጠ ነው፡፡

የናይል ውሃ ግብፅ ከመድረሡ በፊት 3ሺ. ተራሮችንና አረንቋማውን ክፍል የኑብያን ግዛት አቋርጦ ይጓዛል፡፡

ሸለቆዎቹ ውስጥ የሚገኙትን ህዝቦች በአንድ መንግስት ጥላ ስር እንዲዋሃዱ የናይል ወንዝ አስተዋፅኦ ማድረጉን ፀሃፍት ሁሉ በአንድ ድምፅ ይስማሙበታል፡፡ ኢትዮጵያውያን ከግብፅ ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ሄሮዱተስ ልዩ ጥናት ከማድረጉም በላይ ዲሞክሪቲየስ የተባለው የግሪክ ፈላስፋም እስከ መርዌ ድረስ ተጉዞ "ሂዩሮግላፊ" ስለሚባለው ስዕላዊ ፊደል አጥንቶ የምርምር ዘገባውን አቅርቧል፡፡

እርሱ እንዲህ ይላል፡- "ኢትዮጵያውያን የስልጣኔ እርሾ ስለሰጧቸው ግብፃውያን የኢትዮጵያውያን ውለታ አለባቸው፡፡

ከክ.ል.በፊት 3 ሺ. አመታት ቀደም ብሎ በናይል ወንዝ ሸለቆ ይኖሩ የነበሩ የተለያየ እምነት፣ አስተሣሠብና ባህል የነበራቸው ህዝቦች በአንድ የገጠር መንግስት ሲኖሩ ከሌሎች በገጠር መንግስት ከሚተዳደሩ ህዝቦች ጋር ተጣምረው አንድ ሌላ ላቅ ያለ መንግስት ማቋቋም ነበረባቸው፡፡ እነዚህም መንግስታት ከሌሎች ጋር በመዋሃድ በጊዜ ሂደት "የላይኛውና የታችኛው ግብፅ" በሚል ስያሜ የሚጠሩ ሁለት መንግስታትን መፍጠር ቻሉ፡፡

በቀደመው ዘመን ጥቁር ኑብያንስ የተባሉት ኢትዮጵያውያን አሮጌውን ስልጣኔ በግብፅ ከመሠረቱ በኂላ ነው ከመካከለኛው ምስራቅ አሳራባች አገሮች የመጡ ነገዶች ተባብረው በኂለኛው ዘመን የተባበረ መንግስት መመስረት የቻሉትና እየገነኑ የሄዱት፡፡ "ፈርኦን" ማለት "የተባበረ" ወይም "ትብብር" ማለት ነው በእነሡ ቋንቋ፡፡ ከላይ የተጠቀሠው መፅሃፍ "በጥንት ጊዜ የናይል ፈሠስ ሸለቆ የመጀመሪያው የስልጣኔ አንቀልባ ሆኖ



ያገለገለ ምድር ነው፡፡ በዚህ በለሙ የናይል ሸለቆ አካባቢ የሠፈሩ አያሌ ጎሣዎች ነበሩ፡፡ ይህም ዘመኑ ከ5ሺ. አመት በፊት ነበር፡፡ እነዚህም ጎሣዎች ኑሮዋቸውን በዚህ ሸለቆ አካባቢ በማድረግ አንድ ላይ ሆነው መቀመጥ ጀመሩ፡፡ በዚያ ዘመን በዚህ አካባቢ የሚገኙ የነበሩ ነገስታት አካባቢውን በአጠቃላይ ለመግዛት ፍላጎት ስለነበራቸው በመካከላቸው ጦርነት ያካሂዱ ነበር፡፡ እነዚህም ጎሣዎች "ነገደ ኩሽ" የሚባሉት ኢትዮጵያውያን ነበሩ" ይለናል፡፡

ወደሌላው የመረጃ ምንጫችን ስናልፍ የ1951 ዓ.ም.ቱ የተከለፃድቅ መኩሪያ "የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ /ናፓታ መርዌ/ 1ኛ መፅሃፍ በምዕራፍ 5 እንዲህ የሚል ሃተታ እናገኛለን፡፡ "...የታሪክ አባት የሚባለው ስመጥሩው ሄሮዱተስ ወደ ግብፅ መጥቶ ዐባይንም ጎብኝቶ በፃፈው የታሪክ መፃህፍ፣ እንደዚሁም ዲዮዶር የሚባለው የሮማ ፀሃፊ ከግብፅ በፊት ስልጡንና ገናና የነበረችው ኢትዮጵያ መሆኗን፣ ህዝቦቿም ደግ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ሠላማዊ፣ በጦርነት ጊዜ ጀግና ጎበዝ መሆናቸውን እያጋነኑ ፅፈዋል፡፡ ኢትዮጵያም በአገር (በጂኦግራፊ) አቀማመጧ ከፍተኛ (ላዕላይ)፣ ግብፅ ግን ወደ ታች (ታህታይ) ስለሆነች ዓባይም ከላይ ከኢትዮጵያ ወደ ታች ወደ ግብፅ እየፈሠሠ እንደሚያጠጣት፣ አፈርም እያቀበለ እንደሚመግባት እንደዚሁ እንደውሃው አወራረድ ስልጣኔን ለግብፅ መጀመሪያ የሠጠች ኢትዮጵያ መሆንዋን እነዚሁ የታወቁት የጥንት ፀሃፊዎች እነሡንም የተከተሉት ሁሉ አስፋፍተው ፅፈዋል፡፡ በኂላ ግን ግብፅ ደግሞ ከኢትዮጵያ ያገኘችውን ስልጣኔ ይበልጥ አስፋፍታ እንደገና የ18ኛውና የ19ኛው ዳይናስቲ ነገስታት ኢትዮጵያን መልሠው እንደገዙ፣ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ኢትዮጵያውያኖች አይለው እንደገና ግብፅን ይዘው የ25ኛውን ዳይናስቲ እንደመሠረቱና እንደገዙ ተፅፏል..." ይሉናል፡፡

አንድ ሌላ ተቃራኒ መነሻ እንጨምር፡፡ የዴቪድ ላምብ The Arabs (በነብዩ እያሡ "አረቦችና እስራኤል" ተብሎ ተተርጉሟል) "... በግብፅ ምድር ቢጋዛ የሚገኙት ፒራሚዶች ከመሠራታቸው አንድ ሺ. አመት ቀደም ብሎ በ3500 ቅ.ል.ክ ወደ አረቢያ በመምጣት የተዳቀለውና የተዋሃደው ህዝብ በተከታታይ በቡድን በቡድን እየፈለሡ ከሠላጤው ምድር በመውጣት እንደ አዲስ ዘር ወደ ሰሜን ሠፈሩ፡፡ በዚህ በኤፍራጠስና ጥግሪስ ወንዝ ሸለቆዎች የመጀመሪያውን የሠው ልጅ ስልጣኔ ፈጠሩ፡፡

"አውሮፓ ዘላን ጎሣዎች በጭቃ ጎጆዎች የሚኖሩበት አካባቢ በነበረበት ጊዜ ግብፃውያን ታሪካቸውን በራሣቸው ፊደል ይፅፉ ነበር፡፡ ለመስኖ ልማት በዮችንና ፈሠሶችን በመዘርጋት የቅየሣ ስልትን ፈጠሩ፡፡ ፒራሚድን በመገንባት ምህንድስናን አስተዋወቁ፡፡ የዓለም የመጀመሪያዎቹ የህዋ ጠበብት በመሆን 365 ቀኖች ያሉት ቀን መቁጠሪያ በማበጀት አንድን ቀን በ24 ሠአታት ከፈሉት፡፡ በዓባይ ሸለቆ ከበቀሉ ፓፒረስ ከተባሉ እፅዋት የመጀመሪያውን ወረቀት ሠሩ፡፡ ከእህል የመጀመሪያውን ጠላ፣ ከወይን

የመጀመሪያውን ወይን ጠጅ ጠምቀው በጭቃ ምርግ በተከደኑ ማሠሮዎች አቀረቡ፡፡

"የዓባይ የየዓመቱ ውሃ ሙላት ከሚያስከትለው ጥፋት ለመዳንና ወንዙ የሚያመጣውን ድቡሽት አፈር እህል ለማብቀል ለመጠቀም ግብፃውያን መተባበርና መደራጀት ነበረባቸው፡፡ ለዚህም መንግስት አቋቋሙ፡፡ እንደ ውሃው ጥልቀት መጠንም ግብር መክፈል ጀመሩ፡፡ የወንዙ ውሃ ከፍታ በጨመረ መጠን የበለጠ ድቡሽት አፈር ያመጣል፤ ያ ማለት ደግሞ የበለጠ ምርትና የላቀ ግብር ማለት ነው..." ይላል፡፡ ሌላው "የአለም የድንጋይ ዘመን ብቻም አይደለም የሁሉም ቀደምት ስልጣኔ ብርሃን ፈንጣቂ ህዝቦች ጥቁር ኑብያንስ ናቸው" ብለው ያለጥርጥር አስረግጠው የሚገልፁት ተንሸር ፀሃፊና የስነ ዕፅዋት ተመራማሪ የሆኑት Fredric T.Bolton በ"Plant and Planiet ጥናታዊ መፃህፋቸው (እ.ኤ.አ በ1982) ያሠፈሩት ነው፡፡ ዲሞክራቲየስንና ሄሮዱተስን እንዲሁም ሆሜርን ይጠቅሣሉ፡፡ "... ጥቁር ኑብያንስ በላይኛው ግብፅ መንግስታቸውን መስርተው በነበረ ጊዜ በጨረቃ ዘመን 5ሺ. ቅ.ል.ክ የመካከለኛው ምስራቅ ቅልቅል ጎሣዎች በታችኛው ግብፅ መስፈር ጀመሩ፡፡ በየነገዳቸው እየተመሩ የበርሃ እንስሶችን ያረቡ ነበር፡፡ ምናልባትም በኋላ የቴምር ዛፎችን በእንስሶቻቸው እየለወጡ /እየገዙ/ ከላይኞቹ ጋር ሣይስማሙ አይቀርም፡፡ የመጀመሪያው ግብር ታችኞቹ ገባሪ፣ ላይኞቹ አስገባሪ ሆነው የተጀመረው በዚያን ጊዜ ይመስላል፡፡ ኑብያንሶችም/የኑብያ ኢትዮጵያውያን/ ወረድ እያሉ ምርታቸውን ያዩ እንደነበር በብዙ ተፅፏል፡፡ በእርግጥ አንድ አይደሉም፡፡ አማልክቶቻቸው የታችኞቹ ጥጃ/ኮርማ/ ነበር፡፡ የላይኞቹ ብዙ አይነት ነበር፡፡ አሞራና እባብ ይዘወተራል፡፡ ኒል /ዓባይ/ የጋራ አምላካቸው እንዲሆንም ተስማምተው ነበር ይባለል፡፡..." ይሉናል፡፡

ካየናቸው ሁተታዎች የምንረዳው የመጀመሪያዎቹ የኑብያ ኢትዮጵያውያን ከዛሬው ኢትዮጵያ አልፈው እስከ ላዕላይ ግብፅ ግዛታቸውን አስፍተው ሲኖሩ፤ ከመካከለኛው ምስራቅ አገሮች በየራሣቸው ነገድ እየተመሩ ልዩ ልዩ ግዛቶች ላይ ህዝቦች ሲሠፍሩ የኋለኛዋን ስልጡን ግብፅን የመሠረቷት ነገዶችም ወደ ጋዛ እና ወደ ላሣ እየተጠጉ በመጨረሻም በታህታይ ግብፅ (መምፊስ) እንደሠፈሩና የአማልክት መቅደሣቸውን በመምፊስ ሠርተው ባልሠለጠነ የጎሣ አለቃ ሲመሩ እንደቆዩና የላዕላይ ግብፅ መስራቾች (በቴብ) የአማልክታቸውን መቅደስ አቋቁመው በዓባይ ላይ የበላይነትን ይዘው መጤዎቹን ሲያስገብሩ እንደቆዩ፣ ታችኞቹ ከላይኞቹ ግብርናን እንደተማሩ፣ እየቆዩ ሲሄዱም ከጥገኝነት ለመላቀቅ መሠልጠን እንዳለባቸው በመረዳት ለዚህም የአካባቢው ትንንሽ መንግስታት መተባበር እንደሚኖርባቸው በመገንዘብና ተግባራዊ በማድረግ ላዕላይ ግብፅን መጠቅለል መቻላቸውን ነው፡፡

ከድንጋይ ዘመን ወደ ወርቅ ዘመን እስኪሸጋገሩ ድረስ ብርቱ ሆነው መደራጀታቸውንም በቀላሉ እንረዳለን፡፡



ቀደም ሲል "18 ኢትዮጵያዊ ነገስታት ግብፅን ገዝተዋል" የሚል ነገር አይተናል፡፡ ይህ ሲባል ግን በ"ዳይናስቲ" ከሚሠላው ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡ የመጀመሪያው ዳይናስቲ እና የመጀመሪያው ፈርኦን ፍፁም ተደራጅቶ ከመመስረቱ በፊት የነበሩ ታሪኮች ናቸው፡፡ እነዚህን "ሁለት የግብፅ መንግስታት" ተብለው በላይና በታች የተከፈሉትን ጥቂት ፀሃፍት "ሁለቱ ተባብረው ታላቋን ግብፅ መሠረቱ" ይሉናል፡፡ ነገር ግን የበርካቶች አገላለፅ ከዚህ የተለየ ሲሆን፤ ይኸውም ታችኞች በራሣቸው ላይና ታች ሀሜንና ደቡብ በሚል የተከፋፈለ አሠፋፈር ሆፍረው በባላባቶቻቸው ሲመሩ እንደኖሩና ዋናው የበላይ ንጉሠነገስትና አስገባሪያቸው የላዕላዩ ግብፅ የጥቁር ኑብያንስ ነባር መንግስት የነበረ መሆኑን ነው፡፡ እነዚያን ባላባቶች አስተባብሮ ነው "ማኔስ" የተባለው የመጀመሪያው ንጉስ የግብፅን መንግስት ለመመስረት የቻለው፡፡ ግብፆች በአንድ በተባበረ መንግስት ከተጠቀለሉ በኋላ ነው ተደራጅተውና አይለው ኢትዮጵያውያንን ከላዕላይ ግብፅ (ከቴብ) በሃይል ያባረሩዋቸውና ነፃ መንግስት መስርተው ታላቅ መባል የጀመሩት፡፡

ማኔስ የመጀመሪያውን መንግስት መስርቶ ንጉስ የሆነበትን ጊዜ የግብፅን ጥንታዊ የሂዩሮግላፊ ፅሁፍ በመተርጎም የታወቁት ጆሴፍ ፍላቭየስ፣ ማኔቶን ሻምፖሊዮን፣ ሙሴ ማርዮት፣ ወደ ቅ.ል.ክ 5 ሺ. ዓመት ሲያደርሡት ቆይተው ነበር፡፡ በመጨረሻ አሜሪካዊው ሚስተር ብሪስትድ ጠለቅ ያለ ምርምር አድርጎ ቅ.ል.ክ 3400 አደረገው፡፡ በመጨረሻው መጨረሻ ስቱይንዶርፍ የተባለው የጀርመን ሊቅ የጨረቃውን የዓመት አቆጣጠር /354 ቀኑን/ እና የፀሃይ አቆጣጠሩን ግኝት /364 ቀን ከ6 ሠዓቱን/አመሣክሮ ቅ.ል.ክ 3200 ዓመት ላይ ወሠነው፡፡ ዛሬ ድረስ እዚህ ላይ እንደቆመ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ከግማሽ ሚሊኒየም በላይ በሆነ እድሜ የተባዛው የነገድ ካም ህዝብ አሮጌውን ስልጣኔ በላዕላይ ግብፅ መስርቶ ነበር ማለት ነው፡፡

አሮጌውን ስልጣኔ በፀባይ የተቀበሉት የኋለኞቹ የታህታይ ግብፅ መስራቾች ደግሞ አሮጌውን አድሠው በሃይል ላዕላይ ግብፅንም ሲጠቀልሉ የአሮጌው መስራቾች ወደ ኑብያ ኢትዮጵያ ማለትም ወደ ናፓታ ተሸጋሽገዋል፡፡ ናፓታ የኢትዮጵያ የመናገሻ ከተማ የሆነችው ለመጀመሪያ ጊዜ ቅ.ል.ክ 3200 ላይ እንደሆነ በሂዩሮግላፊ ፅሁፍ ያለአንዳች አወዛጋቢ ሁኔታ የተረጋገጠ ነው፡፡ ምናልባት የውጪ አገር ፀሃፍት 3200 B.C ብለው ስለፃፉትና የአገር ውስጥ ፃሃፍትም በተመሣሣይ 3200 ቅ.ል.ክ ብለው በመፃፋቸው በዘመናችን አቆጣጠር የ7 ወይም የ8 አመት ልዩነት ካልኖረ በቀር ትክክለኛው ጊዜ የተጠቀሠው ነው፡፡ ከዚህ ዘመን በፊት ግን ቴብ መናገሻቸው ነበረች፡፡ የመጀመሪያው ፈርኦን እነዚያን ሁሉ ነገዶች አደራጅቶ ኢትዮጵያውያኑን ከቴብ አባረረ፡፡ ስለዚህ ወደ ናፓታ መጡ፡፡ በዚህ መሠረት ከ3200 B.C በፊት የነበረው ስልጣኔ ሁሉ ምንም እንኳ አሮጌ ቢሆን የኑብያንሡ ነው፡፡ የፈርኦኑ ምስረታ መምፊስ ስለነበር እንደማለት፡፡

በርካቶች ይህን ዘመን ያሠፍሩና "ግን እንዴት? በማን ዘመን?" ብለው በመጠየቅ ይመስላል ቁጥሩን አስቀምጠው ብቻ ያልፉታል፡፡ ለምን ቢባል በ3200 ናፓታ መናገሻ ከሆነች ይህ ዘመን በነገስታቱ ዝርዝር ላይ እንደሚታየው የካም (የኖህ ልጅ) አስተዳደረ ተብሎ የተቀመጠበት ዘመን ነው፡፡ ከዚህም በላይ የህዝብ ብዛት የለም፣ በዚህም ላይ ከካም ቀጥሎ የነገሠው ኩሽ ነው፣ እሡም ተከታዩ ሠብታህም ከዚህ በኋላ ነው ወይ የመጡት? እንዴት እነ ጣና ይጠቀሟሉ?.. ወዘተ.. የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሣ ነው፡፡

ኖኅ ከመሞቱ በፊት በነበረው 350 አመታት ካም፣ ሴምና ያፌት ምን ያህል ሊስፋፉ እንደሚችሉ ግልፅ ነው፡፡

ካም እዚህ በነበረ ጊዜ በዓለማዊውም፣ በመንፈሣዊውም ፅሁፍ እንደምንረዳው፤ ወይም ሶስቱ የኖኅ ልጆች ከመሞታቸው በፊት ዓለም በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ህዝቦች መጥለቅለቋን ነው፡፡ ስለዚህም ካም፣ ኩሽ፣ ሰብታህ... እየተባሉ በተከታተሉ ቁጥር ዋና ዋና ግንዱ ሲፃፉ እንጂ በውስጣቸው ያሉት ትውልዶች አንዳንድ ግዛት ለየብቻቸው እየያዙ አገር መስርተዋል፤ ነግሠውበታልም፡፡ ገነን ካሉ አገር በእነሡ ስም ትሠየማለች፡፡ የኩሽ ልጅ የሆነው ናምሩድ ወደ ሠናኦር ከሄደ በኋላ የራሡ የናምሩድ ልጅ አቢስ ከነ ነገዱ በዚች ምድር ይኖር ስለነበር ኩሽ /የኩሽ ነገድ ምድር፣/ አቢስ /የአቢስ ነገድ ምድር/፣ አገሩን አቢሲኒያ ብለው ሠይመውት እንደነበረ ወደፊት የምናየው ነው፡፡ አንድ የትውልድ አለቃ ቢነገስም ባይነግስም ነገዱን ይዞ የሠፈረበት ቦታ፣ አካባቢ ወይም አገር በስሙ ይጠራል፡፡ ወይም ሊጠራ ይችላል፣ የራሡን ነገድ በደንብ ካደራጀና ካጠነከረ ሌላውን ነገድ ወግቶ ሊያስገብር ይችላል.. ወዘተ፡፡ ቋንቋውን ሊያዘምን ይችላል... ወዘተ፡፡ በኋላቀርነቱም ሊቀጥል፣ ሊሠለጥን ይችላል ወዘተ፡፡ በሌላ አገላለፅ ዋናው ግንድ እንዳለ ሆኖ ቅርንጫፎች ይኖራሉ፡፡ የካም የልጁ ልጅ ናምሩድ ባቢሎንን መስርቶ ታላቅ ንጉስ ሆኖ ተመልሶ መጥቶ ወንድሙን ሰብታህን ሊወጋው ቢችል (ነገዱን) ሊገርመን አይገባም ነው ለማለት የተፈለገው፡፡ እዚያው ከቀረ ታሪኩ እዚያው ይፃፍለታል፡፡ የሆነውም ያ ነው፡፡ በሌላ በኩል የልጅ ልጅ አያቱን ተመልሶ መጥቶ ሊወጋውም ይችላል፡፡ የአንድ ሠው እድሜ ከ200 በታች ሆኖ የምናየው ከባቢሎኑ ሴራ በኋላ ባለው ጊዜ ነው፡፡ ለማንኛውም ግን ትልቁ ጥያቄ ወጥ ግዛት ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ከኢትዮጵያ እስከ ባቢሎን ወጥ አልነበረም፡፡ ከኢትዮጵያ እስከ ቴብ ግን ወጥ ግዛት ነበር፡፡ ለምሣሌ ናምሩድ በኢትዮጵያ የነገስታት ዝርዝር የለም፡፡ በባቢሎኑ ግን አለ፡፡ የሡ ወንድሞች መናገሻቸውን ጣና ያደረጉትም፣ ቴብ ያደረጉትም በኛ ታሪክ ነገስት ተዘርዝረዋል፡፡ ወጥ ግዛት ስለሆነ፡፡ ናምሩድ በባቢሎን ሆኖ ኢትዮጵያን ልግዛ ቢል ግን ከኢትዮጵያ እስከ ባቢሎን ወጥ ግዛት ሊሆን ይገባል፡፡



እንግዲህ... የሠው ልጅ የፍጥረት መጀመሪያ አዳም /አደም/ ነው በሚለው አይደል አምነን እዚህ ድረስ የመጣነው? ጥሩ ነው፡፡ ልክ ነን፡፡ ስለዚህ አዳምና ፈጣሪው የተነጋገሩበት ቋንቋ ነበረ፡፡ እብራይስጥኛ እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ፡፡ ግዕዝ ነው የሚሉ ብዙዎችም አሉ፡፡ ዓረብኛ ነው የሚሉም በርካታ ናቸው፡፡ ምንም ይሁን፡፡ ብቻ ግን የሚነጋገሩበት ቋንቋ ነበራቸው፡፡ ኖኅም ከአዳም 10ኛ ግንድ እንደመሆኑ መጠን ያው የድሮውን ቋንቋ ነበር የሚናገረው፡፡ ከፈጣሪው ጋርም በዚያው በሚሠማው ቋንቋ ይነጋገሩ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ ፊደል ግን የለም፡፡ ፊደል ያለመኖሩም ሌላ እውነት ያስጨብጠናል፡፡

ከቋንቋ መደባለቅ በፊት በነበረው ጊዜ በሐይማኖታዊውም ሆነ በሣይንሣዊው ምርምር የተረጋገጠው ስዕል እንጂ የመፃፊያ ፊደል አልነበረም፡፡ እስከ ቅ.ል.ክ 2000 ዓመት ድረስ የሠው ልጆች ወጥ ሆኖ በሚነበብ ተከታታይ ሆሄ /ፊደል/ የፃፉት ነገር የለም፡፡ የግብፅ ሂዬሮግላፊ፣ የግራክ ፒክቶግራም ብቻ ከልደት በፊት 3 ሺ ዓመት ድረስ ይታወቃሉ፡፡ እነሡም በአንድ ስዕል ብዙ መልዕክቶችን የሚገልፁ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ግሪክ ስንል የኒለኛዋን አይደለም፡፡ "ሲዶን" በምትባል ጊዜ ነው፡፡ አቴናውያን፣ ስፓርታውያን ገና ሣይታወቁ፣ የካም ነገድ በሆነው በከነዓን የበኩር ልጅ የተመሠረተውን ከተማ ነው፡፡ ስለግሪክ አመሠራረት ከተክለፃድቅ መኩሪያ ሐተታ እንረዳና ወደ ፊደሉ ስንመለስ ነገሩ ግልፅ ይሆናል፡፡

"ዛሬ ግሪክ በሚባለው ስም የተጠቀሰው ህዝብ ያን ጊዜ ግን ዘሩም ቋንቋውም የተለየያ ነበር፡፡ የኑሮውም ጊዜ በግምት የሚታወቀው ከክ.ል.በ1600 ዓመት ጀምሮ ነው፡፡ ግሪኮች የሚባሉት በምዕራብ በኩል ባለው አገር ተቀምጠው ሳለ ደግሞ ከምስራቅ የመጡት የዮኒክ ቋንቋ የሚናገሩ ዛሬ አቴና ባለበት አቲካና፣ አውቢያ፣ በሚባለው በምስራቅ ወገን ተቀመጡ፡፡ እነዚህም የአቴናን ከተማ የመሠረቱ ናቸው፡፡ ደግሞ ግማሾቹ ከላይ ከሠሜን ከቴሳሊያን፣ ከትራችያ መጥተው እስከ ቆረንጦስ ድረስ ያለውን አገር ያዙ፡፡ እነዚህም ለየግላቸው ሶስት ቋንቋ (ዲያሌክት) ለየራሣቸው የሚናገሩ ህዝቦች በያሉበት ተቀምጠው ጥቂት መቶ ዓመታት እንደኖሩ ከሠሜን ዶሪክ ከሚባለው ስፍራ ቋንቋቸውም የራሣቸው የሆነ የዶርያ ህዝቦች አገራቸውን ትተው በተሣልያ አልፈው የዛሬውን ደቡብ አገር የፔሎፒኒን የላቆኒን አገር ያዙ፡፡ ከዚያም አብረዋቸው ከተደባለቋቸው ግሪኮች ጋር ያለፉት ክራትና ኘሮን የሚባለውን አገር አቀኑ፡፡ የስፖርታንም ከተማ ከተሙ፡፡..." ( ተክለፃዲቅ መኩሪያ 1965 ዓ.ም)

ይህ ሁሉ ከቋንቋ መደባለቅ በኋላ የሆነ ነው፡፡ ስለዚህ በይፋ የሚታወቀው የነገድ ምስረታ በመካከለኛው ምስራቅ የተጀመረው ከህዝቦች ብተናና ከቋንቋ መፋለስ በኋላ ነው፡፡ ለምሣሌ አብርሃም የእብራውያን ነገድ መስራች መሆኑ ይታወቃል፡፡ አብርሃም ይስሃቅን ይስሃቅ ያዕቆብን ከወለዱ በኋላ ነው ያዕቆብ የሚለው ስም እስራኤል በሚል ተለውጦ ነገደ እስራኤል

የሚባሉ አንድ ሆነው ነገር ግን የተከፋፈሉ ዘሮች የምናየው። ከነገድ ምስረታ በኋላ ቀስ በቀስ ሁሉም ነገድ ወይም አገር የየራሡ ፊደል ሲኖረው ችሏል። (አብርሃም የኖረው ከ2ሺ. - 1800 ቅ.ል.ክ ነው) የሁሉም ነገድ የመፃፊያ ፊደል ከየት መጣ? ካልን ወይም መሠረቱን ከጠየቅን ሁለት ቀደምት አገራት ስለሚነሡ ነው የግሪክን አመሠራረት ከላይ ለማየት የተገደድነው። እናም ከግብፅ፣ ከግሪክ፣ ከባቢሎንና ከሌሎች አጎራባች ቀደምት አገራት ክብ ውስጥ አንወጣም። ሙሴ በሲና ተራራ የተፃፈ ህግ የተሠጠው ቅ.ል.ክ. 1300-1200 ባለው ጊዜ መካከል ነው። እስራኤላውያን በግብፅ በባርነት ያሣለፋት ከ1700-1300 ቅ.ል.ክ ድረስ ለ400 አመታት ያህል ነው። ግብፅ ስዕላዊ ፊደል ያገኘችው 3200 ቅ.ል.ክ ላይ ነው። ቴብን የራሷ ያደረገችውም በዚህ ዘመን ነው።ቴብ ማለት የአማልክት ቤት ማለት ሲሆን በጥንታዊው ስዕላዊ ፊደል ቤት ብለው ፅፈውበት ነበር። ግብፅ አገር ከመሆኗ በፊት።

የመጀመሪያው ስዕላዊ ፊደል መስራቾች ግብፃውያን መሆናቸው በይፋ ይታወቃል ተብሏል። ሂየሮግላፊ አሉት። ከዚያ ግሪኮች ፒክቶግራም አሉትና ቀጥለው ቅዱስ የፊደል ቅርፅ የሚል ስያሜ ሠጥተው ከዚያው ከስዕል ያልወጣ ፊደል ቁጥራቸውን በርከት አድርገው አሣደጉት። ግብፆች 3 ሺ. ዓመት ላይ "ሂዮራቲክ-የቀሣውስት ፊደል" አሉና አሁንም አሣደጉት። በጥቅሉ ከ4ሺ. -2ሺ. ዓመት ቅ.ል.ክ በቤተመንግስትና በካህናት አለቆች ብቻ ይታወቅ የነበረውን ስዕላዊ ፊደል ለአፃፃፍ እንዲመች ሆኖ ነገር ግን ያው ስዕልነቱን ሣይለቅ እስከነሙሴ መነሣት ድረስ ቆይቶ ወደፊት ታሪኩን እንደምናገኘው በመጨረሻ በኑብያ ኢትዮጵያ በናፓታ ቆይቶ በነገሠው በቲሃርቃ ጊዜ "ዲሞቲክ-የህዝብ ፊደል" ተብሎ ተሻሽሎ ይሠራበት ጀመር። ይህ ኢትዮጵያዊ ንጉስ ግብፅንም ሊቢያንም መካከለኛው ምስራቅንም የገዛ ንጉስ ነበርና ዲሞቲክን በደንብ እንዲስፋፋ አድርጎ ነበር። በኋላ ላይ ታላቁ እስክንድር ታላቅ ተብሎ ግብፅን ሲይዝ የግሪክና የዲሞቲክ ተቀላቅሎ ኮፕት የሚባለው ፊደል ይሠራበት ጀመር። ይህም ቅ.ል.ክ 300 ላይ ተጀምሮ ለ1ሺ. አመታታ ያህል ቆየና በ700 ዓ.ምህረት ከእስልምና መፈጠር በኋላ ግብፅ በዐረቦች ስትያዝ የአርበኛ ፊደልና ጽሁፍ ተተካ። በኑብያና በግብፅ ፀንቶ ቀረ።

ወደነጥባችን ስንመጣ በጥንቱ በፓፒረስ/በልጥ ብራና/ ይፃፍ የነበረው ስዕላዊ ፊደል ምንም እንኳ ለብዙ ሺ. ዓመታት ተለዋወጠ ቢባልም መነሻውንም፣ ይዘቱንም፣ እምብዛም አልለወጠም፤ ከጥቂት መከረባበት በስተቀር።::: እሡ ይቆየንና ግን ፊደላቱ ሁሉ መነጪ የተባሉት ከግብፅ፣ ከግሪክ እልፍ ሲል ባቢሎን። እነዚህ አገራት ቀደምት ታላላቅ መንግስታት የተመሠረቱባቸው አገራት ናቸው። እነዚህ ሁሉ አገራት ቋንቋ ከመደባለቁ በፊት ያንኑ አንድ ቋንቋ የያዘ ህዝብ የሠፈረባቸው ናቸው። እነዚህ ሁሉ አገራት ከኢትዮጵያ በሄዱ ጥቁር ህዝቦች የተመሠረቱ ናቸው። እነዚህ ሁሉ አገራት ከቋንቋ መደባለቅና ከህዝብ ብተና ጋር በተያያዘ ልዩ ልዩ በተለይ የሲም ነገዶች ሄደው የታጨቁባቸው አገራት ናቸው። ታላላቅና አዳዲስ



መንግስት መስርተው ከመግነናቸው በፊት ግን ነገደ ካም ኩሽ በጣም ያልሠለጠነና አሮጌ ስልጣኔ የሚባለውን መስርተዋል። የገጠር መንግስት የሚባለውን አቋቁመዋል። ፊደልንም ሣይቀር መስርተዋል። ቀደም ሲል በ"መግባቢያችን" ላይ ካነተትናቸው የልዩ ልዩ ፀሃፍት ሃተታዎች ውስጥ የዶክተር ተወልደ ትኩዕን መፃህፍ ጠቅሠን እንዲህ ሲሉ አንብበን እንደነበር የሚታወስ ነው። "…. የካም ዘሮች ያልሠፈሩበት ቦታ አልነበረም። ሔሮዱተስ የግሪክ ቀደምት ነዋሪዎች የካም ዘሮች ነበሩ ብሏል።" የሚል ነገር አይተን ነበር። ስንቀጥል "የጥንት ግብፃውያን ስልጣኔ የነጮች ስልጣኔ እንዳልሆነ የሚከራከሩ ወገኖች የሲፊኒክስን ሃውልት ፊት ማየት በቂ ነው ይላሉ። ያ ፊት ደግሞ የጥቁር ፊት ነው። አሜሪካ በሚገኘው አፍሮ ሴንተሪዝም ማዕከል እንዳውም በግሪካዊነት የሚታወቁት ሶቅራጠስ፣ ሆሜር፣ የሒሣቡ ሊቅ ፓይታጎረስና ኢኩሊድ ሁሉ ጥቁሮች እንደነበሩ ያስረዳሉ። በሰነ ፅሁፍ ረገድም ቢሆን የግዕዝ ሳብዕ ፊደላት የተለየ ድምፅ ተሠጧቸው በቁማቸው ከኢትዮጵያ ፊደላት የተቀዱ ናቸው። ይህ በተጠየቅ ወይም በሎጂክ ያለ እውነታ ነው። እንደዚሁም በዚህ በኢትዮጵያችን ላላው ሃይልና ለተሠሩት ትልልቅ ስራዎች ተጠያቂ የሆን ትውልድ ነበረ፣ አለም፣ ይኖራልም። ይህ እጣተ ነበልባል ትውልድ ነው። ጥበብንና እውቀትን ከመጀመሪያው ጀምሮ ለዓለም ህዝብ በግብፅ አድርጎ ወደ ግሪክ በመላክ የታላቅ ስልጣኔ ባለቤት አስማተሪና መሪ የሆነው።" የሚል ነገር እናደምጣለን ወይም እናነባለን።

ይህ ስለተባለ ብቻ ሣይሆን የመጀመሪያውን ስዕላዊ ፊደልን ጥቁር ኑብያንስ ባሠሯቸው መቅደሶች ላይ "ቤት" የሚል ዛሬ የ"በ"ፊደል ቅርፅ ያለው ፅሁፍ ከግብፅ ምስረታ በፊት ተፅፎበት የነበረ በቁፋሮ ተገኝቷል።

አንባብያን ከመፅሃፍ ቅዱሡ ወጥቶ የተዘረዘረውን የካም ኩሽ ነገድን መለስ ብላችሁ ብታዩ ታሪካችን ፍሠቱን ጠብቆ ከላእላይ ወደ ታህታይ መፍሠሡን በቀላሉ ታረጋግጣላችሁ እላለሁ። ግልጽ ነው "ፈገግ"ም ያሠኛል።

የኖኅ መርከብ በጣናው/በኢትዮጵያው/ አራራት ተራራ አረፈች። ማንም "አረፍ!" ሊለኝ አይችልም እዚህ ላይ፤ ብትሉኝም አላርፍም። ተግባብተን እንደመጣነው እዚህኛው ትረፍ እዚያኛው ትረፍ በታሪካችን ላይ ቀንጣት ተፅእኖ አያሳድርም። አንባብያን በመሠላችሁ ልትወስኑ ትችላላችሁ። ምክንያቱም ከሶስት ነገር አያልፍም ታሪኩ። ዋናው የጥፋት ውሃ መከሠቱን አለመካድ እንጂ መስማማታችን አይቀርም። ለነገሩ በሣይንስም በቅዱስ ቁርዓንም በመፅሃፍ ቅዱስም ተረጋግጧል። ስለዚህ፡-


1ኛ ከጥፋት ውሃ በኋላ የኖኅ መርከብ በአርማንያው አራራት ተራራ አርፋ ኖኅና ቤተሠቦቹ ሲተርፉ ሴምንና ያፌትን ትቶ ወደ ኢትዮጵያ ካምን ይዞ መጥቷል። ሁለቱ ልጆቹ አውሮፓንና እስያን ይዘው ሲስፋፉ አንደኛው ልጁ ካም በአፍሪካ ተስፋፍቷል፣ የካም ልጆች እስከ ኑብያ ድረስ አልፈው ሔደው ሃያላን ሆነዋል፤

2ኛ ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ቤተሠቦቹ ሲተርፉ የቀድሞ ኑሯቸውም እዚያው መካከለኛው ምስራቅ ነበርና አሁንም መርከቧ እዚያው አካባቢ አርፋ ኖኅም እዚያው ቀርቶ እንደተባለው ለሶስቱ ልጆቹ ግዛት ሲያካፍል አፍሪካን ለካም ሠጥቶት ወደዚህ መጥቶ ተስፋፍቷል፤

3ኛ ከጥፋት ውሃ በኋላ የኖኅ መርከብ በጣናው አራራት ተራራ አረፈችና ቤተሠቡ ጥቂት ዘመን ቆይቶ ሴምና ያፌት ከኢትዮጵያ ተነስተው ወደ እስያና ወደ አውሮፓ ሔደው ካም እዚሁ ቀረ። እናም ተስፋፋ። በመሃል እነ ናምሩድ እነከነዓን ወደ ሆው ርስት ዘለቀው ገቡ።

ሁለተኛው ላይ ልንወዛገብ አይገባም። ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ቤተሠቦቹ ሲተርፉ የቀድሞ ኑሯቸውም እዚህ ስለነበር አሁንም መርከቧ እዚሁ ስላረፈች ኖኅም እዚሁ ቀርቶ እንደተባለው ለሶስቱ ልጆቹ ግዛት ሲያካፍል አፍሪካን ለካም ሠጥቶታል ልንል እንደምንችል መታሠብ አለበት። ልክ በዚሁ መጠንም ኖኅ የዓዳምን መኖሪያ እንዲወርስ ተፈቅዶለት ከሆነ ገነት እዚህ ነበረች፤ ገነት እዚህ ካልነበረችና በአርማንያው ከነበረች ደግሞ ብላቴን ጌታ ህሩይ " ትተነዋል" ያሉትን "ነገደ ኦሪን" እናስነሣለን። ያኔ የ7ሺ አመት ታሪክ ይኖራታል ማለት ነው። አዳም ተባሮ የተሸኘባት ምድር ከሆነች የግድ ነው። ግዮንስ የት ሊወድቅ? "ሚስጥር ናት" እያልን ለማለፍ እስካልተዘጋጀን ድረስ እየተፈላሠፍን አይሆንም። አይደለምም።

የኖኅ መርከብ በጣናው አራራት ተራራ ካረፈች በኋላ ባለቤቱና ልጆቹ እንዲሁም አብረዋቸው የነበሩት እንስሣ አራዊትና ነፍሣት ሁሉ ይወጣሉ። ኖኅም እስከመጨረሻው እውነተኛውን አምላክ ሲያመልክና በግብርና ሲተዳደር ኖረ። የቤተሠቡ ሁሉ ቋንቋም አንድ ነበር። ኖህ ከመሞቱ በፊትና በኋላም ነገዶች እየበረከቱ ነበር። በየመሠረቱት ግዛት በየዋሻው የእንስሣና የአውሬ ስዕሎችን አስመስለው ይስሉ ነበር። የተባዙት ነገዶች በያሉበት ሆነው የመሠላቸውን ማምለክ ጀመሩ፤ በአጠቃላይ ከ3844 ቅ.ል.ክ እስከ 3200 አካባቢ አሮጌው ስልጣኔ በአፍሪካ እየተስፋፋ መሔድ ጀምሮ ነበር። በዓለምም ጭምር።

በዓባይ ሸለቆዎች ድንበር የሚበቅለው ፓፒረስ የተባለው ተክል (አሁንም በጣና ሃይቅ ደሴቶች በብዙዎቹ ይበቅላል) በልጡ ላይ የመጀመሪያውን ስዕላዊ ፊደል የኖኅ ልጆች ፈጠሩት ወይም ጀመሩት አሌፍ፣ ቤት፣ ጊሜል፣ ዳሌት... እያለ  የሚከታተለው የሂብሩ ፊደል ወይም አ በ ገ ደ እየተባለ የሚነበበው፣ በአርበኛም መነሻ የሆነው፣ በግዕዝም የፊደል መነሻ የሆነው በአማርኛም "ሀ" ተብሎ የሚነበበው በላቲንም " a" (ኤ) ተብሎ የሚነበበው የመጀመሪያው የስዕላዊ ፊደልም፣ የሠለጠነው ተከታታይ ፊደልም ምንጩ ይሄው ሆነ። ቤት!



ይህንንም ይዘው እነ ናምሩድ አባታቸው ባልፈቀደላቸው (ከኖኅ ምርቃትና በርኮት ውጪ በሆነ አካሄድ) ሔደው በመካከለኛው ምስራቅና በአጎራባች አገራት መንግስት መሠረቱ። ከዚች ምድር ይዘውት የሄዱት ስልጣኔ አለ። የመጀመሪያው የጥጥ ፈትል ውጤት የሆነው ሸማ፣ ጠላ፣ ከወይን የሚሠራ ጠጅ፣ በበሬ የማረስን ግብርና፣ ዝናምን ጠብቆ ከማረስ ጋር በተያያዘ ክረምት፣ በጋ፣ ፀደይ... የሚባሉትን የወራት ክፍልፋዮች ለይቶ የማወቅን ጥበብና ከዚሁም ጋር ተያይዞ የጨረቃውን አቆጣጠር ወደ ፀሃይ አቆጣጠር ለመለወጥ የሚያስችል ዘዴን፣ በጠብታዎች ልኬት ቀንን በሠዓት መከፋፈል መቻልን፣ ንብን በቀፎ ማከማቸትንና ማርን ማግኘት መቻልን፣ ለመድሃኒት የሚሆኑ እፅዋትን ለይቶ ማወቅን፣ ሁሉንም ነገሮች ልጆች ከአባታቸው ከኖኅ ተምረው ነበር። አባታቸውም ከጥፋት ውሃ በፊት የነበረውን የአኗኗር ዘዴ ዘርዝሮ ያውቀዋልና፣ ከእነርሡ በፊት በዙ ኖሯልና፣ የቀድሞውን ስልጣኔ በዚች ምድር አስተምሮ ነበር መርቆ የሸኛቸው። እነ ናምሩድ ግን ፈጠኑ። የፈጠኑት በስልጣኔ ብቻ አልነበረም። ያን ጊዜ እንደ ስልጣኔ በሚቆጠረው በጣኦት አምልኮም ፈጣን ነበሩ። እዚያ ሄደው አጥለቀለቁት። የሠፈሩባት ምድር ሁሉ ለሌላ ነገድ ትሠጥና መንግስትም ይመሠረትና ስልጣኔው ሁሉ ይወረስና ይዘቱን ሣይለቅ መልሶ በሚበተኑ ነገዶች አማካኝነት ይሠራጫል። በራሷ በኢትዮጵያም ይህ መሠሉ ክስተት ሲከናውን እናያለን። ከእነዚህ ውስጥ በኋለኛው ዘመን ውርርሡን በደንብ የምናየው ቋንቋ አንዱ ነው። ፊደልም ጭምር።

እናም አሮጌው ስልጣኔ የሚባለው ሁሉ ምንጩም ፍንጩም ከዚህ ተለኩሶ እየነደደ እዚያ የደረሠ እንጂ ሌላ አይደለም። ግን የሌላውን ሲለኩሡ የራሣቸው ጠፋባቸው። ባጠቃላይ ቀደምት ስልጡን አገር ግብፅ ነች ተብሎ እስከተወሰነ ድረስ የግብፅ ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ስለተወሠደ፣ ሚስጥሩ ሁሉ ይፍታታል።

"የለም የግብፅ መስራቾች ስልጣኔን ከምስራቅና ከባቢሎን ይዘውት የመጡት ነው!" የሚል ተከራካሪ ከተነሣብንም "ያንንስ የመሠረቱት እነማን ሆኑና?" ብለን በመጠየቅ እንገት እናስደፋለን። የነናምሩድ ጉዳይ በመፅሃፍ ቅዱሡም በዓለማዊ ፅሁፉም በደንብ ስለሚታወቅና የኖሩበት ዘመንም ገሐድ ስለሆነ፣ እንዲሁም እነርሡ እዚያ በኖሩበት ዘመን ወንድሞቻቸው ኢትዮጵያ ላይ ነግሠው ስለነበር መፈናፈኛ የለም። እንዲያው ጠንከር ያለ ተከራካሪ አጋጠመን እንበልና " ከግብፅ ወደ ኑቢያ ኢትዮጵያ የካም ዘሮች ፈልሠው መጡ እንጂ እዚህ ሰብታህ የሚባለው የናምሩድ ወንድም የምትሉት አልነገሠም ነበር" ቢሉን እኛ "ያማ ከሆነ በዚያ ዘመን እዚህ ንጉስ ከሌለ ግብፃውያን ሃያል የሆኑበት ዘመን ነበርና፣

ሠው እንደመሆናቸው መጠን የውሃን ጥቅም ያውቃሉና ንጉስ የሌለበትን አገር ይይዙ ነበር እንጂ. ግብፅን የሙጥኝ ብለው ተወስነው የሚቀሩበት ምን ምክንያት ይኖራል? ለድፍን 1ሺ. ዓመት ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ሲዋጉ፣ ሲታረቁ ኖረው አይደለም እንዴ በመጨረሻ ቅ.ል.ክ 1500 ላይ ተማክቶላቸው ኢትዮጵያን ማስገበር የቻሉት? ምን የሚሉት መከራከሪያ ነው?" ብለን እንከፈማለን። ለነገሩ በ "ሰብታህ" የኢትዮጵያ ንጉሰነገስትነት ያልተስማማ "ቀደምት" ፃሃፍት የለምና ቢከራከሩን ብለን የተመኘነው ባእዳኑን ነው። ስለዚህ ገዛ ነው። ምናልባት ያልደፈንነው ቀዳዳ ካለ "የዘመን አቆጣጠሩ የናንተ ዝቅ ያለ ነው፣ እኛ ከእናንተ በፊት ገናና ነበርን" ብለው ቢሞግቱንና የመንፈሳዊውን አቆጣጠር አንቀበለውም ቢሉን እነ ሉሲን፣ ሠላምን፣ አርዲን፣ ካዳሙን፣ እናስነሣለን። "በጥሩት ውሃ የነፈሩ ፖስቸራይዝድ አጥንቶች ናቸው" ቢሉን ደግሞ እሡም የተገኘው እኛ ጋ ነው እንላለን።

ከዚህ የበለጠ ማጠሪያ ቢገኝ የኢትዮጵያን የታሪክ አጥር በደንብ እናጥረው ነበር። ልክ ናምሩድ የባቢሎኑን ቅጥር እንዳጠረውና በኋላ የነገሠችው ንግስት ሴሚራሚስ ጠግባ ህንድን እወጋለሁ ብላ ዘምታ ጦሯ ተሸንፎ የህንዱ ንጉስ ግዛቷን ዘልቆ ገብቶ ቅጥሩን እንዳፈረሠባት ሁሉ የኢትዮጵያ ታሪክም በደንብ የታጠረ የነበረና በኋላ የፈረሠ ነው። የባቢሎን አጥር በኋላ ላይ እንደነገሩ ታጠረ። የኛ ግን ዛሬ ድረስ ሣይታጠር ቆይቷልና በዚህ መሰሉ እውነታ በተቻለ መጠን ፊርሶ ከመቅረት እንታደገዋለን። ላሁኑ ግን የዓለም ቀደምት ስልጣኔ ከኢትዮጵያ መሄዱን አፅድቀን እንለፍ። በሙሉ ድምፅ። ግልፅ ነዋ!

## ምዕራፍ ፭
## የአጋዚያን ዘመነ መንግስት

እነዚያ ያየናቸው ታሪኮች ሁሉ ይከናወኑ የነበሩት ኢትዮጵያ ውስጥ የነገደ ካም ነገስታት እየተባሉ እየተከታተሉ ይነግሡ በነበረበት ዘመን ነው። ምንም እንኳ የኢትዮጵያን ታሪክ የያዙ ቀደምት ፅሁፎችና ፀሃፍት (ዋና መነሻቸውን ታሪክ ነገስት ያደረጉ) ስማቸውንና የገዙበትን ዘመን ሣይዘረዝሩ ባያልፉም የፈፀሙትን ታሪክ አብሮ ለማተት የተቻለበት ሁኔታ የለም። ስለዚህ የአገር ውስጥ መነሻችን እንዳለ ሆኖ በየሡው አገሩ ብናማትርና ብንቀላውጥ አግባብነት ይኖረዋል።

እናም የነገስታት መነሻ ሆነው እስከተዘረዘሩና ስማቸውና የገዙበት ዘመን እስከሠፈረ ድረስ ማን በዘመኑ ምን እንደፈፀመ ገና ለገና በዝርዝር አልታወቀም በሚል መነሻ ምንም ሣይፈፅሙ እንደሞቱ መቁጠር አይቻልም። በዘመናቸው ምን እንደፈፀሙ ካልታወቀ እድሉ ካለ በዘመናቸው ምን እንደተፈፀመ ማወቅ መጠነኛ ግንዛቤ ያስይዛል።

እንግዲህ ቀደም ሲል ያየናቸው እንደ አንዳንዶቹ ከኖኅ፣ እንደ አንዳንዶቹ ከካም፣ እንደ አንዳንዶቹ ከኩሽ፣ እንደብዙዎቹ ከሡብታህ ጀምረው እስከ ጲኦሪ1ኛ ድረስ ነገስታቱ ከተዘረዘሩ በኋላ የጲኦሪ ዘመን ላይ የተለየ ነገር ይከሡታል።

"ነገደ አጋዝያን" የሚባሉት ይተካሉ። ይህ የብዙዎች ድምዳሜ ነው። የነማን? ከተባለ "የነገደ ካም ነገስታትን የሚዘረዝሩ ፀሃፍት ሁሉ" ነው መልሡ። በውጭ አገር ፀሃፊ ለሚያምን እነ ጃንሞሪዎ፣ በአገር ውስጥ ፀሃፊ ለሚስማማ እነ አለቃ ታዬ፣ እነብላቴን ጌታ ህሩይ፣ እነተክለፃድቅ መኩሪያ ወዘተ....።

*ታሪኩ ባጭሩ ይሄ ነው። እስከ ጲኦሪ 1ኛ ድረስ የተዘረዘሩት የነገደ ካም ነገስታት ናቸው። እንዲሁም የካም ወንድም ሴም ዘጠኝ ልጆችን ይወልዳል። ከዘጠኙ አንዱ አርፋክሰድ ይባላል። እርሡም ሳላህን፣ሳላህ ኤቦርን፣ ፋሌቅንና ዮቅጣንን ይወልዳል። ዮቅጣን ደግሞ 13 ልጆች ይወልዳል። ከእነዚህም ከ13 ነገዶች አምስቱ ማለትም ሳባ፣ አባል፣ ኦፊር፣ አቢማር፣ ሐዊላ የሚባሉት ከወንድሞቻቸው ተለይተው ራቅ ያለውን የመካከለኛው ምስራቅን አገር ትተው ወደ የመን ተጠግተው ተቀመጡ። በየመን ሲኖሩም የህንድ ነገስታት እየወጉ ሲያስቸግሯቸው እላይ የተዘረዘረው የነገስታት ዝርዝር እንደሚያመለክተው የካም ዘር ጲኦሪ 1ኛ በነገሠበት ዘመን በ1980 ቅ.ል.ክ የመንን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው መጡና ሰስቱ ነገዶች ሳባ በትግሬ፣ አባል በአዳል፣ኦፊር በኦጋዴን ተቀመጡ። እንደመጡም የመጀመሪያውን አምስቱን አመት ለካሙ ነገድ ለጲኦሪ 1ኛ ሲገብሩ ኖሩ።*

በዚህ መካከል የህንድ ንጉስ ራማ /ብርሃማ/ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ጺኦሬን ወግቶ አሸንፎ መንግስቱን በመቀማት ህዝቡን እንደ ባሪያ መግዛት ጀመረ። በዚህ ጊዜ እነዚህ የዮቅጣን ልጆች ተላልከው ከያሉበት ተሰባሰበው ራማን ወግተው ሠራዊቱን አሸንፈው እርሡን ገደሉና ህዝቡን የካሙን ነገድ ነፃ አወጡት። ተመካከረውና ተስማምተውም የሳባውን ነገድ አክናሁስን አነገሱት። እናም ነፃ ያወጡትን አገር ያዙት፤ መንግስቱንም ተረከቡት። በዚህ ምክንያት አጋዚያን ተባሉ። ይሉናል። ነፃ አውጪ ማለት ነው፤ በዕግዝ።

ፀሃፍቱ በዚህ ይስማማሉ። ትንሽ ግር የሚላቸው "የህንድ ንጉስ..." የሚለው ነው። ይህም ቢሆን የህንድ ንጉስ እንዴት መጣ? እንዴት ገነነ?... አይነት ጥየቄ ከጠቀስናቸው ፀሃፍት ጥቂቶቹ ያነሡና በዚያ ሠዓት የገነነ መንግስታ ባቢሎን...? በሚል ክፍት አድርገውልን ያልፋሉ። ባጠቃላይ እንዴት የሚለውን በዝርዝር ሊነግሩን ባይችሉም የስልጣን ውርርሡን ያምኑበታል።

ስለዚህ የህንዱን ክፍተት ለሌላ ዓላማ ማለትም ስለሌሎች አገራት ሁኔታ ሊተረክበት ታቅዶ ከሠፈረው ፅሁፍ (ከዓለም ታሪክ መፅሃፍ) ቆርሠን ጥያቄውን እንመልስና በዚህ ፋንታ ሌላ ያልተመለሠ ጥያቄ ተክተንበት እናልፋለን። ቀጣይ ፀሃፍት እንዲሞሉት ለማለት ነው። ጥያቄውን እናቆይና መልሡን እናስቀድም።

የዓለም ታሪክ የባቢሎኑን ታሪክ ከተረክ በኋላ ሠዎች ቢበተኑም በዙሪያው የቀሩ እንደነበሩ ያወጋናል። እናም የባቢሎን ከተማ ከቀድሞው የበለጠ እየደመቀች መሄዷን በሚተርክ ጊዜ ዙሪያዋን አሣምረው እንዳጠሯትም ይገልፃል። ቅ.ል.ክ 2229 ላይ ነው የአሶር መንግስት አሹር በተባለው ንጉስ ሲጀመር የሚያሣየን። ለማለት የፈለገው የመጀመሪያውን ዳይናስቲ ነው። ከናምሩድ በኋላ።

ብዙ ጊዜ ይሄ አገር ሲጠቀስ ግር ልንሠኝ አይገባም። የመጀመሪያ ስሙ ሠናአር ነው። ከዚያ ባቢሎን፣ ቀጥሎ አሶር፣ እንደገና ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ወዘተ እያለ ዋና ከተማው እየተለዋወጠ የሚቆይና፤ አንዳንድ ጊዜ አንድ አገር ሆኖ በአንድ መንግስት ሲጠቀለል፣ ሌላ ጊዜ ከሁለት በላይ አገር ሆኖ ባቢሎን፣ አሶር፣ ፋርስ ተብሎእየተከፋፈለ በተለያዩ ነገስታት ሲመራ የኖረ ነው። ምንም ቢባል ቦታው በፋርስ ባህር በስተሠሜን በኤፍራጠስና ጢግሮስ ወንዞች መካከል የሚገኝ ነው። ሞሶፖታሚያ (በወንዞች መካከል)የሚገኙ ተብለውም ይጠራሉ አሶር እና ባቢሎን።. ለማንኛውም ወደ ጉዳያችን ስንመለስ ፈገግ በሚያሠኝ አተራረክ ከምዕራፍ 10 ቁ 5 ጀምሮ እንዲህ የሚል ነገር እናገኛለን።

"... በዚህ ከተማ ውስጥ ደምቆ የሚታይ ቤተ መንግስትና አታክልት ነበረበት፤ ሳሠራሩም እንዲህ ያለ ሁኔታ ነበረው። ከምድር ላይ ጣያርፍ አየር ላይ የተንጠለጠለ ይመስል ነበር። ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችና ብዙ አይነት አበቦች



ነበሩበት። (አጥሩን ወይም ቅጥሩን ማለት ነው) ደግሞ አሶራውያን ለዋናው ጣኦታቸው ለቤሉስ (ቤል) ወይም ለበአል የተሠራ እጅግ ያማረ ቤተጣኦት ነበር። ይህ ቤተ ጣኦት ወደ ላይ ቁመቱ 680 ፊት ነበር። በዚሁም ውስጥ ከፍታው 40 ፊት የሚሆን የጣኦቱ የቤሉስ የወርቅ ምስል ነበረበት። ይህንንም የነገርኳችሁን የባቢሎንን ከተማ ቀድሞ የሠራው ናምሩድ ነው። ስለእርሡም ያ ሃይለኛው አዳኝ ብሎ መፅሃፍ ቅደስ ነግሮናል።

ነገር ግን አትክልቱንና ቤተመንግስቱን ያሠራችው ሴሚራሚስ የተባለች ሴት ነች። የኑኒስ የአሶር ንጉስ ሚስት ነበረች። ነገር ግን ንጉሡ ኑኒስ በሞተ ጊዜ ንግስት ሴሚራሚስ ዋና የመንግስቱ ገዥ ሆነች። ክብርን ፈላጊ ሴት ስለነበረች ባቢሎንን እጅግ ያማረች ከተማ ልታደረጋት ፈለገች እንጂ ዝም ብላ መኖር አልበቃትም። በዓለም ያሉትን ነገዶች ሁሉ አሸንፋለሁ ብላ በክፉ ምኞት ተሠቃየች። ልክ የሌለው ጦር ሠበሠበችና ስመጥሩውን እጅግም ሃብታም የተባለውን የህንድን ንጉስ ለመውጋት ተነሣች። እርሡም ዛሬ ሂንዱስታን በምንለው አገር ይኖር ነበር። ይህም አገር በአሶርያ ደቡብ ምስራቅ በኩል ያለው አገር ነው።.. እጅግ ባለፀጋና ሃይለኛ የነበረ የህንድ ንጉስ አገሩን ለመውረር ሴሚራሚስ እንደመጣችበት በሠማ ጊዜ መክቶ አገሩን ለማዳን ልክ የሌለው ጦር ሠራዊት ሰበሠበ። ካርበኞችም ሌላ ደግሞ አያሌ ትላልቅ ዝሆኖች ነበሩት። የእነዚህም የታላላቆች ዝሆኖች የያንዳንዳቸው ሃይል የመላውን ወታደር ሃይል ያህላል። ጠላት ወደተሠለፈበት ገስግሶ ጠላትን በኩምቢው እያንጠለጠለ ለማምዘግዘግና በዚያም አንዳች በሚያህለው እግሩ ለመዳጥ ደህና አድርጎ ተምሯል።

- ንግስት ሴሚራሚስ ዝሆን አልነበራትምና የህንድ ንጉስ ማያሸንፈኝ አይቀርም በማለት ስለፈራች ይህን የመጣባትን መከራ ካሁን ቀደም ባልተደረገ ነገር ለመከላከል አስባ አስቀድማ 3ሺ በሮች አሣረደች። ቆዳቸው ተገፎ ዝሆን እየመሠሉ እንዲሠሩ አዘዘች። ይህም ከሆነ በኋላ በግመል እየተጫኑ ወደ ጦርነቱ ቀርበው በተደረደሩ ጊዜ በእውነት የተሠለፉ ዝሆኖች መሠሉ። ያለጥርጥር ሴሚራሚስ ይህን ሁሉ ዝሆን ከየት ስፍራ አገኘችው ብሎ የህንድ ንጉስ ተደነቀ።

ጦርነቱ እንደተጀመረ የህንድ ንጉስ እውነተኞች ዝሆኖቹን ባንድ ወገን ይዞ በቀረበ ጊዜ ንግስት ሴሚራሚስም በቆዳ የተሠሩ ዝሆኖቿን በግመል አስጭና ባንድ ወገን ፊት ለፊት በጀግንነት ተጋፈጠችው። የህንድ የጦር አርበኞች ወደ አሶራውያን ሠልፈኞች ፊት በተቃረቡ ጊዜ አንድ እንኳ የነሡን ዝሆን የሚመስል አላዩም። ከዚህ ወዲያ ፍርሃትን ወዲያ አስወግደው ወደ ንግስት ሴሚራሚስና ወደ አርበኞቿ በመናደድ ገሠገሡባቸው።

የህንድ እውነተኞቹ ዝሆኖች ግን የአሶራውያኑን ወታደሮች በኩምቢያቸው እያንጠለጠሉ ወደ አየር ያጎኗቸው ጀመር። መቶ መቶውን እየጨበጡ በእግራቸው ይደፈጥጧቸው ጀመር። እንዲህ ሁነው ያሶራውያን ጭፍሮች ከስራቸው ተነቀሉና የህንድ ንጉስ ፈፅሞ ድል አደረጋቸው። ንግስት

ሴሚራሚስ ክፉኛ ቆስላ ስለነበረ ወዲያው ከሠረገላዋ ገብታ ከመዋጊያው ስፍራ ተነስታ ሸሸች፡፡ ወደ ኋላም ሸመጠጠች፡፡ ነገር ግን በመጨረሻ በታላቅ ሃዘን አምልጣ ወደ ግዛቷ ደረሠች፡፡

ከዚህ በኋላ መኖሪያዋን በባቢሎን ቤተመንግስት አደረገች፡፡ ዳሩ ግን ከአየር የተንጠለጠለ በሚመስለው እጅግ ያምር በነበረው አታክልትዋ መታጣት ደስታ አላገኘችም፡፡ በኋላም ዙፋኑዋን ለመውረስና በህዝቡ ላይ ለመንገስ ብሎ ኒንያስ የተባለው ልጅዋ ገደላት ይባላል፡፡

የታላቂቱ ንግስት የሴሚራሚስ ፍፃሜ እንዲህ የሚያሣዝን ሆኖ ቀረ፡፡ የገዛ ህዝቧን ደስ ከማሠኘት ችላ ብላ የሌላውን አገር ድል አድርጌ ህዝቡን እገዛለሁ እያለች ዘመንዋን ሙሉ ስትመኝ መኖርዋ እንዴት ያለ ስንፍና ነው? ነገር ግን ሌላው ሊያደርግልህ እንደምትወደው አንተም እንዲሁ አድርግለት የተባለውን አልተማረችም ኑራለች፡፡" በማለት ምዕ 11ን ይዘጋል፡፡
(ዮሐንስ ወልደ ማርያም1936 ዓ.ም)

በ...ጣም በፈገግታ እንደደመቃችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምርጥ አተራረክ ነው በእውነት፡፡ "መቶ መቶውን እየጨበጹ..."አሉ ስለዚህ እዚህም መጥተው ጨብደዋል ማለት ነው፡፡ እናም ስልጣኑን እንዲሁ በፈገግታ እንደደመቅን ደስ እያለን እናስረክባለን፡፡ ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር ይሏል ይሄ ነው፡፡ ይች የማትረባ እንዴት ያለች ሆነፍ ነች? አሉ....

ወደ ጉዳያችን እንምጣ፡፡ ከላይ የተጠቀሠው ታሪክ በባቢሎናውያን ዜና መዋዕሎችም የተረጋገጠ ነው፡፡ እነ ሴሚራሚስ ነበሩ፡፡ ተከታዮች አነሠርዳናፓልም ከባቢሎን ጋር በኋላኛው ዘመን በተነሠ ነብያት ሲወሡ ነበር፡፡ ጥቂት የዘመን ከፍና ዝቆች ይኖራሉ እንጂ የህንድ ነገስታት ቅ.ል.ክ 2100-2000 ድረስ በነበረው ዘመን ገናና ነበሩ፡፡

በእነዚያ ዘመናት የህንድ ነገስታት ብርሃማ ብቻ ሣይሆን /ራማ/ በሚል /የማዕረግ ስም/ ተከታትለው የነገሡበት ዘመን ሲሆን ብዙ አገሮችን እየወጉ ማስገበር መቻላቸውም የታወቀ ነው፡፡ በዚህ መሰሉ የህንድ ጥቃት ከመካከለኛው ምስራቅ እየሸሹ ወደ የመን ተጠግተው የሚኖሩ ህዝቦች መኖራቸው የሚታመን ነው፡፡ ምክንያቱም ያች የማትረባ ሴሚራሚስ አርፎ የተቀመጠውን የህንድ ንጉስ ነካክታ ከተሸነፈች በኋላ ህንድም የባቢሎንን ትዋር ፍርስርሡን ማውጣቷ ይታወቃልና ሃያል የነበረችው ባቢሎን ከተሸነፈች ሌላው ሁሉ ለህንድ ቀላል ነበር ማለት ነው፡፡ ብዙዎችን ያስገበረው በርቀት እንደነበር የፃፉም አሉ፡፡ ይህ ጦርነት ቅ.ል.ክ 2200-2100 (እንደ ሌሎች 2000 ቅ.ል.ክ) ሲደርስ አቅራቢያ የተካሄደ ነው፡፡ ሃሙራቢ ከመንግሥቱ በፊት፡፡

ስለዚህ ተወራሪዎቹ ነገደ ዮቅጣኖች በወረራው ማግስት ባይመጡም በሽሽት ወደ ደቡብ አረብ ተጠግተው ጥቂት ዘመን ኖረው ወደ ኢትዮጵያ ባህር ተሻግረው ኑሮ የመሠረቱ ነበሩ፡፡ የባቢሎንን ስልጣኔም ቋንቋም የያዙ ናቸው፡፡ ይህ እውነታ ግልፅ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ የነገስታቱን ዝርዝር



ከማስከተላችን በፊት ለምናነሣው ጥያቄ መንደርደሪያ ይሆነን ዘንድ እንዴ እንድገመው፡፡

የብላቴን ጌታ ህሩይ "ዋዜማ" የሚለው መፃህፍ "... ከነገደ ካም ወገን በኢትዮጵያ ነግሶ የነበረው ጳአሪ 1ኛ እነዚህን ሶስቱን ነገደ ዮቅጣንን 5 አመት አስገብሯቸዋል፡፡ በኋላ ግን ራማ የሚባል የህንድ ንጉስ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ጳአሪን ወግቶ መንግስቱን በወሰደበት ጊዜ እነዚህ ሶስቱ ነገደ ዮቅጣን ከውጋዴን፣ ከአዳል፣ ከትግሬ ተላልከውና ተስማምተው በትግሬ ላይ ከነበረው ከሳባ ዘር አክናሁስን "ሳባ 2ኛ" ብለው አንግሠው ከህንድ ንጉስ ከራማ ጋር ተዋግተው ድል አድርገው ገደሉት፡፡ እነርሡም አገራቱን ኢትዮጵያን ከመገዛት ህዝቡን ከባርነት ነፃ ስላወጡ አጋዚያን ተባሉ፡፡ በግዕዝ ቋንቋ አጋዘ ማለት ነፃ አወጣ ማለት ነው፡፡ አጋዝያን ማለት ግን ነፃ የሚያወጡ ማለት ነው፡፡ አገሪቱም ብሔረ አግዓዚ ተባለች፡፡ ቋንቋቸውም ግዕዝ ተባለ" ይሉና ምንጭ ሲጠቅሡ "የሞሪዎን የመጀመሪያውን መፅሃፉን 237 ገፅ ተመልከቱ" በማለት ይመሩናል፡፡ ሲቀጥሉ "የነዚሁም አጋዓዚያን የተባሉ የነገደ ዮቅጣን ነገስታት ስማቸውና ቁጥራቸው ከዚህ ቀጥሎ የተፃፈው ነው" በሚል ሠንጠረዡን ያስከትላሉ፡፡ ጃንሞሪዮ ኩልቦ፣ ኮንቲሮሲኒ፣ ኤልቤር ካሜረር ወዘተ ወደፊት ለምናገኛቸው ታሪኮች ሁሉ ዋና መሠረት የሚሆኑን ቀደምት ፀሃፍት ናቸው፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ በሠፊው የፃፉ ናቸው፡፡ የቀደመውን የኢትዮጵያን ታሪክ የሚፅፍ ፀሃፊ ሁሉ ከእነዚህ ታላላቅ ፀሃፍት ውጭ ሊንዝ አይችልም፡፡ የፃፉት ከአገር ተወላጅ የብራና ፅሁፍና ከሌሎች አገራት ታሪክነገስትና ዜና መዋዕል፣ ከሃውልቱ.. ወዘተ በመነሣት ነው፡፡"ስለዚህ ልናመሠግናቸው ይገባል፡፡...... ወደ ጉዳያችን ስንመጣ ጥያቄው ቋንቋን መሠረት ያደረገ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

አጋዓዚያን ተባሉ፡፡ የግዕዙ ትርጓሜ ነፃ አውጪ የሚል ነው በአማርኛ፡፡ ነገዳቸው ዮቅጣን ነው፡፡ ዮቅጣን በአማርኛ ነው፡፡ በግዕዝ ዮቃጤን ይባላል፡፡ በእንግሊዝኛ የካታን ይባላል፡፡ ይህ የነገድ ስም ነው፡፡ ወይም ከሴም ዘር የወረደ አንድ ግንድ የሆነው ልም፡፡ ስለዚህ ችግር የለውም፡፡ አጋዓዚያን ያላቸው ማነው? ነዋሪው ህዝብ? ወይስ ራሣቸው "አጋዓዝያን በሉን" ብለው ነገሯቸው? ማነው በዚያን ጊዜ (ክ.ል.ክ 1985) ግዕዝ ተናጋሪ የነበረው? ከዚያ የመጡት ከሆኑ፤ እዚህ የነበሩትስ ቋንቋቸው ምን ነበር? ነው ጥያቄው፡፡

የጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ የሠፈረባቸው የታሪክ መዛግብት ሁሉ በአማርኛ የተተረጎሙትም፣ በግዕዝ የተፃፉትም ግዕዝ የመጣው ከሳባ ቋንቋ እንደሆነ ነው የሚነግሩን፡፡ ለምሣሌ የመጀመሪያው የግዕዝ አባት ሣባ ይሆንና ሣባ ግዕዝን ይወልዳል፤ ግዕዝ አሮጌና አዲስ ተብሎ የሠለጠነና ያልሠለጠነ ተብሎ ይከፋፈልና እንደገና አማርኛን ሲወልድ ነው የምናየው፡፡ አማርኛም በየጊዜው እየተሻሻለና እያደገ ሄዶ እንጂ አሮጌ አዲስ የሚባል እንደነበረው ወደፊት እናገኘዋለን፡፡ ከዓጋዚያን/ከነገደ ዮቅጣን/ መምጣት በፊት የነበረው የነገደ ካም ኩሽ ዘር የሚናገረው ቋንቋ ምን ነበር? የሚፅፍበት ፊደልስ? ስንል

ፊደልን ከስልጡን አገሮች ይዘው የመጡት ሣባውያን እንሆኑ እንረዳለን። እነዚህም ብቻ ሣይሆን በኋላኛው ዘመን በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የገቡና ነገደ ሣባ የሆኑ ከደቡብ አረብ የሚነሡ ስልጡን የሴም ነገዶች ተከታትለዋል። በዚህ ዘመን የመጡት ዮቅጣኖች ፊደል ላይኖራቸው ይችላል። ታሪኩ የተፃፈው በኋላኛው ዘመን ስለሆነ። ቋንቋቸው ግን ልዩነት ነበረው ከነዋሪው ህዝብ ጋር። ይህን ስያሜ ማንም ይስጣቸው ማን እነሡ በነበሩበት ዘመን የተሠጠ ስያሜ እንጂ የኋለኛው ዘመን ፀሃፊ "በቃ አጋዝያን እንበላቸው" ብሎ ታሪካቸውን አይፅፍም። ከዚህ አንፃር ከዚያው ከነበሩበት አገር ይዘውት የመጡት ነው ማለት ይሆናል። ቀደምት ፀሃፍትም ይሄንን ነው የሚሉን።

በኋለኛው ዘመን በመጡ የሴም ነገዶች ተከትቦ የተገኘ በርካታ የታሪክ ሠነድ እንደበረ አይተናል። እነሡ ከመምጣታቸው በፊት የነበረው የኢትዮጵያውያን ታሪክ ደግሞ በጥንቱ በግብፃውያን ፊደል የተከተበ ነው ተብሏል። እነዚህን የመሠሉ ሌሎች ነገዶች ከሠለጠኑት አገሮች ከባቢሎን፣ ከአሶር፣ ከፊንቄ (ጢሮስ) ከእብራውያን… ወዘተ ሲገቡ አማልክቶቻቸውም፣ ባህላቸውም፣ ቋንቋቸውም፣ ፊደላቸውም መሠረቱ ከተዘረዘሩት አገሮች ይሆንና ወደ ደቡብ አረብ ወደ የመን፣ ከዚያም ባህር ተሻግረው ወደ አሁኗ ኢትዮጵያ እንደገቡ ግልፅ የመሆኑን ያህል፤ ነገዳቸው ሴማዊ መሆኑ የመታወቁን ያህል፤ ስልጣኔ ቋንቋና ፊደሉም አብሯቸው እንደገባ /ይዘውት እንደገቡ/ ታምኖበታል።

የኢትዮጵያ መጠሪያ ስምና የግዛት ስፋት በአፍ ሲጠራም ሆነ ሲፃፍ ከቀይ ባህር ወዲያና ወዲህ፣ ከግብፅ ደቡብ እስከ አሁኑ ሠሜናዊ ሡዳን ያለውንና የዛሬውን ምስራቃዊና ምዕራባዊ ድንበር የሚያካትት ሆኖ፤ በሁሉም አይነት ፅሁፍ "ኢትዮጵያ" ተብሏል። በእብራይስጥ ኩሽ ሲባል፤ ኦሪት ሲተረጎም ወደፊት እንደምናገኘው ኩሽ የሚለውን በፅርዕ /በግሪክ/ አይቶፒያ ተብሎ ተተርጉሞ፣ ከግሪክ ወደ ግዕዝ ሲተረጎም ኢትዮጵያ፣ ከግዕዝ ወደ አማርኛም ኢትዮጵያ ተብሏል።

"በኋለኛው ዘመን የመጡ" የሚባል ቃል፣ ታሪክ፣ ንግግር እቃም ይሁን ቋንቋ ፊደልም ይሁን ምን ከኢትዮጵያ ጋር ሲቆራኝ ሁሌም ጥያቄ ያስነሣል፣ ሁሌም ውዝግብ ይኖራል።። ምክንያቱም ከዚህ ሄዶ ተመልሶ ስለመጣ ነው። የተባለውን ጥያቄ እናንሳና ከሡንጠረገኙ በኋላ ሌላውን እንደርስበታለን።

ጥንታዊው የሳባ ቋንቋና ፊደል ለግዕዝ አባት ነው። ግዕዙ ለአማርኛ አባት ነው። የግዕዝ አያት ማነው? አያት ነው የተባለው። ወይም ሳባ /ሱባ/ን ማን ወለደው? ይሄን በተጠየቅ እንያዘውና እንቀጥል። ሌላው የትም አይሄድም። ኩሽቲክ፣ ሴሜቲክ የሚለውንም እናየዋለን። ሣባውያን ከፊንቄ፣ ከእብራውያን አመጡት የሚለውም ቢሆን የሚያራምድ አይደለም።



<u>የዓጋዝያን ዘመነ መንግስት የነገስታት ዝርዝር</u>

<u>ከአክናሁስ ሳባ 2ኛ እስከ ማክዳ ንግስት (ከ1985-1013 ቅ.ል.ክ.)</u>

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስም ዝርዝር | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የገዙበት ዘመን ከክ.ልደት በፊት |
|---|---|---|---|
| 1 | አክናሁስ ሳባ 2ኛ | 45 | ከ1985-1930 |
| 2 | ነክሀቲ ካሊስ | 40 | 1930-1890 |
| 3 | ካስዮጲ | 19 | 1890-1871 |
| 4 | ሳባ 2ኛ (ሳባ ሻባ) | 15 | 1871-1856 |
| 5 | ኢትኦጲስ 1ኛ | 56 | 1856-1800 |
| 6 | ላክንዱን ኒዎር ኦሪ | 30 | 1800-1770 |
| 7 | ቲት ኢዎሐብ | 20 | 1770-1750 |
| 8 | ሐርሐቶር ሸኒ | 20 | 1750-1730 |
| 9 | ኢትኦጲስ 2ኛ | 30 | 1730-1700 |
| 10 | በኑካ | 17 | 1700-1683 |
| 11 | ቦኑ 1ኛ | 8 | 1683-1675 |
| 12 | ሙማዚስ | 4 | 1675-1671 |
| 13 | ኣሩአሣ | 7ወር | 1671-1671 |
| 14 | አሚን አሣሮ | 30 | 12711641 |
| 15 | ኦሪ (2ኛ) | 30 | 1641-1611 |
| 16 | ጲኦሪ 2ኛ | 15 | 1611-1596 |
| 17 | አሚን አምሐት 1ኛ | 40 | 1596-1556 |
| 18 | ፃውዕ | 15 | 1556-1541 |
| 19 | አክቲሳኒስ | 10 | 1541-1531 |
| 20 | ሚንዲስ | 17 | 1531-1514 |
| 21 | ፕሮቲውስ | 33 | 1514-1481 |
| 22 | አሞይ | 21 | 1481-1460 |
| 23 | አንኪ | 5 | 1460-1455 |
| 24 | ቦኑ 2ኛ | 2 | 1455-1453 |
| 25 | ሳቢ 3ኛ | 15 | 1453-1438 |
| 26 | ጆጎንስ | 20 | 1438-1418 |
| 27 | ሰኑካ 3ኛ | 10 | 1418-1408 |
| 28 | አንጋቦሥ 1ኛ | 50 | 1408-1358 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29 | ሚአሙር | 2ቀን | 1358-1358 |
| 30 | ክሊና (ንግስት ሳዶኒ) | 11 | 1358-1347 |
| 31 | ዘግዱር 1ኛ | 40 | 1347-1307 |
| 32 | ሐርሐቶር 2ኛ | 30 | 1307-1277 |
| 33 | ሐርቶር 3ኛ | 1 | 1277-1276 |
| 34 | ኤክቲ 4ኛ | 20 | 1276-1256 |
| 35 | ቲቶን ስትዪ | 10 | 1256-1246 |
| 36 | ሐርመንቶ 1ኛ | 1ወር | 1246-1246 |
| 37 | አሚን አምሐት 2ኛ | 5 | 1246-1241 |
| 38 | ኮንሳብ 1ኛ | 5 | 1241-1236 |
| 39 | ኮንሣብ 2ኛ | 5 | 1236-1231 |
| 40 | ስንካ 4ኛ | 5 | 1231-1226 |
| 41 | አንጋቦ /ህዝባይ/ | 40 | 1226-1186 |
| 42 | አሜን ሀስተት | 30 | 1186-1156 |
| 43 | ሐርሐር | 16 | 1156-1140 |
| 44 | ፒያንኪያ 1ኛ | 9 | 1140-1131 |
| 45 | ጥኖት ሴም 1ኛ | 17 | 1131-1114 |
| 46 | ጥኖት ሴም 2ኛ | 41 | 1114-1073 |
| 47 | ማስሐርታ | 16 | 1073-1057 |
| 48 | ራሜን ከበርም | 14 | 1057-1043 |
| 49 | ጥኖት ሴም 3ኛ | 7 | 1043-1036 |
| 50 | ሣቢ 4ኛ | 10 | 1036-1026 |
| 51 | ተዋስያ ዴውስ /አጋቦስ/ | 13 | 1026-1013 |
| 52 | ማክዳ ንግስት | 31 | 1013-982 |

**(ብላቴን ጌታ ሀሩይ ወልደ ስላሴ1921ዓ.ም)**

በአገራችን ቀደምት አፃፃፍ መሠረት በአጋዚያን ዘመነ መንግስት ስር የነገሡት የነገስታት ስም እና የገዙበት ዘመን ከአክናሁስ ሳባ 2ኛ እስከ ማክዳ ንግስት ያሉት ያየናቸው ናቸው:: ወደ ሌላ ጉዳይ ከመግባታችን በፊት አንድ ነገር ልጠቁማችሁ:: ሁሉም ፀሃፍት እነዚህን ነገስታት ሲዘረዝሩ በተራ ቁጥር 15 ላይ የሠፈረውን "ኦሪ" ብለው ነው የሚያልፉት:: የብላቴን ጌታ ሀሩይ ወልደ ስላሴ ዋዜማ ላይ ግን " ኦሪ 2ኛ" ተብሎ ነው የሠፈረው::

እንደሚታወቀው "2ኛ" ሲባል ያው በዚህ ስም ቀድሞ የነገሠ ካለ ለመለየት ነው:: "ኦሪ" ብለው 2ኛ ያሉበት ምክንያት ግልፅ ነው:: በነገደ ካም ነገስታት ዝርዝር "ኦሪ" የሚል የለም:: በራሣቸው ዝርዝር ላይ እንኳ 22 ነገስታትን ከሰብታ ጀምሮ እስከ ጲኦሪ ሲዘረዝሩ ኦሪ የሚል አላስገቡም:: ይሄን ግን 2ኛ ብለውታል:: በቅንፍ ያስገባሁትም ይህንኑ አግራሞቴን ላካፍላችሁ



ነው:: "ኦሪ" ማለት ከአዳም የዘር ግንዶች አንዱ ነው:: አዳም ሴትን ወለደ፣ ሴት ሄኖስን እያለ 9 የዘር ግንድ ዘርዝሮ 10ኛ ላይ ኖኅን እንደምናገኘው ሁሉ፤ የሁለተኛው ግንድ የሴት ቅርንጫፍ ውስጥ የሚገኝ ንዑስ የነገድ አባት ነው:: ኦሪ::

ስለዚህ በመግቢያችን ላይ እንዳየነው የነገደ ኦሪ አባት የሆነው ራሁ ኦሪ ከጥፋት ውሃ በፊት በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ስለተባለ ነው:: እሁን መረጃ ሳገኘው አልቻልኩም:: እሣቸውም ማንም አያምንም ብለው እንዳልፃፉት ነግረውናል:: እናም ኦሪ ከጥፋት ውሃ በፊት አዳም በተፈጠረ በ970 አመት በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ተብሎ ስለተፃፈ ምንም እንኳ ባያምኑበትና ባያክትቱት ከዚህኛው ኦሪ በፊት ሌላ ኦሪ መንገሡን ሣይገልፁ ማለፍ ከብዷቸው ይሄኛውን ኦሪ 2ኛ ብለውታል ማለት ነው::

ይሄን ሁሉ ትተን ነው ከኖኅ ከትናንቱ ታሪክ የጀመርነው:: ስንቀጥል በኢትዮጵያ ታሪክ የግዛት ዘመን ክፍልፋይ መሠረት ተወስኖ የተቀመጠ ነገር እናገኛለን::

1. የነገደ (ኖኅ ካም-ኩሽ) ዘመነ መንግስት
2. የአጋዚያን ዘመነ መንግስት ከክ.ል.በፊት
3. የአጋዚያን ዘመነ መንግስት ከክ.ል. በኋላ
4. የነገደ ዛጉዬ ዘመነ መንግስት
5. የሸዋ ነገስታት
6. የጎንደር ዘመነ መንግስት
7. የሸዋ ዘመነ መንግስት ተብሎ ይከፋፈላል::

የመጀመሪያውን የነገደ ካም ዘመነ መንግስት የነገስታት ስም ዝርዝር ቀደም ሲል ያየነው ነው:: አሁን ደግሞ ተተኪዎችን የአጋዚያን /ከዮቅጣን ዘር/ የወረዱትን አይተናል፣ ሌሎችንም ወደ ፊት እናገኛቸዋለን::

በብዙዎች እይታ ነገደ አጋዚያን ከገዙ በኋላ ስልጣኑ /መንግስቱ/ ከእነሁ ዘር አልወጣም:: በዚህ መፅሃፍ ደግሞ የምንቆጥረው የነገድ ተዋረድ አይደለም:: እሁን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ታሪኩን ከስሩ ለማምጣት የግድ ሲሆን (በእርግጥም አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝበት አጋጣሚ ይበረክታል) ያኔ እንቆጥራለን:: በተረፈ የኢትዮጵያን ታሪክ ነው የምናየውም፣ የምንቆጥረውም:: የኢትዮጵያን ብቻም አይደለም የአፍሪካን:: የአፍሪካን ብቻም አይደለም የጥቁሮችን፣ የጥቁሮችን ብቻም አይደለም ዛሬ ጥቁር ህዝቦች የሠፈሩባትን ምድር ወይም መሬት ነው:: ለማለት የተፈለገው ጥቁር ህዝቦች መሠልጠን የጀመሩት ስልጣኔን ከነሙች ይዘው በየጊዜው በገቡ ነገዶች መሆኑ ተደምድሟል:: በዚህ መፅሃፍ ግን ያ ሣሠት ነው:: ከዚህ የሄደው ነው ተመልሶ የመጣው የሚለውን ለማሣየት ነው የሚጣረው:: ይሄንን እውነታ በደንብ የምንረዳው 1ኛ እስካሁን ባየናቸው ታሪኮች መነሻነት፣ 2ኛ በዚህ ምዕራፍ ስር በምናየው፣ 3ኛ በቀጣዩ ምዕራፍ በምናነበው፣ 4ኛ በቀጣዩ ቀጣይ

ምዕራፎች በምንመለከተው ይሆንና ከዚያ በኋላ መደበኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ በመደዳ መቀጠል ነው። ያኔ ምንም የምንገረምበት ነገር አይኖርም። እንትን መጣ፣ እንትን ሄደ፣ እዚያ ነገሠ፣ እዚህ ነገሠ፣ እየተባለ ቢተረክ እንግዳ እንዳንሆን እንደማለት።

"አግዓዚያን ተባሉ" ቋንቋቸውም ግዕዝ ተባለ። ማን አለው? የሚለውን ጥቂት ነካክተነው እናልፋለን።

"ግዕዝ" "ግዕዝ" የሚባለውን ስም አገኘ ማለት ነው? ያ ከሆነ ቋንቋው ነበረ ማለት ነው። የሳባውያኑ ቋንቋ "ሳባ" ይባል ስለነበር ከሳባ ወደ ግዕዝ ተሸጋገረ ከተባለ ደግሞ፤ ግዕዝና ኢትዮጵያ ትውውቃቸው ቅ.ል.ክ 1985 ጀምሮ ሊሆን ነው። ይህም ሲሆን የነገደ ካም ነገስታት ከግዕዝ የተለየ ቋንቋ ነበር የሚናገሩት ማለት ይሆናል። እሡ ከሆነ ደግሞ በሁለቱም ዝርዝር ላይ እንዳየነው ጸአረ የሚሉ ስሞች አሉ።

የነገደ ካሙም፣ የነገደ ሴሙም የነገስታት ዝርዝር የሠፈረው በአማርኛ ባየነው መልኩ ነው። "God" አምላክ ነው በእንግሊዝኛ። "እግዚአብሔር" አምላክ ነው በግዕዙም በአማርኛውም። የቋንቋው ጭብጥ አንድ ነው። ሲነገርና ሲፃፍ ይለያያል። ጸአረ በአማርኛ በተፃፈ የነገደካም ነገስታት ዝርዝር ከሠፈረና ጸአረ በነገደ አጋዚያኑ ዝርዝር በዚያው በአማርኛ ከሠፈረ ምን መሆን ይችላል? ነው ጉዳዩ። ይሄም ብቻ ሣይሆን ሌሎችም ብዙ አሉ።

በነጮች ፀሃፍት እይታ እነሡንም ተከትለው በፃፉ ምሁራን አመለካከት የአሁኗ ኢትዮጵያ መስራቾች አክሡማውያን ስልጣኔን ብቻ ሣይሆን ፊደልንም ከሠለጠኑት አገሮች ከባቢሎን፣ አሶር፣ ከለዳውያን፣ አካድያን... ወዘተ እየፈለሡ ወደ ደቡብ አረብ እየተጠጉ በየጊዜው ባህር ተሻግረው በገቡ ጊዜ ያመጡት ነው። የአሁኗን ኢትዮጵያ በተመለከተ ጉዳዩን በዚህ ሲደመድሙ፤ የቀድሞዋ ኢትዮጵያ ኑብያውያን ደግሞ ስልጣኔን ከግብፅ እንደወረሡ አድርገው በመደምደም ያገጣጥሙታል። ስለዚህ ከዚያ ወደዚህ እንጂ ከዚህ ወደዚያ የሚሄድ ነገር እንደሌለ ያሣምኑናል። "እጣንና ከርቤ ብቻ ከዚህ ይሄድ ነበር" በማለት። አክሡማውያን ለምሣሌ ፊደልን በኋላኛው ዘመን ከግሪክ ሲወርሡ እናያለን። የግሪኩ ፊደል (ስልጡኑ) ኤ.ቢ..ሲ..ዲ. የኛ የአሃዝ ቁጥር መሆኑን ከደው የኛ አሃዝ ቁጥር ከእነሡ እንግሊዝኛ ሲወሠድ ይነግሩናል ያሣዩናልም። ይሄ እንግዲህ በ.. ኋላ ላይ ነው። ቁጥር የመጣው በኋላ ግዕዝ የነበረው በፊት ሊሉን አይችሉም።

በጥቅሉ የኑብያ ኢትዮጵያ ታሪክ በግብፅ ተውጦ ሲገኝ የአክሡሙ ደግሞ በግሪክ ተውጦ ይገኛል። ምክንያቱም ሁለቱ አገሮች ግራና ቀኝ ያለውን ታሪክ በየራሣቸው ፊደል እንደልባቸው ፅፈውት ስለሚገኝ ነው። ይህ የሆነው ከኢትዮጵያ የሄደውን የመጀመሪያ ፊደልና ቋንቋ የበለጠ አሻሽለው አሠልጥነው በመገኘታቸው ነው። የራሣቸውን ታሪክ አዳብረው ከፃፉ በኋላ ነው የኛን ታሪክ መፃፍ የጀመሩት። ስለዚህ እኛ የነገስታቱን ዝርዝር ስምና



የገዙበትን ዘመን ብቻ ይዘን ልንቀር ግድ ሆኗል። የግብፅን ቀደምት ታሪክ ማንም ሊክደው አይችልም። በደንብ የተፃፈ ታሪክ አላት። በዚህም ላይ አህጉሯ አፍሪካ ቢሆንም ነጮች ናቸው። እንደገናም መፅሃፍ ቅዱሱን ሊክዱት አይችሉም። ጉዳዩ የቀለም ስለሆነ ነው።

ለዚህም ነው የኛ ብቸኛ አማራጭ መፅሃፍ ቅዱሱ ብቻ ሆኖ የምናገኘው። ምክንያቱም ሌላው ነገር ሁሉ በኋለኛው ዘመን መንጋደድ ስለነበረበት ነው።

ግዕዝ አባቱ ሳባ ከሆነ ሳባ የመጣው በኋለኛው ዘመን ነው። ግዕዝ የመጣው ከእብራይስጥ/ከሂብሩ/ ከሆነ በኋለኛው ዘመን ነው። ከአብራሃም በኋላ። አምላክ ህዝቤ እስራኤል እያለ የሚነግረን ከአብርሃም በኋላ ነው። አብርሃም የኖረበት ዘመን ግልፅ ነው፤ ቅ.ል.ክ 1800። ፊደል የመጣው ከሲናው በርሐ ታሪክ ጀምሮ ከሆነ የሙሴ እድሜና የኖረበት ዘመን ይታወቃል። ቅ.ል.ክ 1300። ግዕዝ የመጣው ከባቢሎን ከአሶር፣ ከፊንቄ (ጢሮስ ወይም ሶሪያ) ከሆነ የእነዚህ አገሮች ምስረታ ግልፅ ነው። ቅ.ል.ክ 2500-2000። ግዕዝ ከግሪክ ከመጣ ቅ.ል.ክ 1500 እንዲያውም ከዚያ በታች!

ቋንቋን መናገርና መፃፍ በእርግጥ ይለያያሉ። ነገር ግን በየጊዜው የሚሻሻልና የሚታደስ እንጂ ቋንቋ ክስተት አይደለም። ስጦታ ነው፤ ይሉታል ራሣቸው። ባለፉት ምዕራፎች ያየናቸውና ስለቋንቋ ድብልቅ የሚያትቱ ታሪኮች አሁን ለምንለው ነገር ጥሩ ይሆኑልናል። (በነገራችን ላይ ይህን መሠሉን ሐተታ ማስገባት ግድ የሚለው የዚያ ሁሉ ነገስታት ታሪክ ተፅፎ ስለማይገኝና ከስማቸው በቀር ያስታቀፉን ሌላ ነገር ስለሌለ ነው። ስለዚህ ለምን? በሚለው ጥያቄ ውስጥ ፍሬ ነገር ካገኘን በሚል ነው)።

እናም ባለፉት ምዕራፎች ስናይ ገና ቋንቋ ከመደባለቁ በፊት ታላቁ መፅሃፍ "የሴም ነገዶች በየህዝባቸው፣በየነገዳቸው፣ በየቋንቋቸው እነዚህ ናቸው" "የካም ነገዶች በየህዝባቸው.." ብሎ ከነገረን በኋላ ነው "ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋ ነበረች" በማለት እንደገና ቋንቋቸው እንደተደባለቀ የሚነግረን። ለዚህም ነው እናት ቋንቋቸው አንድ ነበር ለማለት የተደፈረው። ሲበተኑ የሠፈሩባቸው ቦታዎች ሁሉ ከዚህ የሄዱ ጥቁሮች በመሠረቱት አገር ነበር። እነሡም ናቸው በባቢሎንና በዙሪያው የሚሠፍሩት። ለዚህ ነው ሄሮዱተስ "የቀድሞ ግሪካውያን ጥቁሮች ነበሩ" ያለው። ለዚህ ነው የአለም ታሪክ "እርስ በርሣቸው ለመነጋገር እየፈተኑ /እየሞከሩ/ ወደየአገሩ ጠጋ ጠጋ አሉ" የሚለን። ሲዶንን፣ ኬጤያውያንን፣ እያቡሣውያንን.. እየተባለ የሚዘረዘረው የነገድ አባት ነው። ግሪክ ሲዶን ነበረች። ሲዶን ማለት ዘረግንዱ ጥቁር ነው። ሜዶን፣ መቄዶንያ እየተባለ ነው እነጢሮስ ተከፍለው እየወጡ በዘመን ብዛት የተለያዩ አገሮች እየሆኑ ያኔ አንድ ግዛት የነበረው ዛሬ አንድ አገር የሆነው። እንደ ሡዳንና እንደ ኢትዮጵያ። አጠቃላይ ስልጣኔው ምንጩ ዛሬ ነጮች የሠፈሩበት አገር ተደርጎ እንዲታይ በሚል እንትኖች እንትን ይዘው በላይ ገቡ፣ እንትኖች እንትን ይዘው በታች ገቡ በማለት አፍሪካን ባዶ ያደርጓታል።


እንደገና ነገስታቶቻችሁ እነዚህ ናቸው ብለው ስም ይወረውሩልናል። ግዕዝ በኋላ መጣም ይሉናል። ግዕዝ ግን በኋላ የመጣ ቋንቋ አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም።

የኖኅ አንዱ ልጅ ከነገዱ የኤርትራን ባህር ተሻግሮ ሲሄድ ሌላው ልጁ በኤደን ባህረሰላጤ ሲወጣ፣ የቀረው ልጅ የዓባይን ተፋሠስ ይዟል። የካም የልጅ ልጅ የሆነው ናምሩድ ከዓባይ ተፋሠስ አልፎ ሄደ። ከነዓንም በሴም ድንኳን ሊያድር። ኖኅ እዚሁ ቀረ። ሞተም። ሁሉም በየነገዱ ፊደሉን አበጀ። የሁሉም ቋንቋ አንድ ነበር ግዕዝ። ስሩ ይሄ ነው። የግዕዝ አባት ሳባ ነው ልክ ናቸው። ያማርኛ አባት ግዕዝ ነው። ልክ ናቸው። የግዕዝ አያት ግን ግዕዝ ነው። ልክ ነን። የዛሬው እንግሊዝኛ የኛ የአሃዝ ቁጥር ነው። ሃይሮግላፊ ቢባል፣ ፒክቶግራም ቢባል፣ ላቲን ቢባል፣ ምንም ቢባል ስሩ ያው ያዳም ቋንቋ ግዕዝ ። ስለዚህ ሲመጡም ያንኑ እናት ቋንቋውን/ስሩ/ እንደ የነበረውን በኋላ የተለዋወጠውን የተደበላለቀውን፣ የተገለባበጠውን ምንም ምንም የሆነውን ብቻ ግን ከዚች ምድር የወጣውን ዋናውን ነው። ነገር ግን ስልጣኔም ከዚያ መምጣቱን ለማረጋገጥ ያመች ዘንድ ፊደልንም ከዚያ ሲመጣ ያሣዩናል። በቋንቋችን የተፃፈ ታሪክ እንደሌለ ነግረው ያዝኑልናል።

እንግዲህ በዙሪያችን ያሉት ሂብሩ፣ አረብኛ፣ ግዕዝ ናቸው። ከታሪካችን ጋር የሚገናኙት ሶስቱ ቋንቋዎች የሚለዩበትን ነገር ማጤን እውነታውን ለማረጋገጥ ይረዳል። ስሩ አንድ ነው። መለኮታዊ የተባሉ ቋንቋና ፊደሎች እነዚህ ናቸው። በዚህ አንጋጭም። ከእነግሪክ ጋር ግን እንጋጫለን። እስቲ እንዳው አሁን ማን ይሙት የትኛው ከየትኛው ተኮረጀ ቢባል ይታመናል? ቀደምቱስ የትኛው ነው? እንግዲህ ይሄ ቀጥለን የምናየው በኋለኛው ዘመን፤ አክሡሞች ሲሠለጥኑ አቅራቢያ መጣ የተባለው ነው። ምናልባትም ወደፊት ዘመኑ ላይ ስንደርስ ከታሪኩ ጋር በተያያዘ "ከግሪክ ፊደል ተኮርጆ የተሠራው የአሃዝ ቁጥራችን" በሚል ከሌሎች ፊደላት ጋር ደግመን ልናየው እንችላለን። አተራረካችንም የእውነት እንደመጣ አድርጎ ሊያሣየን ቢችል ግር መሠኘት የለብንም። እውነታውን ከወዲሁ እንይና በኋላ ላይም "መጣ" እያልን እናውራው። ከተክለፃድቅ መኩሪያ መፅሃፍ ያገኘሁትን ነው። የእጅ ፅሁፉም የራሣቸው ነው። እሣቸው ለማሣየት የፈለጉት ከግሪክ መምጣቱን ለአንባብያን ለማመልከት ነው። የዚህ መፅሃፍ አጠናቃሪ ደግሞ ተቃራኒ ነው። ከሠንጠረዡ በላይ የሠፈረችው ቁንፅል ሃተታም ማን ምን ተረድቶ ምን እያስረዳን እንዳለ ታስረዳናለች!

እያችሁ? ይሄ እንግዲህ ገና ገና በኋላ ላይ ተወረሠ የተባለው ነው። እንጂ እነዚህኞቹ ነገደ አጋዚያን ያመጡት የወረሡት አይደለም። በየጊዜው የገቡ ሌሎች አሉ። ነገደ ሃበሳን.... ወዘተ እየተባሉ ከደቡብ አረብ የገቡ። የፊንቂን፣ የአራማይክ፣ የእብራውያን.. የወዘተ ስልጣኔ ይዘው መጡ የሚባሉ።




[illegible]

| የግሪክ ፊደል | [illegible] | [illegible] |
|---|---|---|
| Α | ፩ | አንድ |
| Β | ፪ | ሁለት |
| Γ | ፫ | ሦስት |
| Δ | ፬ | አራት |
| Ε | ፭ | አምስት |
| ϒ | ፮ | ስድስት |
| Ζ | ፯ | ሰባት |
| Η | ፰ | ስምንት |
| Θ | ፱ | ዘጠኝ |
| Ι | ፲ | አሥር |
| Κ | ፳ | ሐያ |
| Λ | ፴ | ሠላሳ |
| Μ | ፵ | አርባ |
| Ν | ፶ | ሃምሳ |
| Ξ | ፷ | ስልሳ |
| Ο | ፸ | ሰባ |
| Π | ፹ | ሰማንያ |
| Μ | ፺ | ዘጠና |
| Φ | ፻ | መቶ |

የእብራውያን.. የወዘተ ስልጣኔ ይዘው መጡ የሚባሉ።

ለማንኛውም ነገደ ዮቅጣን ወይም አጋዚያን የተባሉት የገቡበት ዘመን ያየነው ሲሆን፣ ከዚህ ዘመን በፊት ወደ ኢትዮጵያ የገባ ነገደ ሴም አልነበረም። ከተጠቀሠው ጊዜ በኋላ ግን በየጊዜው አዳዲስ ስልጣኔ እየያዙ ይመጡ ነበር።

ቋንቋ፣ፊደል፣ የአሃዝ ቁጥርን... ወዘተ በሚመለከት ወደፊት የምናገኛቸው እንዳሉ ሆነው፤ ነገር ግን ከወዲሁ መገንዘብ የምንችለው ወይም የሚኖርብን ቀደም ሲል በሌላ ምዕራፍ ስዕላዊውን ፊደል መሠረት ያደረገው ግኝት እንዴት ወደ ኮፕት እንደተለወጠና ከግሪኩ እንደተቀላቀለ፣ ከዚያም በምን እንደተተካ፣ እንደገና ደግሞ በኋለኛው ዘመን ያ የግሪኩ ፊደል ተመልሶ በሌላ አቅጣጫ እንዴት ሲመጣ እንደሚችል ነው።

በተረፈ.. ለምሣሌ በሂብሩ ቁጥር ሲቆጠር "ኤሐድ" አንድ ማለት ነው "አሀዱ" በኛ በግዕዝ አንድ ማለት ነው። "አንድ" በኛ አማርኛ "አንድ" ማለት ነው። በትርግኛም ያው ነው። ይሄ ሁሉ በሴማዊ ስሌት ነው። በኩሽቲክስ? ስንል አሁንም በኋለኛው ዘመን ፊደሉ ላቲን ሆኖ ይገኝና

ምንጩ ከወደ አፍሪካ ቀንድ አገሮች የፈለቀ ያደርጉታል። ስለዚህ አሁን የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑት ውስጥ ቋንቋቸውን ሲፅፉ በላቲኑ/ባሁኑ እንግሊዝኛ/ ቢፅፉ ያው የግሪኩ ፊደል መሆኑ ነው። ይህም ሲሆን የኩሽ ነገዶች ፊደል ሁሉ ከነጭ የመነጨ ይሆናል ሊባል ነው። አህዱ፣ኪሉቱ.. የሚለው ኤ.ቢ..ሲ..ዲ ከሆነ ብዙ ነገር ማለት ይቻላል። እኔ የቋንቋ ሊቅ አይደለሁም። ዓለማዬ መጠየቅ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ በቋንቋና በፊደል ሚስጥራት ታጅሎ ያለ ነውና እውነት ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ በዘመናዊና በሳይንሣዊ የአጠናን ዘዴ "ያገራችን ሊቃውንት" ለማጥናት ቢሞክሩ ለማለት ነው።

በተረፈ "ዞሮ ዞሮ መግቢያው ጭራሮ" እንደሚባለው ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ የቋንቋ ሊቃውንት ወይም የቋንቋ ጠበብት "ኩሽቲክ፣ ሴሜቲክ".. እያሉ ከፍለውታል። "ያፌቲክ" ለምን አይሉም ታዲያ?

ከዚህ በላይ ጥያቄ የለም። ከዚህ በላይ መልስም የለም።

በጣም በሚገርም ሁኔታ "ባለታሪክ ኢትዮጵያ" የተሠኘው የነጋ ወልደ ስላሴ መፅሃፍ በገፅ 43 እንዲህ የሚል ነገር ተካቶበታል። "... የግሪክ አፈ ታሪክ እንደሚለው ከሆነ "የተቃጠለ ፊት ያላቸው ሠዎች አገር" ለሚለው አነጋገር ትርጉም ሲሠጥ "ወራሪ ጠላት ገብቶ አገሩንና ንብረቱን ከመውሠዱ በፊት በአካባቢው ያለውን ንብረት ሁሉ ማውደም ማለት ነው ይላል። የዚህ ትርጉም ስሜት የቀድሞዎቹ ግሪካውያን ስለ ኢትዮጵያ ከሚያውቁት ግንዛቤ ጋር ሲነፃፀር ፍችውን ይበልጥ ውስብስብ ከማድረጉም በላይ አንዱ ደራሲ እንዳስቀመጠው ጥንታዊያን ግሪኮች ስለዚህ አገር /ኢትዮጵያ/ የነበራቸው ግንዛቤ ጥልቅ ካለመሆኑም በላይ በተረታዊ ዘይቤዎች ላይ የተመሠረተ ነበር። ዘመናዊ የታሪክ ምርምር ዋና ዋናዎቹን የኢትዮጵያ ታሪክ ርዕሶች ሊያስጨብጠን የሚችል ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ወሠንና መጨረሻ ወደ ሌለው ወደ ግብፅ ታሪክ ማምራቱ አይቀርም።..." ፀሀፊው ማኔቶን ይጠቅሳሉ። ማኔቶ የሄሮዱተስን ፅሁፍ ለማሻሻል የሞከረ ቅ.ል.ክ 300 ላይ የነበረ ነው።

በእርግጥም እንሄሮዱተስ፣ ሆሜር... ወዘተ ቀደምት የግሪክ ባለቅኔዎችና ታሪክ ፀሃፊዎች "ኢትዮጵያውያን መልካቸው ያማረ ቅኖች.." እያሉ የማወደሣቸውን ያህል በልዩ ልዩ ነገድ ተከፍሎ የሚገኘውን ህዝብ "በዋሻ የሚኖሩ፣ ውሻ የሚያረቡ፣ አራት ማዕዘን ፊት ያላቸው፣ ያሞራ ጭንቅላት..." እያሉ ያካተቱበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን የኋለኞቹ ታሪክ አሣማሪዎች በሃቀኛ ፀሃፊዎች በእንሄሮዱተስ ፅሁፍ ላይ ሌላ ነገር ላለመጨመራቸው ምን ማስረጃ አለ? ምንም። እንዲህ የሚያወዛግቡን ያለነገር አይደለም።



እንዲያውም ከዚሁ መፅሃፍ አንድ ነገር ጨምረን እንለፍ "ስለጥንታዊ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ለማጥናት አጋጣሚው ችግር ስለዚህ ጉዳይ የሚያብራሩ ደንበኛና ማስረጃ የጨበጡ ፅሁፎች በቅርብ አለመገኘታቸው ሲሆን ቢገኙም አብዛኛቹ በግብፃውያን፣በእስራኤላውያንና በሶርያውያን የተዘገቡ ናቸው" ( ነጋ ወልደ ስላሴ1985 ዓ.ም) የሁሉም ብሶት ይሄ ነው። የት ሄደ ያ ሁሉ ታሪክ? ያሠኛል። ታሪኩን ሁሉ አውድመው መልሠው የተቃጠለ ፊት እያሉ በሚስጥር ማንነታችን ይነግሩናል ማለት ይሆን?

"... ሱማ! አካ ሱማ፣ የተባልከው እንደ አግሡማ... ለካ አንተ ነህ..." ይላል የሎሬት ፀጋዮ ገብረ መድህን ቅኔ። በአፍሪካ ቀንድ ብትሄዱ በአፍሪካ ጅራት በኋለኛው ዘመን የተተበተበ ሴራ እንጂ ነገርየው ሁሉ ከዚህ ወደዚያ፣ከዚያ በኋላ ከዚያ ወደዚህ ነው። ዛሬ አንዳንዱ ያወቀ እየመሠለው "የኔ ቋንቋ ላቲን ነው" ይላል። ልክ ይሄን ሲል ታሪኩን ከነቫስኮ ደጋማና ከእነ ፈርናንዶ ምንትስ ቅብጥርስ ጉዞ ጋር በተያያዘ የተገኘሁ ነኝ ማለቱ ሊሆን ነው። እነሡም ከዚያ ፊልሣችሁ ስትመጡ የኛን ቋንቋ ይዛችሁ ገባችሁ ይላሉ። እኛ ደግሞ የኛን አሻሽላችሁ መለሣችሁት እንላለን። ቀጣዩን ምዕራፍ ስንቀጥል ተቀጣጥሎ እናገኘዋለን።

# ምዕራፍ ፮

# የኢትዮጵያ ትክክለኛ መጠሪያ ስም

አንባብያን የመሠላችሁን መርጣችሁ ትይዙ ዘንድ ስለኢትዮጵያ መጠሪያ ስም የተለያዩ ፀሃፍት ያሉትን አሠፍራለሁ። ከዚያ ወደ ዋናው ጉዳይ እናልፋለን።

ዛሬ በአንድ ኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊ ስም የሚታወቀው የአገራችንና የህዝቦቿ/የነገዶቿ/ ስያሜ የቀድሞ መጠሪያዎች በርካታ ነበሩ።

በኦሪት ዘፍጥረት እንደተቀመጠው የኖህ ልጆች ሴም ካም ያፌት መሆናቸውን፤ የካም ልጆች ኩሽ ሚፅራይም፣ ፉጥ፣ ከነዓን መሆናቸውን እንደሚገልፀው፤ የኩሽም ዘር ተራብተውና በርክተው ከዛሬው ሡዳን ጀምሮ እስከኤርትራ ባህር ድረስ ያለውን አገር ይዘው ይኖሩ ነበር። ስለዚህም ቅ.ል.ክ ከ3000-1000 ዓመታት መካከል ካሉት ጊዜያቶች ጀምሮ ግብፆች በሐውልታቸውና በፓፒረስ/በልጥ ብራና/ ፅሁፋቸው ላይ እንደፃፉት ኢትዮጵያን ብዙ ጊዜ የኩሽ አገር፣ አንዳንድ ጊዜ የፑንት አገር እያሉ ይጠሩት ነበር።

ኩሽ ሲሉ ያው የነገድ አባትን ስያሜና የዘሮቹን መኖሪያ ምድር መሠረት አድርገው ነው። አባ ጋስፖሪኒ ደግሞ ፋጥ የሚለውን ጹጥ ካሉ በኋላ ፑንት አሉት ይሉናል። አንዳንድ ጊዜም የደቡብ ምድር ወይም የነህሴ አገር እያሉ ሲጠሩት ኖረዋል። ፑንት የሚባለው አገር ከሠሜናዊ ኢትዮጵያችን ጀምሮ እስከ (ኤልማንደብ) የየመንንም ግዛት የሚጨምር ነበር። የሚሉን ደግሞ ተክለፃድቅ መኩሪያ ናቸው። ነህሴ ማለት ደግሞ ከነገደ ካም 8ኛው ንጉስ ተብሎ የተመደበ ስለሆነ በመሪው ስም የነህሴ አገር ማለታቸው ነው።

በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 12 ቁ 42 ላይ እንደሚገኘው ደግሞ "... ንግስተ አዜብ ይህን ህዝብ ለመፋረድ ትነሣለች ... የሰለሞንን ጥበብ ለማየት ከምድር ዳር መጥታለችና ..." የሚለውን በኛ በግዕዝ ቋንቋ አዜብ ማለት ደቡብ (በደቡብና በምዕራብ መካከል የሚገኝ) ማለት ነው። ይህም ጥንታዊ ግብፆች "የደቡብ አገር" ከሚሉት ጋር ይገናኛል።

የሆነ ሆኖ ግብፆች የኩሽ ህዝብ የሰፈረበትን አገር የደቡብ አገር፣ የኩሽ አገር፣ የፑንት አገር እያሉ ጠርተውታል። የሴም ዘሮች መጥተው ከተቀላቀሉ በኋላም የሰፈሩበትን የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ክፍል በቀድሞ መጠሪያው ፑንት እያሉ ነበር የሚጠሩት። ሌሎች ደግሞ እንደዛሬው አጠራራችን ኢትዮጵያ በማለት ሲጠሯት እንደኖሩ እናያለን።

አቢሲኒያ የሚለው ደግሞ የኩሽ የልጅ ልጅ በነበረው (በናምሩድ ልጅ) በአቢስ ስም የተሰየመ ነው።



ግሪካዊው ሊቅ ሆሜር (ቅ.ል.ክ. ከ1000-900 የነበረው) በኤልያድ (ስ) በምዕራፍ 5 በተለይ ኢትዮጵያ እያለ ደጋግሞ ይጠራል። የታሪክ አባት የተባለው ሄሮዱተስ (ቅ.ል.ክ. 500-400) ኢትዮጵያ ይላታል።

ከእስራኤሎችም ወገን ተመሣሣይ አጠራር እናገኛለን። ቅ.ል.ክ. 1100 ላይ የነበረው ዳዊት በመዝሙሩ ኢትዮጵያ ሲል በ700ኛው ቅ.ል.ክ. የነበረው ኢሣያስ ደግሞ በትንቢቱ በምዕራፍ 18 እና 11፣ ሶፎንያስ በምዕ.3 ቁ. 10 "የኩሽ አገር እያሉ ነው የጠሯት። መሠላቸው እምባቆም ደግሞ በምዕ.3 ቁ. 7 ላይ መልሶ ኢትዮጵያ ይላታል። እነዚህ ሁሉ ቀደምት ነብያትና ፀሃፍት ለእስራኤል ልጆች ተግሣፅና ምክር ወይም ለአምላካቸው የፀሎትና የምስጋና ቃል ሲያቀርቡ እግረ መንገዳቸውን የአገራችን ጉዳይ ሲያጋጥማቸው አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያ በሌላ ጊዜ የኩሽ አገር እያሉ ሲጠሩት ኖረዋል።
በኋለኛው ዘመን ደግሞ የሴም ዘሮች ነገደ ሳባና ነገደ ዮቅጣን ከደቡብ አረብ የኤርትራን ባህር እየተሻገሩ ከካምና ከኩሽ ዘር ጋር ተደባልቀው በተቀመጡ ጊዜ በስም ላይ ስም እየበረከተ ሄዷል።

ምንም እንኳን የቀድሞዎቹ እስከ ኑብያ መንግስታቸውን /ግዛታቸውን/ አስፍተው የኩሽ አገር እየተባሉ ቢቀመጡ የተቀላቀሉት የሴም ዘሮችም በዚያው መጠሪያ ሲጠሩ ቢኖሩም፤ በስልጣኔ፣ በፅሁፍ፣ በልማድና በጥበብ ሁሉቱም ነገዶች የሚለያዩበት ሁኔታ ቢፈጠርም፣ መደባለቃቸው ግን ግድ ነበርና አንድነትም ልዩነትም ነበራቸው ይሉናል።

‹‹በኋላ ግን ነገደ ዮቅጣን ነገደ አግኣዚ አጋዝያን፣ አገሩን ብሄረ አግዓዚ፣ ቋንቋቸውን ልሣነ ግዕዝ ብለው ከኩሽ ዘር ለመለየት ሞክረዋል።›› ( ተክለፃድቅ መኩሪያ 1951 ዓ.ም )

ዓረብ መታወቅ ከጀመረ በኋላ ደግሞ በንግግሩም በጽሑፉም ሐበሻ /ድብልቅ/ ብሎ ይጠራናል። መደባለቆችን ለማመልከት ነው ተብሏል።

ሐበሻ ሲሉን የቻሉበት ሌላው ምክንያት ደግሞ በዛሬው ምዕራብ የመን የሚገኘው የአገሩ ስም ሀበሳት፤ ሠዎችን ሀበሳን የተባሉት "ሃበሳ" ከሚባል የነገድ አባት የወረዱና ከአገራቸው ተሻግረው በኢትዮጵያ ሠሜን ስለተቀመጡ ሃበሳ የሚለው መጠሪያቸው ሆነ፤ በማለት በሳባውያን ፊደል "ሳ" የነበረው በአረብኛ "ሳ"በ"ሻ" ተለውጣ "ሃበሻ" የሚለውን መጠሪያ አገኙ ይሉናል።

በሌላ በኩል በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት ምዕ. 10 በኖኅ ዘር ውስጥ ሁለት ሳባ እንዳለ እንረዳለን። አንደኛው የኖህ የልጅ ልጅ ኩሽ የወለደው ሳባ ነው። ነገር ግን ከሌላው ለመለየት ሳባኖባ ይሉታል። ይህ የካሙ ገነድ የኑብያው ኢትዮጵያ የነገድ አባት መሆኑ ነው። እናም ሳባኖባ ሲገዛ ግዛቱን በስሙ ኑብያ ብሎ እንደሰየመ ይነገራል። ይህም በነገደ ካም የነገስታት ዝርዝር ውስጥ 10ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያየነው ነው።

ሁለተኛው የሳባ ትውልድ ደግሞ ኖኅ የካምን ወንድም ሴምን፣ ሴም አርፋክድስን አርፋክድስ ሳላህን፣ ሳላህ ኤቦርን፣ ኤቦር ዮቅጣንን፣ ዮቅጣን ሳባን ይወልዳል።

ይህን የዮቅጣንን ልጅ ሳባ ሻባ ይሉታል። እርሱም በነገደ አጋዝያን የነገስታት ዝርዝር ውስጥ ተራ ቁጥር 4 ላይ ሰፍሮ ያየነው ነው።

ሳባሻባ ወይም የሴም ዘር ግንድ የሆነው የኢትዮጵያ ገዥ ከገዛ በኋላ በእርሱ እግር የተተካው በዝርዝሩ 5ኛ ላይ የሰፈረው ኢትኦጵስ 1ኛ ደግሞ ግዛቱን ኢትዮጵያ ብሎ ሰየመ ይባላል።

በእነዚያ ዘመናት በአሁኒቷ ኢትዮጵያ የሚገኙት አግዓዚ ወይም ሃበሳን የሚባሉት የአሁኗን ኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ይዘውና ጠብቀው ሲኖሩ ቀደም ሲል የነበሩት ነገደ ካም /ኩሽ/ የሚባሉትም በኑብያ ኢትዮጵያና በአሁኗ ኢትዮጵያ መኖራቸውን ቀጠሉ።

በዚህና በዚህ መሰል መልኩ የኢትዮጵያ መጠሪያ ስም የተለያየ እንደነበር እንረዳለን። ባጠቃላይ በመጀመሪያ በኩሽ፣ ቀጥሎ በናምሩድ ልጅ አቢስ አቢስኒያ ከዚያም በሳባ ኖባ ስያሜ ኑብያ ... ወዘተ... እየተባሉ ሲጠሩ ቆይተው የሴም ዘሮች ውስጥ ነገደ አጋዝያን ከመጡ በኋላ ደግሞ ከእነሱ አንዱ በሆነው በኢትዮጲስ 1ኛ ኢትዮጵያ ተብላ መሰየሟና በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ በገቡት ነገደ ሃበሳን... ወዘተ ሲባሉ ሃበሻ የሚለው መጠሪያ እንደመጣ ነው የሚታመነው።

በዚህ መፅሃፍ አጠናቃሪ እይታ ከላይ የተዘረዘሩት የተለያዩ የኢትዮጵያ መጠሪያ ስሞች (ከሁለቱ ውጪ) መጤ ናቸው። ወይም መሰረት የላቸውም። ስራቸው በሚገባ የተጠና አይደለም።

ይህ ማለት ግን ለምሳሌ "ፑንት" በሚለው ስም አንድ ታሪክ ተፅፎ ቢገኝ ኢትዮጵያን ለመግለፅ ተብሎ የተፃፈ መሆኑን እንክድም። "ኑብያ" ተብሎ በተጠራና በተፃፈ ጊዜ የኢትዮጵያን ግዛት እየገለፀ እንደሚገኝ እንክድም። "ሃበሻ" በሚል ቃል ታሪካችን በሆነ ቦታ ሰፍሮ ቢገኝም እኛን እንደሆነ አንክድም። አቢሲኒያ ቢሉንም እንሰማቸዋለን።

የኛ ጉዳይ ሌላ ነው። የኢትዮጵያ የመጀመሪያው መጠሪያ ስም፤ ስሩ፣ ምንጩ የቱ ነው? የሚለው ነው። ምክንያቱም ያየነው ስያሜ ሁሉ፤ ሁሉም የየራሱን አገር መስርቶ መሰልጠን፣ መፃፍ፣ ማዩል ከጀመረ በኋላ ነው የተኘርጎደጎደው።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ፀሃፍት ዘንድ በተለያየ አጠራርና ስም ስትጠራ መኖሯ እንዳለ ሆኖ በዋናነት በኦሪት ላይ "ኩሽ" ተብላ ሰፍራ እናገኛለን። ከዚህ በኋላ 70 ሊቃውንት በጋራ ሆነው ብሉይን ከእብራይስጥ ወደ ፅርዕ /ግሪክ/ ሲተረጉሙ "ኩሽ" የሚለውን ቃል/ከግብፅ በስተደቡብ ያለውን አገር ሁሉ ለመጠቆም ይጠቀሙበት የነበረውን የነገድ አባት ስም/ "አይቶ ፒያ" ወይም "Aithio - Pia" ብለው ተረጎሙት።



ይህንኑ ወደ ግዕዝ ሲተረጉሙትም ቃሉን ብቻ እንደወረደ "ኢትዮጵያ" ብለው አሰፈሩትና ከግዕዝ ወደ አማርኛ ሲተረጎምም እንደገና ያለፍቺ ሆኄውን ብቻ "ኢትዮጵያ" አገሯን፤ ህዝቡን "ኢትዮጵያዊ" አሉት።

የቃሉ ስረ መሰረት የት ነው? ሲባል ግሪክ ሆነና ትርጓሜውስ? ተብለው ሲጠየቁ "በፀሃይ የጠቆረ፣ በፀሃይ የተቃጠለ ፊት ያላቸው ..." ብለው የነገሯቸው ወይም የዋሹዋቸው ብሉይ ከሂብሩ ወደ ፅርዕ በተተረጎመበት ዘመን ቅ.ል.ክ. 282 ላይ ነበር። Aithio — Pia የሚሉት እነዚህ ሁለቱ ቃላቶች "አይቶ" ጥቁር፣ አደረገ፣ አቃጠለ፣ የሚል ትርጉም ሲሰጥ "ኦፕያ" ወይም "ኦጵስ" ፊት የሚል ትርጉም ይይዝና ነዋሪዎች ፊታቸውን ፀሃይ ያቃጠለው በሚል ፀና። አንዳንዶችም ሲራሩልን ጠይም ለማለት ነው ይሉናል።

በዚህ ምዕራፍ ይህን ቀልማዳነት አፍርሰነው እናልፋለን።
በዚያ ባልሰለጠነው የግሪክ ፒክተግራም ሆሜር በኤልያድ/Iliad/እና በodyssey ላይ "በኢትዮጵያ የሚኖሩ ህዝቦች እጅግ ሃያላን እጅግ የሚያምሩና የተከበሩ ናቸው። ..." ይላል፤ በመዝሙሩ ቁ 423 ላይ። "የአማልክት አባት ዜውስ ሃያላኑን ኢትዮጵያውያንን ለማየትና አብሯቸው ምግብ ለመብላት/ማዕድ ለመሳተፍ/ ወደ ታላቁ ወንዝ ይወርዳል..." እያለ የተረከው ቅ.ል.ክ. ከ1000-900 ባለው ጊዜ መካከል ነበር። ያኔ "አይኦቶፒያ" "Aiotopia" ተብሎ የሚነበብ ያልሰለጠነ ፊደል ነበር የነበራቸው።

የኋለኛው ዘመን ግሪካዊ ሊቅ ሄሮዱተስም ቅ.ል.ክ. 490 ላይ የተወለደው "ኢትዮጵያውያን ወይም የኢትየጵያ ነዋሪዎች ከሰዎች ሁሉ የተዋቡና ታላላቆች፣ ቁመናቸው ያማረ ሃያላን ናቸው ..." ይላል 3ኛ መፃህፍ ም.20 ቁ. 114

ይሄ ሁሉ በቀድሞው ባልሰለጠነው ፊደልና ቋንቋ ውበትን ለመግለፅ ሲጠቀሙበት የኖሩት ቃል ነው።

ቀደም ሲል የኒጋ ወልደስላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ ገፅ 45 ላይ ያየነውን አንድ አንቀፅ እንድገመው፡- "የግሪክ አፈ ታሪክ እንደሚለው ከሆነ "የተቃጠለ ፊት ያላቸው ሰዎች" ለሚለው አነጋገር ትርጉም ሲሰጥ "ወራሪ ጠላት ገብቶ አገሩንና ንብረቱን ከመውሰዱ በፊት በአካባቢው ያለውን ንብረት ሁሉ ማውደም" ማለት ነው ይላል" በማለት የእንሄሮዱተስ ፅሁፍ ላይ የራሱን ፅሁፍ ጨመረ የተባለውን ማኔቶን ጠቅሰው ጠቁመውናል። ማኔቶ ቅ.ል.ክ. 300 ላይ እንደነበረም አይተናል። ምንም እንኳ ይህ መፅሃፍ ከዚህ ያለፈ ነገር ሊነግረን ባይችልም ለኛ በቂ ነው።

ይህ ወቅት ማለትም ቅ.ል.ክ. 300 ማለት አስገራሚ ዘመን ነበር። ታላቁ እስክንድር ታላቅ የተባለበት ዘመን፤ ግብፅን ያስዋበበት ዘመን፤ የእስክንድርያን ከተማ በስሙ ሰይሞ 24 ሰአት መብራት የሚበራባት ከተማ አድርጎ ያሸበረቀበት ዘመን... ነበር። እስክንድር ያልያዘው ኢትዮጵያንና ህንድን ብቻ ነበር። ነገር ግን እሱ የሞተው በ323 ነበርና የጦር አለቆቹ

ግዛቱን ሲከፋፈሉ /ገድለውታልም ይባላል/ ከእሱ ዓላማና እቅድ ውጪ የሆነ ተግባራትን እንደፈፀሙ ታሪክ ይነግረናል።

እስክንድር የሆሜር ፍፁም አድናቂ እንደነበርም ይታወቃል። ኢትዮጵያንም የሚያውቃት እነሆሜር በፃፏትና ባዩባት አይን መሰረት መሆኑ ግልፅ ነው። በጥቅሉ እስከእርሱ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ የተዛባ ትርጉም አልነበራትም።

የሆነ ሆኖ ከእርሱ ሞት በኋላ ታሪክ ተለዋውጧል። እናም ያ ዘመን የኑብያ ኢትዮጵያው ፊደል ከዲሞቲክ የህዝብ ፊደል የተቀላቀለበት፣የአዶሊስ ወደብ የተሰራበት፣ ወደቡ ከእስክንድር ተከታዮች አንዱ በሆነው በኘቶሎሚ /በጥሊሞስ/ ስም የተሰየመበት፣ አክሱማውያን መግነን መታወቅ የጀመሩበት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ ወደብ የተሰራበት፣ በግብፅ ጥንታዊው ፅሁፍ ቀርቶ "ኮፕት" ተግባራዊ የተደረገበት፣ የአሃዝ ቁጥርን ለመጀመሪያ ጊዜ ከግሪክ ፊደል ወረሱ የተባለበት/እንደ እውነቱ ከሆነ ዳግም የተፈጠሩበት/ ታሪካቸውን በግሪክ ቋንቋ መፃፍ የጀመሩበት፣ በደቡብ አረብ በየመን የእነ ዜውስ ጣኦት የተተከለበት ... ዘመን ነበር።

ማኔቶ ግሪካዊ ሆኖ ሣለ የግብፅ ካህን የሆነበት ዘመን ነው። ደራሲም ነው፣ ፈላስፋም ነው፣ ታሪክ ፀሃፊም ነው፤ አፈታሪክ የሆነውን ነገር... ያውቃል። የእነሄሮዱተስን ፅሁፍ የማሻሻል፣ የመጨመር ብቃትም እውቀትም ስልጣንም ነበረው። የግሪክ አዲሱ መዝገብ ቃላት የተዘጋጀበት ዘመን ነው። ኑብያም የተያዘችበት ዘመን ነው።

እስክንድር ግን "የአማልክት መቀመጫ፣ የእነዜውስ አገር" እየተባለች በእነ ሆሜር የተገለፀችውን አገር በጦር መያዝ አልፈለገም። ግብፅን ከያዘ በኋላ እንኳ ኑብያን አልነካም። ይልቁንም ከልጅነቱ ጀምሮ ያስተማረው አርስቶትል በመከረው ምክር መሰረት የዓባይን ምንጭ አስመረመረ እንጂ። በኋላም መጥቶ ለኢትዮጵያዊቷ ንግስት የአክብሮት ሰላምታውን አቀረበ እንጂ። ስለዚህ ... የትርጉም ለውጥ ... ማለትም ማውደም ማቃጠል ... የሚለው እግረ መንገዱን ... የተቃጠለ ፊት ... ወዘተ እየተሰኘ ተሻሻለ እንጂ ጥንትማ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ነበረች። አፈታሪኩን ይዘን አይደለም ይህን ያምነው። እሱን እንደ አንድ ተጨማሪ ማዳበሪያነት እየተገለገልንበት ነው። ገና አልጨረስንም።

"ኢትዮጲስ 1ኛ" "ኢትዮጲስ 2ኛ" የሚለው ስም ግሪክ ከመታወቋ ሺ አመት ቀድሞ እዚህ የነገስታት መጠሪያ ስም የነበረ ነው። "ኢትዮጲስ" በአማርኛም፣ በግዕዝም፣ በሱባም በእንግሊዝኛም፣ በምንም ቢለዋወጥ ያው ኢትኦፒስ ነው። ያው ነዋ! የአገሪቱ ስም ትርጉሙ በግሪክ ብቻ ከተገኘ ንጉስ ኢትኦጲስ ከግሪክ የወሰደው ስም ነው? በአማርኛ በኋለኛው ዘመን ተለውጦ ነውንጂ የንጉስ ኢትኦጲስ ስም ትርጉሙ "የተቃጠለ ፊት ያላቸው ህዝቦች ንጉስ" ሊባል ነው?



የአክሱም ታሪክ ወደ ፊት እንደምናገኘው በየሃውልቱ ላይ ግሪክኛ ፊደል ተፅፎባቸውና እነሱው መረጃ ሆነው ስለተገኙ ብቻ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ፊደል አወራረስንም ሆነ፤ ቁጥር አኮራረጅን ሊወስኑ አይችሉም። ያ ከሆነ ኢትዮጵያ የ1600 አመት ታሪክ ይኖራታል።

የግዕዝ ቋንቋ ግን በአጋዝያን ዘመን ነበረ፤ በግዕዝ የተፃፈ ሰነድም ሞልቷል። የአሃዝ ቁጥርም ነበራቸው፤ አራትም ገብቷል ... ወዘተ። ኢትዮጵያም ቋሚ ስም፤ ትርጉም ያለው ስም ነበራት።

"ኢት– ስጦታ፣ ዮጵ ብሜ ወርቅ ወይም እንቁ፣ ግዮን ፈሣሽ ወንዝ፣ በጥቅል ኢትኦጵግዮን "የግዮን ወርቅ ስጦታ ተብሎ በሱባ/በሳባ/ ይተረጎማል" ለመሪ ራስ አማን በላይ እናጨበጭባለን። /መፅሃፈ አብርሂት 1999 ዓ.ም/

እኛ ጥሩ ጥሩውን ወደኛ እያመጣን አይደለም። በእውነቱ ከላይ የታተቱት ሃተታዎች ሁሉ ግጼታ ሆነው አይደለም። "ኢትኦጵ" የሚለውን ብቻ አስፍሮ "የግሪኩን እርሱት" ብሎ ተክቶ ማለፍ ይቻላል። ነገር ግን ይህቺ ሀገር በራስዋ ቋንቋ ትርጉም የሚሰጥ ስም የነበራት አገር መሆኗንና ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ምንጩም ፍንጩም ከግሪክ አለመሆኑን ገልጾ ለማለፍ ሲባል ነው። መፍረስም ይኖርበታል።

"ኢትዮጵያ ማለት" ብለን በመጀመር ተወራርሶ ሲቀመጥ እንዴት እንደሚሆን ማደራጀት ሳይኖርብን አይቀርም። ኢትዮጵያ ማለት በትክክለኛው፤ ፍፁም በጠራው አገላለፅ ባሁኑ "ኢት–ዮጵ" የአማርኛ አባት በሆነው በግዕዝ "ኢትዮጳግዩን" የግዕዝ አባት በተባለው በሳባ "እንቅዮጳዝዮን" ቋንቋ ከመከፋፈሉ በፊት በኖኅና በቤተሰቦቹ ዘመን ኩሽቲክ ሴሜቲክ ተብሎ ከመከፋፈሉ በፊት በነበራት ስያሜ "እንቅዮጳዝዮን" የተባለች አገር ናት።

የመፅሀፈ አብርሂትን አገላለፅ እንደወረደ ሳስፍርና አብረን በደንብ እናፀድቀዋለን።

"ኢት–ስጦታ፤ ዮጵ–ብሜ ወርቅ ወይም እንቁ፤ ግዮን • ፈሳሽ ወንዝ፣ በጥቅ ል ኢትኦጵግዮን፤ የግዮን ወርቅ ስጦታ ተብሎ በሱባ ይተረጎማል። እንቅዮጳግዮን የሚለውን እንቅዮጳዝዮን ብለውታል" ይሉናል። ደህና ሁኑ! በኋቸው። የእነርሱን የተወላገደ ትርጉም እዚያው ለራሳቸው!

አሁን እኛ ማስረጃችን ብዙ ነው። እንግዲህ ያ ዕሁፍ ከደንጎላው ሰነድ አንዱ መሆኑ ነው። በኋለኛው ዘመን በመጡ ሴማውያን የተከተበና በሱባ ቋንቋ ትርጉም የሚሰጥ ስም ነው።

አለቃ አያሌው ታምሩ በ1995 ዓ.ም በአንድ ያገራችን ጋዜጣ ያስቀመጡት እውነታ አለ፡ "ግዕዝ የዓለም ቋንቋ ነው፤ የዓለም ህዝብ በዚህ ቋንቋ ዛሬ ባይጠቀምበትም የዓለምን ድምፅ አጠቃሎ የያዘ ግዕዝ ነው። ግዕዝ ለዓለም ቋንቋ መሰረት ነው። ልዑል እግዚአብሄርና ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የተነጋገሩበት ቋንቋ ግዕዝ ነው። ሰባት የድምፅ ንብረት ያለው ብቸኛ ቋንቋ ግዕዝ ነው። ይህ ድምፅ በመላው አለም እየሠራ ነው። በአገሩ ግን የተናቀ ሆኗል፤ በተለይ ዛሬ።" ብለዋል።

"ኢትዮጵያ ማለት ምን ማለት ነው?" "እ ... በግሪክ የተቃጠለ ፊት ማለት ነው ቲቸርዬ" "ብራቮ በትክክል ተመልሷል። የተቃጠለ ፊት ወይም በፀሃይ የጠቆረ ፊት ያላቸው... ጎበዝ ልጅ!" ትምህርት ቤት'ኮ ነው። ኢትዮጵያዊ መምህርና ኢትዮጵያዊ ተማሪ። ፈተና ላይ ሳይቀር ይቀርባል።

ወዲያው ደግሞ እዚያው ክፍል ውስጥ "ኢትዮጵያ የ3 ሺ አመት ታሪክ ያላት፣ የራሷ ፊደልና ቋንቋ ያላት፤ ዓለም ባልሰለጠነበት ዘመን የወጪ ንግዷ አጣን፣ ብርጉድ፣ ከርቤ፣ የዋሊያ ቀንድ፣ ያውራሪስ ቀንድ፣ በታችኛው ሽለቆ፣ በላይኛው ሸለቆ፣ የኩሽቲክ ተናጋሪዎች በሰፈሩበት፣ ሴሜቲኮች ከመግባታቸው በፊት፣ ኒሎ ሰሃራ ከመሰልጠኑ በፊት፣ በአሞቲክ ተፋሰስ ... ምንትስ ቅብርጥስ" እየተባለ ይሽጎደጎዳል።

ኪርኩለሙ የነሱ ከሆነ መቸስ ምን ይደረጋል?

ለማንኛውም መቀበል ካለብን ራሳችን ለማሞገስ ሳይሆን፣ በግሪክ የሚወክለን ትርጉም ስለሌለው ሳይሆን በቂ ማስረጃ ስለሌላቸውና እኛ ግን ስላለን ነው። ምነው መረጃ መረጃ ይባል የለ? እነሱ እኛን የሚያስፈራሩን በመረጃ የተደገፈ በሚል ውሸክታ ነው። ስለዚህ ያብራሩልን።

ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ከየት ይመጣል? ዓባይ መቸም ትርጉም አለው። በአማርኛ ዓባይ፣ በግዕዝ ፈለገ ግዮን፣ በጥንት ግብፃውያን ዴልታ፣ በቅዱስ መፃህፍ "የኣር" በአዲሱ ላይ ማስክ፣ በአረቦች ምስር፣ ፊደል አልባ በነበሩ አገሮች ኒል ኧረ ብዙ ብዙ እየተባለ ተገለባብጦ ትርጉም ሲሰጥ የኖረ ወንዝ ነው።!

ስለዚህ በአማርኛ ኢትዮጵያ እያልነው ያለነው በዘመን ብዛት ተወራርሶ እዚህ ደረሰ እንጂ በጥንታዊ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አንድ አይነትና ተመሳሳይ፣ ቢገለባበጥ ይዘቱን የማይለቅ፣ በራሱ በፈጣሪ የተሰየመ፣ ከነውነቱ የተሰጠ ስያሜ ነው። የምድር ሁሉ ቋንቋ አንድ በነበረች ጊዜ፣ በቋንቋዎች ሁሉ እናት ቋንቋ፣ ፈጣሪ ከፍጡሮቹ ጋር በተነጋገረበት ቋንቋ "እንቅዮጳዝዮን" ስትባል ቆየችና ቀስ በቀስ "ኢትዮጵግዮን" መባል ጀመረችና በመሐል ቤት ተሰረቀች። ከዚያ በኋላ ለሌላ ግልጋሎት ሲጠቀሙበት ኖረው ብንፈልግ፣ ብንፈልግ፣ ብንዳብስ፣ ብንዳብስ አጣነው። በመጨረሻ "ኢትዮጵ" ሆኖ አገኘነው። ኢት፤ ስጦታ ዮጵ፤ ብሩሄ ወርቅ፤ ኢት ዮጵ–አሃ ብለን ስንመረምር ፍርፕርጡ ወጥቶ ቁጭ። ስሟ ተገኘ!

"ኢት" ምንድነው? "ስጦታ" ዮጵ? "ብሩሄ ወርቅ ወይም እንቁ" ግዮን? "ፈሳሽ ወንዝ" በጥቅል? "ኢትዮጵግዮን" አጠቃላይ ምን ይሆናል? "የግዮን ወርቅ ስጦታ" በድሮው የኢትዮጵያ ቋንቋ ምን ትባል ነበር? "ኢትኦጵግዮን" ከዚያ በፊትስ ይች ምድር ማን ትባል ነበር? "እንቅዮጳዝዮን" ባጭሩ የአገሪቱ ስያሜ ምን ተብሎ ይገለፃል? "የግዮን ምንጭ" ጎበዝ ልጆች በትክክል ተመልሷል። በሁሉም ቋንቋ ትርጉሙ ይሄ ነው። ወደፊት ልጅ ስወልድ የማስተምራቸውን እየተለማመድኩ ነው። እንዳይንዛዛባቸው "ኢትዮጵ" እላቸዋለሁ። ከፍ ሲሉ "ኢትኦጵግዮን" እላቸዋለሁ። ለአቅመ አዳምና ለአቅመ



ሄዋን ሲደርሱ "እንቅዮጳዝዮን" መሆኑን እነግራቸዋለሁ። ፀሃይ ለፀሃይ እንዲንከራተቱ ሳይሆን በነፋሻማ አየር ዘና ብለው ወርቅ እንዲፈልጉ!

ለማንኛውም እኔና እናንተም በዚህ መልኩ ብንቀበለውና በደንብ ብናፀድቀው ደስ ይለኛል። ጥልቅ ምርምሩንም ሆነ አወራረዱን አሰፋፈሩንም ሆነ አጠቃላይ ሁኔታውን ለምሁራን እንተዋለን።

እውነቱ ደግሞ ይሄ እና ይሄ ብቻ ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከ "ኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ/ናፓታመረዌ/" መፅሃፍ ስለዚያ ዘመን ሁኔታ የተወሰኑ ነጥቦችን ቆርሰን አውጥተን ጥቂት ነገሮችን እንዲያው ለትዝብት ያህል ... ስለ አክሱምና ስለግሪኮች ግንኙነት እንመልከት። ከወዲሁ ጠርጥረን ካላለፍን እዚያ ዘመን ላይ ስንደርስ'ኮ... የግል ሃተታ አናስገባም። የተባለውን ማለት ብቻ ነው።

"... እስክንድር ሊሞት ሲል ግዛቱን በደፈናው "የሚገባው ሰው ይውሰድ" ብሎ የማንንም ስም ሳያነሳ ሞተ ይባላል። የጦር አለቆቹ ግን "እኔን ይሆናል" በማለት በአሳብ ትንሽ ተተራመሱ። ተዋጉም። ከሞተ በኋላ ከ ሮክሳን የተወለደው አሌክሳንደር ኤጎ የሚባለው ልጁ በመቄዶንያ ዙፋን በሞግዚት የሁሉ የበላይ ሆኖ እንዲገዛ ተደርጎ ነበር። ዳሩ ግን የገዛ ሞግዚቱ ካሳንድር ከነእናቱ ጋር ገድሎ መቄዶንያን ያዘ። የቀረውንም ሰፊ ግዛቱን "ዲያዶክ – ተከታይ" የተባሉት የጦር አለቆቹ በክፍፍልና እኔ የበላይ ልሁን በማለት እርስ በርሳቸው ብዙ ጊዜ ሲዋጉ ቆይተው የመጨረሻው ጦርነታቸው በ301 ቅ.ል.ክ. በ ኢፕሱስ ከተደረገ በኋላ እርቅና ሰላም ሆኖ ከዚህ እንደሚቀጥለው በስምምነት ከሶስት ላይ ተከፋፈሉት።

1ኛ:– ግብፅና አካባቢው ለፕቶሎሚ/በጥሊሞስ/ የላጎስ ልጅ

2ኛ:– ሶርያና አካባቢው ለሴለውኩስ

3ኛ:– መቄዶንያ ከካሳንድር በፊት ለአንቲገን በኋላ ለካሳንድር።

እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ቀጥሎ እስከ ሮማውያን መነሳትና እስከ ክሊዮፓትራ ድረስ የበጥሊሞስ ዘር እየተከታተለ በግብፅ ዙፋን ተቀመጠ። የመርዌና ያክሱም መንግስታትም ... ግንኙነት አድርገው የግሪክን ስልጣኔ በመጠኑ ማስገባት የቻሉት ሽቀጥ ለሽቀጥ የተለዋወጡት ከነዚሁ ከነበጥሊሞስ ጋር ነው።" ይሉናል በገፅ 173።

በምዕራፍ 29 በገፅ 178 ደግሞ "... እርሷንና (የመርዌዋን ህንዳኬን) አገሯን ለመሰለል ከግብፅ ሰላዮች በላከ ጊዜ ራሱ ትልቁ እስክንድር ከሰላዮቹ ጋር እንደ አንድ ተራ ሰው መስሎ መጥቶ እንደነበርና አውቃው "አንተ ዓለምን የያዝኸው እስክንድር ንጉስ ዛሬ ደግሞ ባንዲት ሴት ተያዝህ" እንዳለችውና እርሱ ደግሞ "አንችንም ልጆችሽንም በደግነት እጠብቃችዋለሁ፤ አንችንም ሚስት አደርግሻለሁ" እንዳላት... የዮሃንስ መደብርን መፃህፍ ጠቅሰው አስፍረዋል። ወረድ ስንል:–

"... የሆነ ሆኖ እስክንድር ባለፈው ባመለከትነው አይነት ሞቶ ግዛቱን የጦር አለቆች ሲካፈሉት የግብፅ ግዛት ለፕቶሎሚ ሶተር ደርሶ ይኸው

ኙቶሎሚ በግብፅ ላይ ነግሶ በሚያስተዳድርበት ዘመን በመርዌም ንግስት ህንድኬ ሞታ አስተርክ አሚን ገነሰ። (ሶስት መቶ አመት ከክርስትና በፊት) በዚህም ጊዜ የግብፅ ገዥዎች ኙቶሎሚ ሶተርና ከእርሱ የቀጠለው ኙቶሎሚ ፊላደልፍ በኢትዮጵያ የሰሜን ጠረፍ ወታደርና ሰው መላክ ጀመሩ። በተለይ ኙቶሎሚ ፊላደልፍ በምጥዋ ወደብ አንድ የባህር ወደብ አሰርቶ በስሙ ኙቶሎማይስ ብሎ ሰየመው። እንደዚሁም ከቀድሞ ዥርምሮ የነበረው የአዶሊስ ከተማ ወደብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ ተሟሙቆ የግብፅና የኢትዮጵያ ዋና የሸቀጥ ማመላለሻ ሆኖ ነበር።

ይኸም ኙቶሎሚ ፊላደልፍ በ282 ቅ.ል.ክ. ላይ ከእስራኤል ሊቃውንት ውስጥ ሰባ (70) ሊቃውንት ራሱ መርጦ አምጥቶ ብሉይን ከእብራይስጥ ወደ ፅርዕ ለመጀመሪያ ጊዜ ስላስተረጎመ በትርጓሜው ስራ ራሱ አብሮ ስለሰራ ስመጥርነትን አግኝቷል።

ከህንደኬ ንግስት ይኸውም ከ300 አመት ቅ.ል.ክ. ወዲህ በመርዌ ምንም ያህል ሃይለኛና ታሪካዊ ስራ የሰራ ንጉስ አልተነሳም። አስተርክ አሜን፣ አርካሜን፣ አሩአሞን፣ ሐርሲኦተው የሚባሉ ነገስታት በዙፋን አልፈዋል። እነዚህም ምናልባት በዘመናቸው ብዙ ስራ የሰሩ ይኖርባቸው ይኖራል። ዳሩ ግን ከእነዚህ ውስጥ የአርክአሜን በመጠኑ ሲገኝ የቀሩት ስራቸው በታሪክ ውስጥ ሽፍን ነው።..."

እንግዲህ ... በግልፅ እንዳየነው "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም በዚሁ ጊዜ ነው መሰረቱን የያዘው ማለት ነው። ስመ ጥርነትን ... አሉ...

"ኩሽ" የሚለውን ወደ ፅርዕ /ግሪክ/ ሲተረጉሙ "ኢትዮጵያ" አሉት አይደለም የተባለው? በዚህ ጊዜ ነው በፀሃይ መቃጠላችን የነገሩን፤ መክሰላችን ያረዱን፤ መጥቆራችን ያበሰሩን፤ ከዚህ ጊዜ በፊትስ? እነ ሆሜር፣ እነ ሄሮዱተስ ማን ይሉን ነበር? "አይቶፒያ" ምን ለማለት? "ታላላቆች፣ መልካቸው ያማረ፣ ቅኖች፣ በጎ አድራጊዎች፣ ሸበላዎች..." እያሉ የዚችን ምድር ነዋሪዎች ሲገልጿቸው ነዋ። ታዲያ ከምኔው ጠቆርን ጎበዝ? ከዚህ በፊት ስሟ ማን ሆነና!

"አሯል ሆዴ ጨሷል ሆዴ

ቢቸግረኝ እንጂ ጠላቴን መውደዴ!" አለ ያገሬ ሰው! "ዘራፍ!" አትልም ... እንዳባቶችህ!



# ምዕራፍ ፲

## የአክሱም ኢትዮጵያና የኑብያ ኢትዮጵያ ልዩነትና አንድነት

የአክሱሙ ኢትዮጵያና የኑብያው ኢትዮጵያ ልዩነትና አንድነት ስንል ከታሪክ አንፃር እንደመሆኑ መጠን የአዲስ አበባ ኢትዮጵያና የድሬዳዋ ኢትዮጵያ እያልን እንጂ ሌላ አይደለም። በዚህ ግ--ር ወይም ቅ--ር የሚሆኝ ካለ ‹‹እሽ በቃ የአስመራው ኢትዮጵያና የአዲስ አበባው ኢትዮጵያ እያልን ነው›› ብለን እናረጋጋዋለን። በዚህ ምሣሌ ካልተግባባን ኢትዮጵያ የ20 አመት ታሪክ ያላት ናት ልንል ስለሆነ ይቅርብን።

ቀደም ሲል እንዳየነው በኢትዮጵያ በነበሩ የካም ኩሽ ነገድ ላይ ነገደ ዮቅጣኖች ከተቀላቀሉ በኋላ የአሁኗን ሠሜናዊ የኢትዮጵያ ክፍል ይዘው ሲኖሩ፤ ነባሩ ህዝብ ደግሞ ወደ ኑብያ እየተስፋፋ ሔዷል። ያም ቢሆን በቀደመው ዘመን በጣም የገነነው መንግስት መቀመጫው በኑብያ ኢትዮጵያ የነበረና ነገስታቱ መቀመጫቸውን እየለዋወጡ በየግዛቱም በንጉሰነገስቱ ስር የሆኑ ንጉሶች እየተሾሙ በጋራ ያስተዳድሯት የነበረች አገር ናት። ‹‹በመላ አፍሪካ ከሚታወቁት የቋንቋ ቤተሠቦች መካከል አፍሮ እስያዊና አባይ ሠሃራዊ የተሠኙ ሁለቱ በኢትዮጵያ ይነገራሉ። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገሩት ከ70 የሚበልጡ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሁሉ ከተጠቀሡት እናት ቋንቋዎች እንደመነጩም ይታወቃል። የኢትዮጵያ ህዝብ ተሠባጥሮና ተቀላቅሎ መስፈር ከቋንቋዎች ስርጭትም አኳያ ሊገለፅ ይችላል። በጥቅል ሲታይ የኢትዮጵያ ህዝብ ተወራርሷል፣ ተጋብቷል፣ ተዛምዷል። በጋራም የረጅም ታሪክ ባለቤትነቱን በጦርነትና በሠላም ጊዜ ተጋርቶአል።›› (ኘ/ር ላጵሶ1983 ዓ.ም)

ከዚህ አንፃር በኑብያ ኢትዮጵያም ሆነ በአክሡሙ ኢትዮጵያ የነገስታቱ የዘር ሃረግ አመዛዘገ ወጥ የሆነና ተዋረዱን ጠብቆ የተከታተለ አነጋገስ ነበረ ብሎ ማሠቡ ብዙ አያስኬድም። ይህ ምናልባት በኋለኛው የአክሡም ዘመን ተግባራዊ የተደረገ ቢሆን እንጂ በጥንቱ ዘመን ሆኖ ነበር ለማለት አይቻልም። የአሁኗ ኢትዮጵያ መስራቾች አክሡማውያኑ መሆናቸው ይታወቃል። ነገር ግን ታሪክ የሚነግረን ከጎናቸው ያለው መንግስት እየደከመ ሲሄድ (የናፓታና የመርዌው) አክሡማውያኑ አክሡምን እያቀኑ፣ እያገነኑ መነሳታቸውን ነው።

ዛሬ በካርታ ተከልለው ሁለት የጎረቤት አገራት የሆኑት እነዚህ ህዝቦችና መንግስታት በጥንቱ ዘመን አንድ በነበረው ግዛታቸው በአንድ አይነት ስም ሲጠሩ ያሣለፉ ናቸው። ልዩነታቸው በኑብያ በኩል ኩሾች መበርከታቸው፤ በአክሡሙ በኩል ሴማውያን መበርከታቸው ሲሆን፤ በባህል፣ በልማድ፣ በቋንቋና በአምልኮ ላይ የተመሠረተ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም ሲባል የናፓታና የመርዌዎቹ ከግብፅ እንደመዋሠናቸው መጠን

ቋንቋና ባህል ወግና ልማድ አምልኮና መሠል ነገሮቻቸው ከግብፅ ጋር የተወራረሠ ነው። በአክሡም በኩል ደግሞ ከደቡብ አረብ እንደመዋሠናቸው መጠን የተጠቀሡት ነገሮች ከደበብ አረብ የሚወራረሡ ናቸው። ደቡብ ዓረብ ስንልም

በየመን አድርገው ቀይ ባህርን ተሻግረው የገቡ ያልናቸውን የሴም ዘሮችን መሆኑ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለም ዓረብ ስንል ከእስልምና በፊት ቦታን፣ ከእስልምና በኂላ የህይማኖቱ ተከታዮች የሰፈሩበትን ቦታ መወከል መጀመሩን አንዘነጋም። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚነገሩ ቋንቋዎች በምሁራኑ እይታ በ3 የተከፈሉ መሆናቸው ይታወቃል።

1. የኩሽ ቋንቋዎች፦ አገውኛ፣ ቤጂኛ፣ ብሌን፣ ሀድይኛ፣ ከምባትኛ፣ ደራሲኛ፣ ኮንሶኛ፣ ሲዳምኛ፣ ሳሆኛ፣ አፋርኛ፣ ሱማሊኛና በሠፊው ኦሮምኛ የሚገኙበት ሲሆን፣ በጠቅላላው 23 ያህል የኢትዮጵያ ብሄረሠቦች የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው።
2. የኦሞ ቋንቋዎች፦ 16 ያህሉ የኢትዮጵያ ብሔረሠቦች የሚናገሩበት ቋንቋ ሲሆን፣ ከነዚህ መካከል ከፍኛ፣ ጃንጃሮኛ፣ ወላይትኛ፣ሽናሽኛ፣ ጊሚርኛ፣ ኮሉኛ (ኮንታ)፣ ማጂኛ፣ ዶርዚኛ ይገኙባቸዋል።
3. የሴም ቋንቋዎች፦ አማርኛ፣ ትግረ፣ ትግርኛ፣ አርጎብኛ፣ ጉራግኛ፣ ጋፋትኛ፣ ሐረርኛን ጨምሮ አስራ ሠባት ብሔረሠቦች የሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው ተብሎ ተዘርዝሯል። በዚህ መሰረት ስለ ልዩነት እና ስለአንድነት ስናነሳ ለምሣሌ በአፄ ዮሃንስ 4ኛ ዘመን "ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ" ተብለው የነገሡትና የሚታወቁት ራሣቸው አፄ ዮሐንስ ነበሩ። መቀመጫቸውም መቀሌ አድዋ ነበር። ልክ በዚያው ዘመንም አፄ ምኒልክ የሸዋ "ንጉስ" ነበሩ። አፄ ምኒልክ የሸዋ ንጉስ ቢሆኑም ግን ለማእከላዊው መንግስት መገበራቸው አልቀረም።

የንጉስ እና የንጉሠነገስትን ልዩነት ሳንዘነጋ፤ እነዚህ ሁለት ነገስታት የሚያስተዳድሩት ህዝብ በቋንቋ፣ በባህል፣ በጂኦግራፊ፣ እንዲሁም በሌሎች ዘርፈ ብዙ ነገሮች የተለያየ ህዝብ ነበር።.. በብሔርም እንዲሁ።

ሁለቱም የየራሣቸው ሠራዊት ነበራቸው። ሁለቱ ነገስታት እንዲሁም የሚያስተዳድሩት ህዝብ ግን በአንድ ኢትዮጵያ ስር የሚካተቱ ናቸው። የሚገናኙት በአመትም በሁለት አመትም፣ ወይም ጦርነት ሲኖር፣ አሊያም በሌላ ጉዳይ ብቻ ነበር። ሌላው ቀርቶ ምኒልክና ዮሃንስ በብሄርም/እናት ቋንቋቸው አንድ መሆኑን ሣንዘነጋ/ በሚናገሩት ቋንቋም ልዩነት ነበራቸው። ከመሐላቸው አንዱ ከገነነ የበላይነቱን በሃይል ይይዛል። ሌላውም ተነስቶ የንጉሠነገስትነቱን ስልጣን ሊነጥቅ ይችላል፣ የመናገሻ ከተማውንም ሊለውጥ ይችላል.. ወዘተ። ነገር ግን ግዛቱ አንድ



ወጥ ሆኖ በኢትዮጵያ ስም የሚጠቃለል ነው። በዚህ መሠሉ ቀላል ምሣሌ በቀላሉ አንድነታቸውን እያሠብን መቀጠል እንችላለን። በአንድነታቸው ውስጥም ልዩነታቸውን። ይህ እውነታ በካርታ ተከልለው እስኪለያዩ ድረስ የቆየ መሆኑንም እንዲሁ።

በጥቅሉ የናፓታና የአክሡም አገሮች በአገር ጉርብትናም በዘርም የሚገናኙ በየተራ ገናና መሆን የቻሉ ወንድማማቾች ናቸው። ‹‹ሁለቱ አገሮች በመጀመሪያ ናፓታ፣ ቀጥሎ መርዌ በገነኑ ጊዜ በአክሡም ዙሪያ የሚገኘው አገር ለእነርሡ መገበሩ፤ አክሡም በገነነ ጊዜ ደግሞ አብርሃ/ኢዛና/ ከኑተከታዮቹ ኑብያን/ /ናፓታንና መርዌን/ መግዛታቸው የተረጋገጠ ነውና ይህን መሠሉ የእርስ በርስ መገዛዛት አንድነታቸውንም ጭምር ያሣያል።›› ( ተክለፃድቅ መኩሪያ 1965 ዓ.ም)

ኢትዮጵያ ሲባል ደግሞ በጥንቱ ዘመን ከግብፅ በደቡብ፣ ከኤርትራ ባህር ወደ ምዕራብ እስከ አትላንቲክ ድረስ ያለውን ግዛት ያጠቃልል ነበር። በአንዳንድ ፀሃፍት ዘንድም ምስራቁ ኢትዮጵያ ምዕራቡ ኢትዮጵያ ተብሎ ተገልፆ ይገኛል።

ምንም ቢባል ግን ከኑብያ እስከ ሳዕላይ ግብፅ፣ ከኤርትራ ባህር ወዲህና ወዲያ እስከ አሁኑ የመን ድረስ የሚያጠቃልለው ግዛት ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራ ወጥ የሆነ ግዛት ነበር...። በአጭር አገላለፅ የአሁኗ ኢትዮጵያ ላይ ኤርትራን፣ ሱዳንንና የመንን መጨመር ማለት ነው።.... ስለዚህ ልዩነታቸውንና አንድነታቸውን ስናይ፤ ልዩነታቸው ጠባብ፣ አንድነታቸው ሰፊ ሆኖ እናገኛቸዋለን።

## ምዕራፍ ፫

## ኢትዮጵያ በታላቁ መፃህፍ

በዚህ ምዕራፍ አባ ጋስፖሪኒ ገብረማርያም ጥቂት ያግዙናል።

"በኦሪት ዘፍጥረት ምዕ 2 ቁ 13 ለመጀመሪያ ጊዜ ኩሽ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያን ምድር የከበበው የትልቁ ዠማ የግዮን ነገር በሚነገርበት ላይ እናገኘዋለን" ይሉናል። "... የሁለተኛውም ስም ግዮን ነው እርሡም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል" የሚለውን ማለታቸው ነው።

- ❖ በኦሪት ዘፍጥረት ም10 ቁ 7 ላይ የካም ልጆች ኩሽ፣ ሚዝራም ፋጥና ከነዓን ተጠርተዋል"ም ይሉናል።
- ❖ "በኦሪት ዘኑልቁ ም12 ቁ 1 ማርያምና አሮን በሙሴ ሚስት በኢትዮጵያዊቷ ላይ መናገራቸው ይገኛል "ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና።" ይላል።
- ❖ መዝሙረ ዳዊት ም67 ቁ 31 " መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ፣ ኢትዮጵያ ወደ እግዚአብሔር እጆቿን ትዘረጋለች።"
- ❖ መዝሙረ ዳዊት ም86 ቁ 4 "እነሆ ፍልስጤማውያን ጢሮስም የኢትዮጵያም ህዝብ እነዚህ በዚያ ተወለዱ"
- ❖ 2ኛ ዜና መዋዕል ምዕ. 12 ቁ 3 የሠለሞን ልጅ ሮብዓም ታማኝነቱን አጉድሎ በአምልኮ ባእድ ወደቀ የሚል ቃል ይተርካል። በዚያን ጊዜ አምላክ የግብፅን ንጉስ ሱሳቂምን አስነስቶ እርሡም የልብያን የትሮግሎዲትንና የኢትዮጵያ ወታደሮችን ጨምሮ አስከትሎ ኢየሩሣሌምን ይዟታል። "የኢትዮጵያ ሠዎችም ነበሩ" ይላል።
- ❖ በዚሁ መፅሃፈ ዜና ም21 ቁ 16 የዓረብ ወሠንተኞች የሆኑ ኢትዮጵያውያን ዝና ባጭሩ ይተረካል "የፍልስጤማውያንና በኢትዮጵያውያን አጠገብ የሚኖሩትን የዓረባውያንን መንፈስ በኢዮራም ላይ አስነሣ።"
- ❖ ትንቢተ አሞፅ ምዕ 9 ቁ 7 "የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር" ይላል። እዚህ ላይ የአባ ጋስፖሪኒን ትንታኔ እንስማ። "በአሞፅ ትንቢት ላይ ስለ ኢትዮጵያ የሚናገር እጅግ የሚያስደንቅ ነገር እናገኛለን። ክክ.ል በፊት 750 ላይ ቀድሞ ትንቢት የተናገረው አሞፅ "እናንተ የእስራኤል ልጆች ለኔ እንደ ኢትዮጵያውያን ናችሁ" ይላል እዚህ ላይ የተናገረው የመለኮታዊ ቃል አነጋገር በጣም ግልጥ ነው። እግዚአብሔር ኢትዮጵያውያንንና የተመረጠውን ህዝብ እስራኤልን በአንድ አይነት ፍቅር አፈቅራቸዋለሁ ይላል። ይህም ደግሞ ኢትዮጵያ በአምላካዊው ፍቅር ለመወደዷ የሚመሠክር ዐብ የሆነ ምስክር ነው።" ይሉታል።



ስለ ኢትዮጵያ ደጋግሞ የሚያነሣው ኤልያስ ነው። ኤልያስ በትንቢቱ ኢትዮጵያን ሲያነሣ የጠራቸው የኢትዮጵያ ነገስታት በኑብያ ናፓታ የነገሡ መሆናቸውን ስናስብ የኑብያና የአክሡም ኢትዮጵያ ተጠቃለው በአንድነት መጠራታቸውን እናረጋግጣለን።

ኤልያስ የነበረበት ዘመን ቅ.ል.ክ 730-690 ባሉት ጊዜያቶች ነው። ይህ ታላቅ ነብይና ትንቢተኛ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ነገስታት መቀመጫ ናፓታ ነበረ።

- ❖ ትንቢተ ኢሣያስ ም 45 ቁ 14 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የግብፅ ድካምና የኢትዮጵያ ንግድ ቁመተ ረጅሞችም የሳባ ሠዎች ወደ አንተ ያልፋሉ ለአንተም ይሆናሉ..."

የአባ ጋስፖሪኒ መፅሃፍ እንዲህ ይላል" የግብፅ ስራዎች የኢትዮጵያ የንግድ እቃዎችና ረጅም ቁመት ያላቸው ሳባውያን ወደ አንቺ/እየሩሣሌም/ ያልፋሉ ያንችም ይሆናሉ። እጃቸውን አጣምረው ይከተሉሻል፣ እጅ ይነሡሻል፣ ልመናቸውንም ያቀርቡልሻል፣ ስለምን? ባንቺ ብቻ አምላክ ስላለ፣ ካንችም ውጪ ስለሌለ ነው" ይላል ይሉናል።

- ❖ በምዕ 43 ቁ 3 "ግብፅን ላንተ ቤዛ አድርጌ ኢትዮጵያንና ሣባንም ለአንተ ፋንታ ሠጥቻለሁ..።" ይላል።
- ❖ ትንቢተ ሶፎንያስ ም2 ቁ 12 "እናንተ ኢትዮጵያውያን ደግሞ..." ሲል ያነሣናል። ም3 ቁ 10 ላይ " ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ" ተብሎ ተጠቅሷል።

ሌላው ቅ.ል.ክ ከ626-587 የነበረው ኤርሚያስ ኢትዮጵያን ሁለት ጊዜ ይጠራል። ትንቢተ ኤርሚያስ ምዕ 13 ቁ 23 "በእውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?"

- ❖ አሁንም ኤርሚያስ በትንቢቱ ምዕ 38 ቁ 7 "በንጉሡም ቤት የነበረው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርሚያስን በጉድጓድ ውስጥ እንዳኖሩት ሠማ።... ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌክን ከአንተ ጋር ሠላሣ ሠዎች ከዚህ ውሠድ፤ ነቢዩም ኤርሚያስ ሳይሞት ከጉድጓድ አውጣው ብሎ አዘዘው.." የሚል ሁተታ ሰፍሯል በትንቢተ ህዝቅኤል በምዕ. 30 ደግሞ "ኢትዮጵያና ፋጥ" ተብሎ ሠፍሯል። (ቅ.ል.ክ 590)
- ❖ ትንቢተ ኢሣያስ ምዕ 18 "በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላለች፤ ክንፍ ያላቸው መርከቦች ላሉባት፤ መልዕክተኞችንም በባህር ላይ፤ የደንገል መርከቦችንም በውሃ ላይ ለምትልክ ምድር ወዮላት! እናንተ ፈጣኖች መልእክተኞች ሆይ፤ ወደ ረጅምና ወደ ለስላሣ ህዝብ፤ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ወደ ሆነ ወገን፤ ወደሚሠፍርና ወደሚረግጥ፤ ወንዞችም ምድራቸውን ወደ

ሚከፍሉት ህዝብ ሂዱ። በዓለም የምትኖሩ ሁሉና በምድር የምትቀመጡ ሆይ፤ ምልክት በተራሮች ላይ በተነሣ ጊዜ እዩ፤ መለከትም በተነፋ ጊዜ ስሙ።" ይላል።

በአባ ጋስፓሪኒ የኢትዮጵያ ታሪክ መፃህፍ በገፅ 13 እንዲህ ይብራራል። ከእብራይስጡ እንዳለ ተርጉመው ያሠፈሩት ነው።

"የአክናፍ ጩኸት የሚሠማባትና (ግብፅ) ከኩሽ ቨርሞች ወዲያ ያለች (ኢትዮጵያ) አገር፤ ከፓፒሩስ በተሠራ ታንኳዋ መልዕክተኞቿን በባህር ውሃ ላይ የምትልክ ምድር፤ ወዮላት! ፈጣኖች መልእክተኞች ሆይ ቁመተ ረገቨርም፣ መልከ ጠይም፣ (ቆዳቸው ወደሚያብለጨልጩ) ወደ ሆኑት፤ እጅግ በጣም ሩቅ የሆኑትን አገሮች ሁሉ ወደሚያስፈሩት፤ ሃያላን በመሆናቸው ሁሉን በእግራቸው ወደሚረግጡት፤ አገራቸውን ገርሞች (ወንዞች) ወደተለሟት (ወደፈረፈሯት) ህዝብ ተመለሡ ይላል። ይህ በነቢዩ አፍ የተነገረው ሁናቴዋን የሚያስታውቀው የአምላክ ቃል ለኛ ክብሯን፣ ሃይሏንና፤ ስልጣኗን የኢትዮጵያንም ስመ ጥርነት ያስረዳናል" ይሉናል። ይህ ምክር ለኢትዮጵያዊው ንጉስ ለሻባካ የተነገረ ነበር። በአሶር ንጉስ ላይ ተባባሪ እንዳይሆን ለማስታወቅ።

በምዕ 37 ቁ 9 ደግሞ "ትልቁ የኢትዮጵያ ንጉስ ቲርሃካ በአሶር ንጉስ በሰናክሬብ ላይ ሊዘምት ነበር" ይላል።

ዳንኤልም በትንቢቱ ንጉስ አንጥያኮስን "በግብፅ፣በሊቢያና በኢትዮጵያ ላይ መዝመቱን" ይናገራል።

ከግብፅ፣ ከአሶር፣ ከኢየሩሳሌም፣ከጢሮስ.. ወዘተ በዚያ ዘመን ሃያል ከተባሉ አገሮች ተርታ ኢትዮጵያ ከነነገስታቷ ስም ስትጠራ በደንብ እናያለን። በተለይ በነፒያንኪ፣ ሻባካ፣ ቲርሃካ፣ታንታሙን ጊዜ በተደጋጋሚ ተነስታለች። ወደፊት እንደምናየውም እነዚህ ታላላቅ ነገስታት በታላቁ መፃሃፍ ስለተጠቀሱ ብቻ ስራቸውን በቁፋሮ ከተገኙ ሐውልቶችና የሃውልት ላይ ፅሁፎች በመተርጎም" ተመራማሪዎች ይፋ አድርገውታል። በታላቁ መፃህፍ አገላለፅ እነ ሻባካ፣እነቲርሃካ "የኢትዮጵያ ነገስታት" ተብለው በግልፅ ተቀምጠዋል። የኒለኞቹ የታሪክ ተመራማሪዎች ቢያንስ "የቀድሞ የኢትዮጵያ ነገስታት" ብለው ለመጥቀስ አልደፈሩም። አገር በስዕልና በካርታ በተከለለ ቁጥር ታሪክ መካፈል ይቻል ይሆን?



## ምዕራፍ ፱
## የግብፅ ስልጣኔ

ማኔስ የተባለው የግብፅ የመጀመሪያው ፈርኦን ቅ.ል.ክ 3200 ላይ ተበታትኖ የሠፈረውን ህዝብ ገሚሡን በማስተባበር፣ የቀረውን በሃይል በመጠቅለል ከሁለት የተከፈለውን ህዝብ አንድ በማድረግ የመጀመሪያውን ዳይናስቲ መሠረተ።

ከኑብያ ኢትዮጵያ የሚዋሡኑት በአሞንና በእባብ ሲያመልኩ፤ በታህታይ ግብፅ የሠፈሩት ደግሞ "አዚት" በምትባል በሴት አንቀፅ በምትጠራ እባብ ያመልኩ ነበር። የእነዚህ አማልክት ካህናት አንድነት መስርተው እንደተለመደው ህዝቡን ማስተዳደር ጀመሩ። በቀደመው ዘመን የግብፅ ፈርኦኖች ተጠሪነታቸው ለአማልክቱ ካህናት ነበር። ማኔስ "አማት" ላይ መቀመጫውን አድርጎ በግብፅ በሠፈሩ ህዝቦች ላይ ከነገሠ በኋላም ተከታታይ ዘሮቹ እየተተኩ ጥቂት ዘመን ገዙ።

በኋላም "የወንዶቹ ወንድ" የሚል ትርጓሜ ያለው "ካካኡ" የተባለ የጦር አለቃ ዙፋኑን ከማኔስ ዘር ቀምቶ ሁለተኛውን ስርወመንግስት መሠረተ። በካካኡ ዘመን ብዙ አይነት አምልኮ ተስፋፋ። ዋናው በሠው አምሣያ የሚቀረፀው "ኘታህ" እና የእርሡ ማደሪያ የሆነው "አፒስ" ወይም ሐፒ የሚባለው ኮርማ ነው።

ከጥጃ በላይ ከበሬ በታች የሆነ ኮርማ ይፈለጋል። ጥቁር ቦታ የሆነ፣ ግንባሩ አካባቢ ነጭ ሆኖ ነጩ ክፍል ሶስት ማዕዘን ያለው፣ደረቱ ላይ የሩብ ጨረቃ አይነት ቅርፅ ኖሮት ነጭ ቢሆን፣ ከወደ አፉ የጢንዚዛ ቅርፅ ከያዘ እሡ አምላክ ነው ይባላል። መረጣውን የሚያከናውኑት ካህናቱ ናቸው። የተጠቀሠውንና ያልተጠቀሡትን አይነት መመዘኛዎች ያሟላ ጥጃ ከውልደቱ ጀምሮ ይታደንና ከተገኘ "ኘታህ አድሮበታል" ተብሎ ስለሚታመን ጥጃውን ወስደው ያሣድጉታል። አድጎ ኮርማ ሲሆን የተቀደሠ ውሃ በሚባለው ቦታ ወስደው ይነክሩታል ወይም ያጠምቁታል። የአምላክነት ክብር ሠጥተው ይቀድሡታል። በቤተመቅደስ አስቀምጠው ይሠግዱለታል። በህይወት ዘመኑ ሁሉ ዓመታዊ ክብረበዓላቶች ይከናወኑለታል። ሲሞት በታላቅ የቀብር ስነስርዓት ከመሠል አምላክ ወንድሞቹና ከነገስታቱ ጎን ይቀበራል። እንደገና ሌላ ይመረጣል።

የዚህን አይነቱን ኮርማ ምስል በተለያዩ በድንጋይ፣ በብረት፣ በነሃስ፣ በብር፣ በወርቅ ተቀርፆ ይሠራና ደስ የሚል አብረቅራቂ ጨርቅ ጀርባው ላይ ይለብሣል... ወዘተ።

ይሄ የጥጃ አምላክ ለረጅም ምዕተ አመት በግብፅ ፀንቶ የቆየ ነበር።ነገር ግን የቀድሞዎቹ የአሮጌው ስልጣኔ ፀለቤቶች እንስሣውን፣ዛፉን

ወይም አሞራውን እባቡን እንዲሁ ራሡን ብቻ ያመልኩትና ይቀርፁት እንዲሁም ይሠግዱለት ነበር እንጂ ማደሪያው የሆነውን "ሠውን" አላዘጋጁም ነበር።

በኋላ ግን የሠው ማደሪያ ያለውን አሞንን በላእላይ ግብፅ በቴብ ቤተመቅደሡን ሠርተው ማምለክ ከጀመሩ በኋላ ግብፅ ራሷን የቻለች አገር ሆና ስትመሠረትና ላእላይ ግብፅን ስትጠቀልል የአሞንን ቤተ መቅደስና አምልኮውንም ልትወርስ ችላለች።

በኋለኛው ዘመን ከ1700-1300 ቅ.ል.ክ እስራኤሎች በግብፅ በተገዙ ጊዜና ከ400 አመት በኋላ በሙሴና በአሮን እየተመሩ ወደ አገራቸው ሲሄዱ እስራኤላውያን ጥጃ ቀርፀው ያመለኩትና ሙሴን ያበሣጩት፣አምላካቸውንም ያስቆጡት በፒታህ/በኮርማው/ አምሣል እንደነበር ይታወቃል።

ከዚህም ባለፈ በጥንቱ ዘመን በግብፅ ተዘርዝረው የማያልቁ ልዩ ልዩ አማልክት ነበሩ። እስከዚህ ዘመን ድረስም አሞን እጅግ አልገነነም ነበር። ኘታህ ከኋላው ተነስቶ በልጦት ነበር ማለት ነው። "ከ2ኛው ስርወ መንግስት በኋላ እስከ 10ኛው ስርወ መንግስት ድረስ ከ2980-2060 ቅ.ል.ክ ድረስ ብዙ ነገስታት ሲያልፉ የውስጥ አስተዳደራቸውን ከማደራጀት ጥበባቸውን ከማስፋፋት በቀር ግዛት ለማስፋፋት ገና አልተቀሰቀሡም፤ ትንሽ በምስራቅ በኩል እስከ ሲና ተራራ ድረስ ሄደው አስገብረዋል" (ተክለፃድቅ መኩሪያ 1965 ዓ.ም)

ግብፃውያን ግዛት ማስፋፋት ሳይጀምሩ ገና የሠሯቸው ስራዎችም በተለይ ከ3ሺ. አመት ጀምሮ የቀን ቆጠራውን ካላንደር ከማዘጋጀት ጀምሮ የተለያዩ የቤተመንግስት አደረጃጀቶችን፣ የግብር አሠባሠብ ስልትን፣ የጦር አደረጃጀትን፣ ቢሮክራሲውንና መሠል ነገሮችን ሲያደራጁ ቆይተዋል። በተለይ በ4ኛው ዳይናስቲ የፒራሚድ ግንባታውን ጨምሮ በርከት ያሉ የምህንድስና ጥበቦች ሊታዩ ችለዋል።

በግብፆች አጠራር "ኩፉ" /khouwou/ በግሪኮች "ቼዮኘስ" (CHEOPS)የተባለው የ4ኛው ዳይናስቲ አንዱ ንጉስ በሕይወቱ እያለ ያሠራው መቃብር ቤት ከሁሉ የበለጠ መሆኑን ፀሃፍት አረጋግጠዋል።

ይህ ፒራሚድ 2 ሚሊዮን 300 ሺ. ድንጋይ በሠው ትከሻ እየተጋዘ የተሠራ ሲሆን፤ ከመሠረቱ ውጪ ቁመቱ 146 ሜትር እንደሚደርስ የፖልፒዬሪ መዝገበ ቃላት ያሣያል።

100 ሺ. የሚደርሱ ባሮች በምሬት እንዳያመልጡ አንገታቸው በገመድና በሠንሠለት ተሳስሮ ራቁታቸውን ሆነው ከኋላ ገራፊ ተዘጋጅቶ በጅራፍ እየተገረፉ ያቀላጠፉት ግዙፍ ህንፃ ነው። አንድ ሠው አንድ



ሜትር ኩብ ድንጋይ ባንድ ጊዜ ይሸከም ነበር። ስራው 20 አመት እንደሌሎች 40 አመት ፈጅቷል።

ነገስታቱ ሞተው ሲነሡ ሊኖሩበት የፈለጉት ቤት እንደመሆኑ መጠንም ተቀብረውበትም በዘበኞች ይጠበቃል፣ አገልጋዮችም ተመድበው ንብረቱ ሁሉ ተቀምጦበት ይገኝ ነበር።

ከ1ኛ እስከ 10ኛው ዳይናስቲ ድረስ የነበሩት ዋና መቀመጫ ከተማ መምፊስ/ታህታይ ግብፅ/ ነበረች። አምላካቸውም ፒታህ ነበር። ከ11ኛው ዳይናስቲ ጀምሮ ግን መምፊስ ጣል ጣል እየተደረገች ቆይታ ከ13ኛው ዳይናስቲ በኋላ የመምፊስ ገናናነት ወደ ላዕላይ ግብፅ ወደ ቴብ ዞረና የፒታህ አምላክነትና ገናናነትም ወደ አሞን እየዞረ ሄደ።

የቀድሞውን የአሞን ቤተመቅደስም አፍርሠው ሌላ እጅግ ያማረ መቅደስ ገንብተው "የሠማይና የምድር ፈጣሪ፣ዘላለማዊ የሆነ አንድ አምላክ" ብለው እነ ሴት 1ኛ፣ እነ አሚኖፊስ 3ኛ መቅደሡን ገንብተው መንበረ አሞን/የአሞን መቀመጫ/ አደረጉና ፒታህ ምክትል አምላክ ሆነ።

141 ክፍሎች ያሉት 102 X51 ሜትር የሆነውና ዛሬ ድረስ ፈራርሶም ቢሆን የሚታየው ይህ መቅደስ የተሠራው ቅ.ል.ክ 1400-1300 ባለው ጊዜ ነበር። ይህ ዘመን ማለት ደግሞ ወደ ፊት እንደምናየው ግብፅ የኑብያ ኢትዮጵያን ቅኝ አድርጋ በሃይል የያዘችበት ዘመን ነበር።

በ12ኛው ዳይናስቲ ሳኑስትሪ (በግብፆች አጠራር) በግሪኮች ሴሶስትሪ የሚባሉት በየተራ በነገሡ ጊዜ ነበር አብርሃም ከዑር ከለዳውያን ወደ ግብፅ የተሠደደው። (ቅ.ል.ክ 2000-1800) በእነዚያ በ12ኛው ዳይናስቲ በተከታተሉ የግብፅ ፈርኦናት ጊዜም ግብፅ ከነበረው የበለጠ የሃውልት፣የቤተመቅደስ፣ የመንገድ፣ የዘመናዊ የውሃ ቦይ... ስራዎች ተስፋፍተው እየተሠሩ በምዕራብ ሊቢያን፣በምስራቅ የሲናን አገር እየወጉ አስገበሩ። ወደ ደቡብም ዘልቀው እስከ ኑብያ ሠሜን ደረሡ። እስከ 1700 ቅ.ል.ክ የ13ኛው ዳይናስቲ ነገስታት ቴብን የመናገሻ ከተማ ሲያደርጉ ነው ሁለት ታላላቅ ከተማ ሊኖራቸው የቻለው። ቴብ እና መምፊስ። ነገር ግን እንዲህ በገነኑ ጊዜ ቅ.ል.ክ 1680 "ሂክሶስ" በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ነገዶች መጥተው የግብፆችን ነገስታት ገልብጠው አገር ያዙ። እነዚህ ሂክሶሥ የተባሉት እነማን እንደሆኑ ውሣኔ ላይ ባይደረስም" ኢትዮጵያውያን መሆናቸው በብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል። ግዛታቸውም ለድፍን 100 አመት የቆየ ነበር። የሠሜኖቹ ኢትዮጵያውያን ናቸው ከሚሉት ውስጥም ጀምስ ብሩስ ይገኝበታል። ይህ ሰው "ወደ ኑብያና ወደ ሐበሻ ጉዞ" በተሠኘ ፅሑፉ "የሂክሶስ ዘሮች በኢትዮጵያ ነገደ ዮቅጣን የተባሉት ናቸው" በማለት አስረግጦ ይገልፃል።

አንዳንድ ያገራችን ፀሃፍትም ሠሜኑ ኢትዮጵያ ለ100 አመት የህል ባዶና ሠው አልባ ሆኖ ቆይቶ ነበር በማለት ህዝቡ ከ1680-1580 የት ሄዶ ነበር? በማለት ይጠይቃሉ። የሆነ ሆኖ ሂክሶሶች ለ100 አመት ግብፅን ገዝተው በ14ኛው ዳይናስቲ ተካተው ይገኛል። ብዙ የስልጣኔ ስራ እንደሠሩም ይነገራል። ስማቸውም (የነገስታቱ) የብዙዎቹ በሃውልት ላይ ተገኝቷል። "አፒፒ" ይባላል።

የአብርሃም የልጅ ልጅ የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ ወንደሞቹ ሸጠውት የመጣውና የታሠረው፣ በህልም አፈታት ምክንያት ተፈትቶ እንደራሴ የሆነውም፣ አባቱን ያዕቆብንም ከነቤተሠቡ ከከነዓን ወደ ግብፅ ያስመጣው በነዚሁ በሂክሶሶች ነገስታት ዘመነ መንግስት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

ታላቁ መፃህፍ በሃዋርያት ስራ ም7 ቁ 17-19 "የእስራኤል ህዝብ በምስር/በግብፅ/ በረከተ፣ ሌላ ንጉስ ዮሴፍን የማያውቅ እስኪነሣ ድረስ ይህ በዘመዶቻችን እየደረሠ ያለው ስለዚህ ነው.."የሚለውም ቀደምት ፈርኦኖች በሌላ ነገስታት መባረራቸውን ያስረዳል። የግብፅ ህዝብ ምንም እንኳ የሂክሶሥ ነገስታት በርካታ ስራዎችን ቢሠሩም በፀጥታ ሲገዛ አልፈለገም። አመፅ በረከተ።

ስለዚህ የቴብ የአሞን ካህናት ከላዕላይ ግብፅ ሹማምንት ጋር ተስማምተው ሳቅኑሪ 1ኛ የተባለውን ግብፃዊ መሪ አድርገው "አፒፒ 3ኛ" የተባለውን ከሂክሶሥ ወገን የሆነ ፈርኦን በነገሠበት ዘመን ውጊያ ጀመሩ። ሳቅኑሪ1ኛ ተሸንፎ ተባረረ። አሁንም ውጊያው ቀጠለ። እናም ከ1680-1580 ድረስ የቆዩትን ነገስታት በአህሞሲሥ መሪነት ከግብፃውያን ተወላጆች ጋር በመተባበር በሽሽት ያለው ሠራዊት ተደራጅቶ በመግጠም ሂክሶሶችን ማሸነፍ ተቻለ። እነርሡም ከነህዝባቸው ተበተኑ። ግማሹ ወደ ምስራቅ የቀረው በየመንገዱ በከነዓን አገር ተበተኑ።

ቀዳማዊ አህሞሲሥ ድል አድርጎ ስልጣን ከያዘ በኋላ ሂክሶሶች የመሠረቷቸውን አዳዲስ አምልኮ ጣኦቶችን እያፈራረሠ የቀድሞዎችን እየተካና እያደሠ በደንብ አሠራው። ከዚህ በኋላ ነው ግብፃውያን እንደአዲስ ተደራጅተው አገር መውረርና ግዛት ማስፋፋት የቻሉት።

የግብፅ ጦር ሠራዊት የሞዓባውያንን፣ የኤዶማውያንን፣ የፍልስጤማውያንን፣ የሂቲትን (ፓለስታይንን)፣ የዓረባውያንን ሠሜናው ክፍል ሁሉ፣ ከአሶርና ከባቢሎን በስተቀር ታናሽ እስያን/ቱርክን/ የኑብያ ሠሜኑን በሙሉ ወግተው እያስገበሩ በየአገሩ የሚገኘውን ወርቅ፣ ብር፣ መሣሪያና ልዩ ልዩ ሀብት በዘረፋም፣ በግብርም እየሠበሠቡ የግብፅን ቤተ መንግስት በሃብት አጥለቀለቁት። ነገስታቱ ሁለ ነገራቸውን በወርቅ ማሠራት የጀመሩበት ዘመንም ይህ የአህሞሲስ ዘመን ነበር። ከአህሞሲስ በኋላም "ቱትሞሲስ" በሚለው ስም 3 ነገስታት የተከታተሉ ሲሆን፤



በቱትሞሲስ 3ኛ ጊዜ ግብፅ የዓለም አገሮች የበላይ የሆነችበት ዘመን ነበር።

"ባለታሪክ ኢትዮጵያ" የተሠኘው መፅሃፍ "ቀዳማዊ ቱትሞሲሰ በነበረበት ዘመን በሞሶፖታሚያ ውስጥ የነበሩትን አሶራውያንን ባቢሎንን ድል በመምታቱ ስሙና ዝናው የገነነ ነበር" ይለናል። እናም "አቢደ" በተባለው ታላቅ ቤተ መቅደሡ ውስጥ የተገኘው ፅሁፍ "የሌሎችን ውጤት ጨምሬያለሁ፤ ከኔ በፊት በነበሩት ነገስታት ጊዜ የነበሩት አማልክት በደንብ ተመልክባቸዋል፤ መቅደሣቸውም በጥሩ ሁኔታ አሸብርቀው ታይተውላቸዋል። የግብፅን ዳር ድንበር ፀሃይ እስከምትደርስበት ድረስ ከማስፋቴ በላይ ግብፅን ከሌላ አገር የላቀች አገር አድርጌያታለሁ" ይላል።

ስለዚህም ግብፃውያን ከድንጋይ ዘመን ወደ ወርቅ ዘመን የተሸጋገሩት ከ16-15ኛው መቶ አመት ቅ.ል.ክ ሲሆን፤ እስከዚህ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያውያንን ለማስገበር ደፋ ቀና ሲሉ ነበር እንጂ ተሣክቶላቸው አልያዟትም። ከዚህ ዘመን በኋላ ግን ለ300 አመት ያህል ልንገብርላቸው ሣንገደድ አንቀርም። ከዚያ በፊት ግን ስለወንዛችን ስለ ዓባይ ቀደምት ፀሃፍት ካሉት ተነስተን፣ ዛሬ ያለበትን ሁኔታም ጨምረን ጥቂት ነገሮችን እንይ።

<u>ዓባይ</u>

ከሚያምር አዳራሹ ወጥቶ በሠረገላ ተቀምጦ እየተጎማለለ ግራና ቀኝ የደስታ ድምፅ ለሚያሠማው ህዝብ ፈገግታ እያሣዬ ለረጅም ዘመን እንደሚጓዝ መስፍን የዓባይም ውሃ ከአዳራሹ ከጣና ወጥቶ ለኑብያና ለግብፅ መሬት ህይወት እየሠጠ ከረጅም ጉዞ በኋላ ከቤተዘመዱ ከሜዲትራኒያን ባህር ይገባልና አረፍ ይላል። ይተኛልም። በጉዞው ወቅት ሁልጊዜ እግረ መንገዱን ለአሸዋማው ለግብፅ አገር የአፈር ስንቅ እንዳቀበለ ይኖራል። ለዚህ ውለታ ግብፃውያኑም፣ ኑብያዎችም ሣይቀሩ ለዓባይ የአምላክነት ደረጃ ሰጥተው በህይወት ላይ ህይወት ከምትጨምርላቸው ከፀሃይ እኩል እያመለኩ የነጭ በሬ መስዋዕት ሲያቀርቡለት ኖረዋል። ጥንታውያን ግብፆች ከኛ ይበልጥ ዓባይን በመውደድና በማክበር ያመልኩታል። ስሙን የአማልክቶቻቸው ካህናት ይኸውም ማለት የቀለም ሠዎች የሆኑት /የተማሩት/ "ሐፒ ቅዱስ ወንዝ" ሲሉት ያልተማሩት ህዝቦች ደግሞ "አቱር" ወይም እውር ወንዝ ብለውት ይገኛል።

የግብፅ አገር ራሡ የደቡብና የሠሜን አገር እንደሚባለው፤ ንጉሡም የደቡብና የሠሜን ንጉስ እንደሚባለው፤ ዓባይንም የደቡብና የሠሜን ዓባይ ብለው ምስሉን ለምለም ነገር በራሣቸው ባሠሩ፣ በእጃቸው ለአማልክት የሚሠጥ የፍራፍሬ ስጦታ በያዙ ሠዎች ተስሎ ይታያል። አንዳንድ ጊዜም ብቻውን ይሣላል። (ከምስሉ 2ቱ በሉቭር ሙዝየም

የተቀመጡትን ተመልክቻለሁ ይሉናል የዚህ መፅሃፍ ዋነኛ ምንጫችን ክቡር ተክለፃድቅ መኩሪያ) እናም የአማልክቱ ካህናት ዓባይ ከኦስሪስ (በጎ አድራጊው አምላክ) ክንድ እየፈሠሠ ለፍጥረት ሁሉ ህይወትን የሚሠጥ ራሡ ከፀሃይ የሚወዳዳር አምላክ ነው ብለው ለዚሁ ለበጎው ተግባሩና ለአምላክነቱ የሚገባ መዝሙር ደርሠውለት መዝሙሩን "ማስፔሮ" የተባለው ፈረንሣዊ ፀሃፊ ወደ ፈረንሣይኛ ተርጉሞታል፡፡

የአማልክት አገር ከሚባለው ከኢትዮጵያ ከሚመነጨው ዓባይ ህይወታቸውን ደጅ የሚጠኑ የጥንት ከተሞች መርዌ፣ናፓታ፣ቴብ፣ሔሬክሊዮፖሊስ፣መምፊስ... በሚያልፍበት መንገድ ላይ ተኮልኩለው ይታያሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ መርዌና ናፓታ የኑብያ ኢትዮጵያ፣ሔሬክሊዮፖሊስ/ሄሊዎፖሊስ/ መምፊስ፣ የግብፅ ከተሞች ናቸው፡፡ "ባለመቶው በር ከተማ" ብሎ ሄሮዱተስ የሠየማት የቴብ ኰተማ ግን በሁለቱ አገሮች መካከል ሆና የደከመ ግብፃዊ ፈርኦን ሲለቃት፣የበረታ ኢትዮጵያዊ ንጉስ ሲይዛት፣ እንደ ካምቤዝ /የሶርያ ንጉስ/ ጨካኝ የሆነ ወራሪ ሲያፈርሳት፣ከወረራ በኂላ በኢትዮጵያውያኑ ወይም በግብፃውያኑ ነገስታት መልሳ ስትሠራ የኖረች ናት፡፡ ቴብ መከረኛ ከተማ ነበረች፡፡ ለማንኛውም ግን ዓባይንና ምንጩን ለመያዝ ያላሠፈሠፈ ነገስታት አልነበረም፡፡ ዓባይ ያኔ አምላክ ተብሎ ይሠገድለታል፣ መስዋዕትም ይቀርብለታል፣ ይመለካል፣ በኂለኛው ዘመን ደግሞ የኢትዮጵያውያን ነገስታት ማስፈራሪያ ሆኖ በማገልገል "ዋ! ዓባይን ገድቤ ጉድ ሣላደርግህ ቶሎ ብለህ ጳጳስ ላክ!" እያሉ ጳጳስ ያስመጡበት ነበር፡፡

*ዛሬ ደግሞ ዓባይ ከጳጳስ ማስመጫነት ወደ ሃይል ማመንጫነት እየተዛወረ ነው፡፡ ዓባይ.. ብዙ ነገር ነበር፣ ነውም፣ይሆናልም፡፡*



## <u>ምዕራፍ I</u>

## <u>የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ</u>

ቅ.ል.ክ. ከ 2ሺ. ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያውያንና በግብፃውያን መካከል ፀብም፣ ፍቅርም ሲስተናገድ ኖሯል፡፡ ከ 1580 ወዲህ ግን ግብፆች እየገነነ በመጣው ስልጣኔያቸው አማካኝነት ግዛት የማስፋፋት ፍላጎት አደረባቸው፡፡

በቱትሞሲሥ 3ኛና በሌሎች ከእርሱ በፊት በነበሩት ፈርኦኖች ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ነገስታት የነበሩት እነ አሜንምሐት፣ እነ ጻውዕ በሰንጠረዡ ዝርዝር 17ኛና 18ኛ ላይ የሰፈሩት የኢትዮጵያ ነገስታቶች በዚያ ጊዜ የነበራቸው ሃይልና ገናናነት ከግብፅ አንፃር ሲታይ ደካማ ነበር፡፡ እናም መመከት አልቻሉም፡፡

ስለዚህ ከቱትሞሲስ 3ኛ በፊት የነበረው ፈርኦን /አህሞሲሥ/ የተባለው ከ 1580 እስከ 1557 ቅ.ል.ክ መካከል ባለው ጊዜ የኢትዮጵያን ወሰን እያለፈ መውጋትና መዝረፍ ጀመረ፡፡ ተከታዩ ፈርኦንም እንዲሁ ይበልጥ እየገፋ አገር ያዘ፡፡ ቀጥሎ የነገሰው ቱትሞሲሥ 3ኛ የተባለው ፈርኦን ደግሞ ከ 1500-1480 የነገሰው ማለት ነው ከእነርሱ በበለጠ ጦር እየላከ ኢትዮጵያን /ኑብያን/ አስያዘ፡፡

በምስራቅ በኩል ብዙ አገሮች አስገብሮ ግብፅን አገነነ፡፡ በዘረፋና በግብር የሚገኘው እቃ፣ ብርና ወርቅ የግብፅን መንግስት አከበረው፡፡ "ወርቅ ባንተ ዘንድ እንደ አሸዋ ነውና እባክህን ላክልን" እያሉ የባቢሎን ነገስታት ይለምኑት ጀመር፡፡

ሻምፖሊዮን የተባለው የፈረንሳይ ሊቅ የጥንቱን የግብፆችን ፊደል የአፈታት ሚስጢር እስኪገልጠው ድረስም እነዚህ የግብፅ ነገስታት በአገራቸው ውስጥና ከአገራቸው ውጭ የሠሩት በርካታ ታሪክ ተደብቆ ይኖር ነበር፡፡ነገር ግን የፊደሉ ሚስጢር ከተፈታ በኋላ የጀርመን፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይና የአሜሪካ ሊቃውንት በቡድን በቡድን እየሆኑ ወደ ጥንታዊቷ ከተማ ወደ መምፊስ፣ ቴብ፣ ሉክሶር ፣ ካርናቅ እየሄዱ በየሃውልቱና በየቤተመቅደሱ፣ በየቤተመንግስቱ አዳራሽ ግድግዳ ላይ፣ የፈርኦኖች አፅም በሚሸፈንበት የእንጨትና የድንጋይ ልባሥ በውስጥም በውጭም እንደ ስዕል ተስሎ ከሚገኘው ፅሑፍ ላይ ተገልብጦና ተተርጉሞ የብዙ ፈርኦኖች የጦርነት፣ የመንግስትና የነገስታት፣ የአማልክትና የካህናቱ ታሪክ ከነስርዓቱ ተገኘ፡፡ በዚህም ውስጥ ፈርኦኖች እነራምሲስ፣ እነቱትሞሲሥ 3ኛ ኑብያን ያስገበሩበት ታሪክ አብሮ ተገኝቷል፡፡

ቱትሞሲሥ 3ኛ በግብፅ በ18ኛው ስርወ መንግስት / ዳይናስቲ/ ውስጥ ከነገሱት ዋና ዋና ፈርኦኖች ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ በካርናቅ

ቤተመቅደስ ግድግዳ ላይ ተገኝቶ የተተረጎመው ታሪክም በምስራቅ አገር አሶራውያንን፣ ፊኒቃውያንን፣ በደቡብ በኩል የኑብያን አገር ማስገበሩን እንዲሁም የእርሱ እህት የሆነችው ሐታሱ የተባለችው የስልጣን ተካፋይ ሆና ለብቻዋ ጦር አዘጋጅታ ፑንት የሚባለውን ሀገር ወግታ ልዩ ልዩ የከበሩ እቃዎችን እንዳስመጣች ታወቀ።

ፑንት የሚባለው አገር ደግሞ ቀደም ሲል እንዳየነው ከሰሜናዊ ኢትዮጵያችን እስከ ኤልማንደብ የሚያጠቃልልና የየመንንም ግዛት የሚያካትት ነው። በዚህ በተገኘው ፅሁፍም የወረራ ምክር የለገሷቸው ጣኦታቱ እንደሆኑ የሚገልፅ ሲሆን፤ ቱትሞሲሥ 3ኛም በጦር መሳሪያና በበርካታ ሠራዊት የኑብያ ኢትዮጵያን መውጋቱን ይገልፃል።

ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ለግብፅ አንገዛም ብለው የፈርኦኖቹን ሃይል ይመልሱ የነበሩት ኢትዮጵያውያን በቱትሞሲሥ 3ኛ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ተሸንፈው ገበሩ። የቀሩትም ውጊያውንና ዘረፋውን መቋቋም ተስኗቸው ወደ አትባራና ወደ ተከዜ ሸሹ። ቀጥሎ ባለው ጊዜ የግብፅ ጦር ወደዚሁ ሸሽተው ወደመጡበት አገር ዘልቆ በመርከብ መጥቶ ወግቶና ባላባቶችን ማርኮ ተመለሰ እንጅ በሰሜኑ ኢትዮጵያችን ጦሩን አላሰፈረም።

በቴብ ከተማ በካርናቅ የአሞን ቤተ መቅደስ ውስጠኛ ግድግዳ ላይ "ቱትሞሲሥ 3ኛ ራ-ሜን- ኬፐር /ደጉ አምላክ/ የሁለቱ አገራት /የደቡብና የሠሜን፣ የግብፅና የኩሽ/ ንጉስ፣ ለዘላለም የሚኖረው በጦር ያስገበራቸው አገሮች" ተብሎ የ15 አገሮች ስም በዝርዝር ተፅፎ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥ በመጀመሪያው መስመር የሚገኘው የኛው የኩሽ አገር ነው። በተዘረዘሩት አውራጃዎች ውስጥ ኡትሊት፣ ታካሩ፣ ሐማሱ፣ ታና የሚል ቃል ስላለበት አዱሊስ፣ ትግሬ፣ አማሴን፣ ጣና ማለቱ ሳይሆን አይቀርም የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።

ከዝርዝሩ ጎን ደግሞ የፑንት አገር ሰዎች የገበሩበት ስዕል ይታያል። እንግዲህ ግብፆች የቀድሞ ኢትዮጵያ የሚባለውን የዛሬውን ሱዳን ከያዙ በኋላ ከአትባራ ወዲህ ሠሜኑንና ምስራቁን የዛሬውን ኢትዮጵያ ጦር እየላኩ አስገበሩ እንጂ ቋሚ ጦር አስቀምጠው አልገዙትም ማለት ነው። የኑብያን ግን ግዛቱን በሙሉ ወደራሳቸው ግዛት ደባልቀው ሹም ሽር እያደረጉ በገዥነታቸው ሊቀጥሉ ችለዋል።

ለዚህ ግዛት የበላይ አስተዳዳሪም የፈርኦኑ የበኩር ልጅ አልጋ ወራሹ ሆነ። የማእረግ ስሙም "የኩሽ ንጉሳዊ ገዥ" ተባለ። በስሩም ከቀድሞዎቹ ከኢትዮጵያ ነጋሲዎች ውስጥ ታማኝ የተባለው እየተመረጠ የበታች ሆኖ ይገዛ ጀመር። እነዚህ የኑብያ ኢትዮጵያ ነገስታትና ህዝቦችም በተመቻቸው ጊዜ የግብፅን ገዥዎች አባረው የራሳቸውን መንግስት ለማቋቋም ደፋ ቀና ማለታቸውን ገፉበት። ነገር ግን ከቱትሞሲስ 3ኛ በኋላ



የተነሱ ፈርኦኖች የበለጠ እየገነኑ ስለሔዱ የነፃነት ተስፋቸው እየመነመነ ሔደ።

ከቱትሞሲሥ 3ኛ በኋላ ከተነሱት ከሀይለኞቹ ፈርኦኖች መካከል ደግሞ ይበልጥ ገናናና ስመጥር የሆነው ራምሲሥ 2ኛ ሲሆን፤ እርሱም ኑብያን መግዛቱን ቀጥሏል። በ18 አመቱ እንደነገሰና ኑብያውያን ሸፍተውበት በድጋሚ ድል እንዳደረጋቸውም ታውቋል።

ታላቁ ራምሲሥ ዳግማዊ የግዛት ዘመኑ ከ1292-1225 ቅ.ል.ክ ሲሆን በዚህ የግዛት ዘመኑም ግብፃውያንን፣ የኑብያ ኢትዮጵያውያንን ፣ ሊቢያን፣ የከነዓንንና የሶርያን፣ የሞሶፖታሚያን አገሮች 67 አመት ገዝቶና አስገብሮ በ85 አመቱ ሞቷል። እስከዚህ ጊዜ ድረስም የኑብያ ኢትዮጵያውያን በተገዥነት ላይ ነበሩ። ከታላቁ ራምሲስ ቀጥሎ ሜኔፕታህ የተባለው ልጁ ሲነግስ ልክ በዚያው ወቅት እስራኤሎች በሙሴና በአሮን እየተመሩ ግብፅን ለቀው ወደምድራቸው የተጓዙበት ዘመን ነው።

ሙሴ በነበረበት ዘመን የግብፅ ንጉስ/ፈርኦን/ የነበረው መጠሪያ ስሙ ራምሴስ እንደሆነና፤ ሜኔፕታህ እንደተካው፤ በዚህ በሻምፖሊዮን ጥናት ይፋ ተደርጓል። ራምሲሥ ማለት ደግሞ የፀሀይ ልጅ የሚል ትርጓሜ አለው። ይህ ንጉስ የእስራኤሎች መብዛት ባሰጋው ጊዜ "የበኩር ወንድ ይገደል" የሚል ትዕዛዝ ያስተላለፈው ነው። ይህ ንጉስ ከንጉስ ሰለሞን የበለጠ ሚስትና

እቁባት እንደነበረው፤ ከሚስቶቹ ውስጥ ደግሞ ሶስቱ የራሱ ልጆች እንደነበሩና ባጠቃላይ 111 ወንድ ልጆችና 51 ሴት ልጆች ነበሩት ተብሏል። ሌላው ደግሞ እስራኤሎችን አልለቅም ያለውና በኋላ ላይ ለቆ እነርሱን ሲያሳድድ በኤርትራ ባህር ሰጠመ በማለት መፅሐፍ ቅዱስ ፈርኦን ብሎ የጠራው ንጉስ ስሙ ሜኔፕታህ እንደሆነና /ያፕታህ ወዳጅ/ የሚል ትርጉም እንዳለው ተረጋግጧል።

እርሱም የገዛበት ዘመን ከ1225-1215 ድረስ እንደነበር ታውቋል። የኑብያ ኢትዮጵያን ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ገዛ ያልነው የቱትሞሲሥ 3ኛ የግዛት ዘመን በ18ኛው ዳይናስቲ የሚካተት ነው ብለናል። የራምሲሥ 2ኛና የሜኔፕታህ የነጋሲነት የዘር ሃረግ /ዳይናስቲ/ 19ኛው ሲሆን፤ የ20ኛው ዳይናስቲ ደግሞ እንደርሱ የቴብ ዘር የሆነው ከገዛ በኋላ፤ የ21ኛው ዳይናስቲ የተመሰረተውም የታኒትና የቴብ ድብልቅ ከሆነ የዘር ሃረግ ነው።

22ኛው ደግሞ የነጋሲ ዘር የሆኑት የሊቢያና የቡባስቲ ነገድ ተብለው በየተራ ከገዙ በኋላ 23ኛው ዳይናስቲ የታኒት ዘር፤ 24ኛው የሳይስ ዘር ተብሎ ተዘርዝሯል።

ከዚህ በኋላ ግን የግብፅን 25ኛውን ስርወ መንግስት /ዳይናስቲ/ ኢትዮጵያውያን እንደመሰረቱት ነው የተረጋገጠው። ይህንንም ቀጥለን በስፋት የምናየው ይሆናል።

በእነዚህ በተዘረዘሩት ፈርኦኖች የግዛት ዘመን ጊዜ የኑብያ ኢትዮጵያ ለግብፅ እየገበሩ መኖራቸው በበርካታ ማስረጃ የተረጋገጠ ነው። (National Geography feb,2008) ይህም ሲሆን በኑብያ ያሉ ነገስታቶች ሃይማኖታቸው ከእነርሱ ጋር እየጠነከረ፣ እነርሱ የሚያመልኩትን እያመለኩ፣ ቋንቋቸውን እየተናገሩና በአጠቃላይ በሁለነገራቸው ከእነርሱ ጋር ተመሳስለው ከመኖራቸውም በላይ፤ በጣም ጥልቅ ትስስር ከመፈጠሩ የተነሳም የጣኦታቱ የነአሞን አገልጋይ ካህናት እስከመሆንና ልዩ ልዩ መንፈሳዊና ስጋዊ መስተዳድሮች ላይ በታማኝነት ሊሾሙ ችለዋል። እዚህ ላይ አንባብያን በድጋሚ ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ አለ። ይኸውም ይህ ሁሉ በኑብያ ኢትዮጵያ ሲከወን የአሁኗ ኢትዮጵያ መስራቾች አክሱማውያን በዚያው በኢትዮጵያችን ሠሜናዊ ክፍል እንደሰፈሩና በራሳቸው ነገስታት እየተዳደሩ፤ እንዲሁም ኑብያን የገዙትና ያስገበሩት ግብፃውያን ድንበር ዘልቀው ገብተው ሲያስገብሯቸው እንጅ በሙሉ ሃይላቸው መጥተው ሠፍረው ቋንቋቸውን አልበረዙም፣ ባህልና ልማዳቸውም አልተቀየጠም። እዚያው በሰፈረ የግብፅ ሃይል ተገዙ የሚል ማስረጃም የለም። ነገር ግን የኑብያ ኢትዮጵያና የአክሱሙ ኢትዮጵያ አንድ አገር ነበሩና፤ ልንል የምንችለው ግብፆች ከፊሉን ኢትዮጵያ ገዙ፣ ከፊሉን ደግሞ በርቀት ሆነው አስገበሯቸው ነው።

በእነዚያ ዘመናት በኑብያ ያሉት ኢትዮጵያውያን ውስጥ ለውስጥ የነፃነት እንቅስቃሴ ሲያደርጉና ያገኙትን የመንፈሳዊና ስጋዊ አስተዳደር ስልጣን ተጠቅመው የግብፅን ግዛት ነቅለው ለመጣል ሲሞክሩ ቆይተዋል። ከረጅም ጊዜ በኋላም ተሳክቶላቸው የግብፅን ሰራዊት ጠራርገው ለማስወጣትና ነፃነታቸውን ለመቀዳጀት ችለዋል። በአጠቃላይ የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ የቆየው ከ1500-1200 ቅ.ል.ክ እንደነበር ታውቋል። ይህም ማለት ለ300 አመታት ያህል መሆኑ ነው። የኢትዮጵያውያን ሐብት በከፍተኛ ሁኔታ የተዘረፈበት ዘመን መሆኑም የታወቀ ነውና ናፓታ ለጊዜው ቀዝቀዝ ብትል አይገርም



## ምዕራፍ ፲፩

## ከንግስት ሳባ እስከ ንጉስ ባዚን ያሉት የኢትዮጵያ ነገስታት ዝርዝር

የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ በቆየበት ወቅት ግብፆች ሲመጡ መመከት አቃታቸው ካልናቸው ከአሚን አምሃት 1ኛና ከፃውእ በኋላ እንዲሁም ግብፆች እስከወጡበት እስከ 1200 ድረስ የነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታትና ከእነርሱ በኋላ እስከተዘረዘሩት እስከ ተዋስያ ዴውስ፤ ማለትም ከንግስተ ሣባ በፊት እስካለውና ከ1026 እስከ 1013 ድረስ እስከነገሰው ያሉት የኢትዮጵያ ነገስታቶች በግዛት ዘመናቸው ምን እንደፈፀሙም ሆነ ስለ ሌላ ተያያዥ ታሪካቸው የሚገልፅ ማስረጃ ከስም ዝርዝራቸው በቀር አልተገኘም። ምናልባትም የኑብያ ኢትዮጵያ ከግብፅ ቀንበር ከተላቀቀ በኋላ እየቀዘቀዘ ሄዶ ከኤርትራ ባህር ወዲህና ወዲያ ያለው ግዛት ገነን እያለ ሣይሄድ አልቀረም። ለማንኛውም እስካሁን ያየናቸው ታሪኮች ሁሉ የተከናወኑት ከንግስተ ሣባ በፊት በነበረው ዘመን ነው። ቀጥለን ከምናየው የነገስታት ዝርዝር በኋላም ከንግስት ሣባ ጀምሮ ያለውን ታሪክ ይሆናል የምንመለከተው። እነዚህን ነገስታት ስናይም በሠሜኑ ኢትዮጵያችን በኋላ የገነነውና አሁን ድረስ ገናናነቱን በሃውልቱና በፅሑፉ ያወቅነው የአክሱም መንግስት እስካሁን ማለትም ቢያንስ ከ1ሺ. ቅ.ል.ክ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ ጊዜ ድረስ ጥቂት ቀደም ብሎ ባለው ዘመን እጅግ አለመግነኑንና አለመታወቁን ስንረዳ፤ ነገር ግን ከዚህ ዘመን በፊት በክልሉ በአክሱምና አካባቢው እንደነበረ በብዙ መረጃ የተረጋገጠ ነው። በመጀመሪያ ናፓታ፣ ቀጥሎ መርዌ፣ ከዚያም አክሱም የኢትዮጵያ ነገስታቶች መናገሻ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፤ ንግስተ ሣባ ግን በጥንቱ አጠራር ሣባ በምትባለውና በአክሱም አቅራቢያ በምትገኘው ከተማ መንገሷን ቀጥለን የምንረዳው ይሆናል።

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስም | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የገዙበት ዘመን ከ.ክ.ልደት በፊት |
|---|---|---|---|
| 1 | ንግስተ ሳባ | 31 | 1013 -982 |
| 2 | ሚኒልክ 1ኛ | 25 | 982-957 |
| 3 | ሐንድዮን | 1 | 957 -956 |
| 4 | ሲራህ 1ኛ | 26 | 956 -930 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | አሜን ሆቴብ /ዘግዱር/ | 41 | 930 -889 |
| 6 | አክሱማይ ራሚሱ | 20 | 889 -869 |
| 7 | ሲራህ 2ኛ | 38 | 869 -831 |
| 8 | ተዋስያ 2ኛ | 21 | 831 -810 |
| 9 | ፒያንኪ 2ኛ /አብራሊዮስ/ | 32 | 810 -778 |
| 10 | አክሱማይ ወረደ ፀሀይ | 23 | 778 -755 |
| 11 | ካስታህ ሐንዲዮን | 13 | 755 -742 |
| 12 | ሻባካ | 12 | 742 -730 |
| 13 | ኒካንታ ህንዳኬ | 10 | 730 -720 |
| 14 | ቲሃርቃ /ወረደ ነጋሽ/ | 49 | 720 -671 |
| 15 | አርድአሜን አውስያ | 6 | 671 -665 |
| 16 | ገሰዮ | 6 ሰዓት | 665 -665 |
| 17 | ታንታሙን | 4 | 665 -661 |
| 18 | ቶማድዮን ፒያንኪያ 3ኛ | 12 | 661 -649 |
| 19 | አሚን አሳሮ 2ኛ | 16 | 649 -633 |
| 20 | ፒያንኪያ አውጥዮ 4ኛ | 34 | 633 -599 |
| 21 | ዝዋሬንብረት አስፑርታ | 41 | 599 -558 |
| 22 | ሰይፋይ ሐርሲኣተው | 12 | 558 -546 |
| 23 | ራምሃይ ናስቶሰኔን | 14 | 546 -532 |
| 24 | ሐንዲው አብራ | 11 | 532 -521 |
| 25 | ሰፎሊያ ኒኮቦን | 31 | 521 -490 |
| 26 | አግልቡል ሰዌኮስ | 21 | 490 -469 |
| 27 | ጽዕመረት /ወረደ ነጋሽ/ | 21 | 469 -448 |
| 28 | አውስያ ብራኩስ | 12 | 448 -436 |
| 29 | ቀኒዝ ጽሰሜዝ | 13 | 436 -423 |
| 30 | አጽራስ | 10 | 423 -413 |
| 31 | ካስታህ ወልደ እሁህ | 20 | 413 -393 |
| 32 | ኤላልዮን ቲአንኪ | 10 | 393 -383 |
| 33 | አርቲስክ አሚን 3ኛ | 10 | 383 -373 |
| 34 | አርቲስክ አሚን 4ኛ | 10 | 373 -363 |
| 35 | ሐዲና | 10 | 363 -353 |
| 36 | አርቲስክ አሚን 5ኛ | 10 | 353 -343 |
| 37 | አርቲስክ አሚን 6ኛ | 10 | 343 -333 |



| | | | |
|---|---|---|---|
| 38 | ኒካውላ ህንዳኬ 3ኛ | 10 | 333 -323 |
| 39 | ባስኡ | 7 | 323 -316 |
| 40 | ኒካውላ ህንዳኬ 4ኛ | 10 | 316 -306 |
| 41 | አውጥጥ አራውራ | 10 | 306 -296 |
| 42 | አርካሚን 2ኛ | 10 | 296 -286 |
| 43 | ክልአስ 2ኛ | 10 | 286 -276 |
| 44 | ዙዋሬ ንብረት | 16 | 276 -260 |
| 45 | ስትዮ | 14 | 260 --246 |
| 46 | ሰይፋይ | 13 | 246 -233 |
| 47 | ኒኮሲስ ህንዳኬ 5ኛ | 10 | 233 -223 |
| 48 | ራምሐይ አርሚን 4ኛ | 10 | 223 -213 |
| 49 | ፊልያ ሁርኔክሐት | 15 | 213 -198 |
| 50 | ሃንዲ አውኪራራ | 20 | 198 -178 |
| 51 | አግሐቡ ብሴህራን | 10 | 178 -168 |
| 52 | ሉሳይ ከዋውማኑን | 20 | 168 -148 |
| 53 | መሰልኒ ቁራርሜር | 8 | 148 -140 |
| 54 | ነክሳይ ብስንቲ | 10 | 140 -130 |
| 55 | ኤትቢኑ ካውር | 10 | 130 -120 |
| 56 | ሰፊልያስ አብራሚን | 20 | 120 -1 0 |
| 57 | ሠናይ | 10 | 100 -90 |
| 58 | አውሲና ንግስት | 11 | 90 -79 |
| 59 | ዳዊት 2ኛ | 10 | 79 -69 |
| 60 | አግልቡስ | 8 | 69 -61 |
| 61 | በዋውል | 10 | 61 -51 |
| 62 | ባረዋስ | 10 | 51 -41 |
| 63 | ዳኒዳድ | 10 | 41 -31 |
| 64 | ኣሞይ መሐሲ | 5 | 31 -26 |
| 65 | ኒክትራስህንዳኬ 6ኛ | 10 | 26 -16 |
| 66 | ኖልኪ | 2 | 16 -14 |
| 67 | ሉዛይ | 8 | 14 -6 |
| 68 | ባዜን | 6 | 6-1 ዓ.ም ህረት |

(አጭር የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በአለቃ ታዬ)

ባዚን በኢትዮጵያ በነገሠ በ6ኛ ዓመቱ ኢየሱስ በቤተልሔም ተወለደና የዘመን አቆጣጠሩም እንደ አዲስ ወደፊት እንድ ተብሎ መቆጠር ጀመረ።

ከንግስተ ሣባ የሚነሳው የኢትዮጵያ የነገስታት ዝርዝር ዶክተር ሬይዝነርና ሌሎች የአገራችን ፀሃፍት፤ እንዲሁም መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው የታሪክ መዛግብት ባየነው መልኩ ነው የሚዘረዝሯቸው። የሁሉም መነሻ የአገራችን ክብረ ነገስትና ታሪክ ነገስት መሆኑም ይታወቃል።



## ምዕራፍ ፲፪
## የንግስተ ሳባ ታሪክ

ንግስቶ ሳባ የነገሠችው በአክሱም አቅራቢያ በጥንቱ አጠራር ሳባ በምትባለው ከተማ ነበር።ንግስቶ ሳባ በአባቷ በአጋቦሥ /ተዋስያ/ እግር ተተክታ ኢትዮጵያን መግዛትና ማስተዳደር የጀመረችው ከክ.ልደት በፊት ከ 1ሺ 13 ጀምሮ ነው።
ንግስቶ ሳባ የሚለውም ስሟ ሳይሆን የሳባውያን ንግስት ማለት ነው።

የንግስቶ ሳባ መጠሪያ ስሟ በክብረ ነገስት ማክዳ፣ በመጽሐፈ ነገስት በቀዳማዊና ካልዕ፣ በዜና መዋዕል ንግስቶ ሳባ፣ በወንጌል ንግስቶ አዜብ ትባላለች።

በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ወሰን ወይም የንግስቶ ሳባ ግዛት ስፋቱ በምስራቅ እስከ ማዳጋስካር፣ እስከ ፋርስ ባህር፣ በምዕራብ እስከ ኑብያ፣ እስከ ምስር/ግብፅ/ ጠረፍ፣ በደቡብ እስከ ኒያንዛ የቪክቶሪያ ባህር ድረስ ነው ይባላል። በእርሷ ዘመን በኢትዮጵያ የዓረብ፣ የግብፅ፣ የህንድ፣ የእየሩሳሌም ሰዎች የዘመኑን ሽቀጣሽቀጥ ልብስ፣ ሽቶ፣ እጣን፣ ወርቅና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ይነግዱ ነበር። በዚሁ ዘመን ደግሞ በእየሩሳሌም የነገሰው የዳዊት ልጅ ሠለሞን ነበር።





Solomon embraced and
311 x 318 - 36k - jpg
mythencyclopedia.com

ንግስተ ሳባ በኢትዮጵያ፣ ሰለሞን በእየሩሳሌም ነግሰው በነበረበት ዘመንም ታምሪን የሚባል ነጋዴ ከኢትዮጵያ ወደ እየሩሳሌም እየተመላለሰ ይነግድ ነበር።

እርሡም ለንጉሥ ሰለሞን የሚሆኑ ጥሩ ጥሩ እቃዎች ከኢትዮጵያ ገዝቶ ወስዶ ለሠለሞን ካስረከበ በኋላ፤ ሲመለስ የሰለሞንን የቤተ መንግስት ስነ ስርዓትና ጥበቡንም፣ ክብሩንም ሁሉ ለንግስተ ሳባ ነገራት።

በታምሪን አማካኝነት የተጀመረው ግንኙነትም እየቀጠለ ሔደ። በዚህ ነጋዴ አማካኝነትም በሁለቱ ነገስታቶች አገር የማይገኙ እቃዎችን በስጦታ መልክ ይላላኩ ጀመር። ንግስተ ሳባ የንጉስ ሠለሞንን ጥበብ፣ የቤተመንግስቱንና የስርዓቱን ሕግ እና አደረጃጀት በደምብ ከሚያውቀው ከታምሪን እንደበት ብዙ ጊዜ እየጠየቀች ከሰማች በኋላ በመጨረሻ በጆሮዋ የሰማችውን በአይኗ ለማረጋገጥ በብዙ ወታደሮቿና ደንገጡሮቿ ታጅባ ለሠለሞን የምታበረክተውን ልዩ ልዩ ስጦታ አስጭና በነጋዴው መሪነት ወደ እየሩሳሌም ተጓዘች።

በደረሰችም ጊዜ ንጉስ ሠለሞን በታላቅ ክብርና በደስታ ተቀበላት። እርሷም ከኢትዮጵያ ይዛለት የሄደችውን የከበረ እንቁና ወርቅ፣ ሽቱና ሌሎች ስጦታዎችን አበረከተችለት።



ንጉስ ሰለሞንም ስጦታውን በክብር ተቀብሎ ልዩ ማረፊያ ቦታ መርጦ ለእርሷና ለአጃቢዎቿ አዘጋጀላቸው። በየቀኑም በእርሱ ትዕዛዝ በሬ፣ በግና ፍየል እንዲሁም መጠጥ ለአጃቢዎቿም ለራሷም እንደ ደንቡ ሲያቀርብላቸው ቆይቶ፤ አንድ ቀን ንጉስ ሠለሞን ለንግስተ ሣባ ክብር ትልቅ ግብር/ግብዣ/ አዘጋጅቶ ጠራት።

ከዚህ ግብዣ ቀደም ብሎም ቤተመንግስቱንና ቤተመቅደሱን ሲያስጎበኛት ነበር። በዚህ እለት ደግሞ ስለ እርሷ ክብር በተዘጋጀው ግብዣ የአዳራሹን አይነት፣ የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን አገባብና አቀማመጥ ለማሳየት በራሱ ዙፋን አቅራቢያ ለእርሷ ልዩ ዙፋን አዘጋጅቶ ዙፋኑንም እሷ ከውስጥ ሆና ማናቸውንም ነገር ለማየት እንድትችል፣ ከውጭ በኩል ግን እሷን ማንም እንዳያያት ተደርጎ በተሠራ መስታዎት መሠል ነገር አስጋርዶ አስቀመጣት። በዚህ ባማረ ዙፋን ተቀምጣ የመሳፍንቱን፣ የመኳንንቱን፣ የወታደሩን አገባብና አቀማመጥ፣ በየክፍሉ የሚያገለግሉትን የወይን ጠጅ አሳላፊዎችንና ሠራተኞችን አለባበሱና የስራቸውን ቅልጥፍና እየተመለከተች ተደነቀች።

ግብዣው ሲጠናቀቅም ንጉስ ሠለሞን ንግስተ ሣባን ሊያነጋግራት እርሷ ወዳለችበት ዙፋን አመራ። እርሷም፡- "የጥበብህንና የስራህን ነገር እዚህ ሆኜ በአይኔ ተመለከትኩት፤ በአገሬ ሳለሁ ከሰማሁት እጅግ ይበልጣል" በማለት አድናቆቷን ገለፀች።

ከዚያም ወደተዘጋጀላት ሠፈሯ ለመሄድ ስትጠይቀው "መሽቷልና እዚህ እደሪ" አላት። በዚህ ጊዜ ሌሊት ላይ ንጉስ ሰለሞን ንግስተ ሳባን ተገናኝቷት አደረ፤ እናም ፀነሰች። በዚህ ጊዜ ንግስተ ሳባ "ልጅህ መሆኑን የምትረዳበት ምልክት ስጠኝ" በማለት ከሠለሞን የጣቱን ቀለበት ተቀብላ በቶሎ ወደ አገሯ ተመለሰች። /እዚህ ላይ ታሪክ ነገስትና ክብረ ነገስት ሠፋ ያለ ሐተታ በመስጠት አግሯ ላይ ሽሆና እንደነበርና እየሩሳሌም ስትደርስ እንደወለቀላት፤ ጨው የበዛበት ምግብ አብልቶ በውሃ ጥም ወደ እሱ መኝታ ውሃ ፍለጋ እንደሄደችና በዚያ ዘዴ እንደተገናኛት.... ወዘተ የሚል ነገር አስፍሮ ይገኛል/። የሆነ ሆኖ ንግስተ ሳባ ፀንሳ ልትመለስ ስትነሳ በእየሩሳሌም ርስት ይሆናት ዘንድ ቦታ ሠጥቷት አብያተ ክርስቲያናት ታንፀውበት ዛሬ ድረስ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። /የዴር ሱልጣን ገዳምን/

ንግስት ሳባ ከነአጃቢዎቿ ወደ አገሩዋ ስትመለስ የኤርትራን ባህር ተሻግራ በሐማሴን አውራጃ ማይበላ ከተባለው ቦታ /አገር/ ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች።

ንግስት ሳባም የወለደችውን ልጅ ስሙን እብነ መለክ የሚል ስም አወጣችለት። ትርጉሙም የንጉስ ወይም የገዥ ልጅ ማለት ነው። እብነ ሐኪምም ተብሏል። ይህም የብልህ ልጅ ማለት ነው።

የመጀመሪያውም ሁለተኛውም የስም ስያሜ የግንቱ የሳባውያን አነጋገር ሲሆን፤ ታሪኩ የሰፈረበት ክብረ ነገስት በግባውያን ቋንቋ ተፅፎ ስለነበርና በኋላ ላይ እንንበረእድ ይስሐቅ ወደ ግዕዝ ሲተረጉሙ የአረብኛውን ስም እንዳለ ወስደው እንደተረጎሙት ይነገራል።

ምኒልክም አድጎ ሐያ አመት እንደሞላው "አባቴ ማነው ንገሪኝ" ብሎ እናቱን ሲጠይቅ እርሷም "የእየሩሳሌሙ ንጉስ ሠለሞን ነው" ብላ ነገረችው። አባቱን ሠለሞንን ለመገናኘትም የእናቱን ፈቃድ ጠይቆ ወደ እየሩሳሌም ሔደ።

አባቱ ንጉስ ሠለሞንም ልጁን በደስታ ተቀበለው፤ ባየውም ጊዜ ስሞ ባረከው። ምኒልክ ለ3 ዓመታት ያህል በእየሩሳሌም የኦሪት ህግ፣ የመንግስት አስተዳደር በእብራይስጥ ቋንቋ ተምሮ ሲጨርስ፤ ወደ እናቱ ወደ ንግስተ ሣባ ተመለሰ። ሲመለሡም ንጉስ ሠለሞን ልብሰ መንግስት አልብሶ ከ12ቱ ነገደ እስራኤል 12ሺ የእብራዊ የበኩር ወንድ ልጆች /ከእያንዳንዱ ነገድ አንድ አንድ ሺ ማለት ነው።/ የዳዊትን ልጅ ወንድሙን ጨምሮ ብልሆችንና አዋቂዎችን መርጦ፤ ከተማሩትም ካህናት እንዲሁም ከመሳፍንቱ ልጆች 22 ታላላቅ ሹማምንት ጋር የኢትዮጵያ ንጉሰነገስት ይሆን ዘንድ ልብሰ መንግስቱን አሠፍቶ፣ ቅብዓ ሜሮንን በሊቀ ካህናቱ በሳዶቅ አስቀብቶ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 ወደ ኢትዮጵያ ሸኘው።

ንግስተ ሣባ ልጇ ምኒልክ ከእየሩሳሌም ሲመለስ በታላቅ ክብር ሠልፍ አድርጋ ተቀበለችው። ምኒልክና ሰዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አዛርያስ በሚባለው ሊቀ ካህን አማካኝነት በልዑል እግዚአብሔር ጣቶች ተቀርፆ ለሙሴ የተሰጠው እውነተኛ ፅላት ወደ ኢትዮጵያ አብሮ መጣ።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ገሚሱ አባቱ ንጉስ ሠለሞን ፈቅዶለት እንደሰጠው፤ ሌላው በድብቅ ይዞት እንደመጣ ይገልፃል። ያም ሆነ ይህ ፅላቱ/ታቦተ ፅዮን/ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ በግልፅ የሚታወቅ ሲሆን፤ በአክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን አምላክ በመረጣቸው ሠዎች እየተጠበቀ እንደሚገኝ ነው የሚታወቀው።

ከዚያም ንግስተ ሣባ ምኒልክን ተቀብላ በሕያወች እያሏት በኢትዮጵያ አነገሰችው። ንግስተ ሳባ በኢትዮጵያ ለመንገሷ ከመፅሐፍ ቅዱስ ጀምሮ በሁሉምታሪ ካዊና መንፈሳዊ ፅሁፎች ውስጥ የተረጋገጠ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ፤ ገናና ንግስትና በጥበብ የተሞላች እንደነበረችም ይታወቃል። .

ከዚህም በላይ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ገፅታ መለወጧን ልብ ይሉታል። ይህም የንግስናውን ዘር ከእየሩሳሌሙ ጥበበኛ ንጉስ ጋር



በማስተሳሰሯ ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም ብዙሃኑ በጣኦት ማምለኩን ትቶ በኦሪተ ህግእየተመራ እውነተ ኛውን አምላክእንዲያውቅ የተደረገው/ በፍላጎት/ በእርሡዋና በልጇ ዘመን ነው።

ጤፍ ለምግብነት የዋለው በእርሷ ዘመን እንደሆነ ስለሚነገርላት ስለዚች ንግስት በርካታ ፀሃፍት የፃፉላት ሲሆን፤ ከግሪክ ሊቃውንት እንደ ሔሮዱተስ፣ መልዚ፣ ሆሜር...... ከኢጣልያ ሊቃውንትም ሆነ ከሌሎች የአውሮፓና እስያ ታሪክ መርማሪዎች ብዙ ብለውላታል። ሞሪዮ የተባለው የፈረንሳይ ሊቅም ስለ ንግስተ ሳባ ሲገልፅ «በአክሱም አጠገብ በምትገኝ ሳባ በምትባል ከተማ ተቀበረች። ከመቃብሯ ላይም 24 ሐውልቶች አሉበት። አሁን ግን ተሠባብሮ አልቋል» ይላል።

ከንግስተ ሳባ ጋር በተያያዘ ተደጋግሞ የሚነሳው ጥያቄ ንግስተ ሳባ የዓረብ ንግስት ወይስ የኢትዮጵያ? የሚል ነው። ከአምስት በላይ የሆኑ አገራትም የኛ ናት እያሉ ይሻሟታል። ነገር ግን የተነሳችው ከቀድሞዋ የኢትዮጵያ ግዛት እስከሆነ ድረስ ፤ የዛሬውን ክፍፍል መነሻ አድርጎ መወዛገብ አይገባም። ያም ቢሆን ግን በዛሬው የካርታ ክለሳም ብንሄድ ሣባ የኢትዮጵያ ነች። የተቀበረችውም በአሁኗ ኢትዮጵያ እንደሆነ በርካታ ፀሃፍት የተስማሙበት ነው። በተረፈ ..... ሣባ የመጣችው ከዘንዶ ነው ...... ወዘተ ... የሚል ሐተታ ይገኛል። በብዙዎቹ የዛሬ ሊቃውንት አይታ ይሄ መሰሉ ሃተታ ተረት ተረት ተብሏል። ነገር ግን ሚስጥራዊ አገላለፅ ይመስላል።

ለማንኛውም ንግስተ ሳባ /ማክዳ/ በኢትዮጵያ 31 ዓመት ገዝታ ልጇን ምኒልክን በሕይወቷ እያለች ተክታ አልፋለች